ወወጽአት መንፈሱ በዲበ ዓራቱ፣

ባልጋው ላይ ሳለ ነፍሱ ከሥጋው ተለየች፤

ምዕት ወኃምሣ ወሰመንቱ ዓመት ሎቱ፤

በሞተ ጊዜ መቶ ኃምሳ ስምንት ዘመን ሆኖት ነበር፤

ወቀበርዎ በክብር፣

አክብረው ቀበሩት፤

፲፪፤ ወአመ ሞተት ሐና እሙ ቀበራ ጦብያ ወልዱ ምስለ አቡሁ፣

ሐናም በሞተች ጊዜ ልጁ ጦብያ ከአባቱ ደረባት፤

ወሖረ ጦብያ ምስለ ብእሲቱ ወደቂቁ ውስተ ባጥና ኀበ ራጉኤል፣

ጦብያ ከሚስቱና ከልጆቹ ጋራ ወደ ራጉኤል ዘንድ ወደባጥና ሄደ፤

፲፫፤ ወረስዐ ራጉኤል ወእድና ብእሲቱ፣

ራጉኤል አረጀ፤ እድና ሚስቱም አረጀች፤

ወሞቱ፣

ሞቱ፤

ወቀበሮሙ ጦብያ በክብር ለታሕማሁ፤

ጦብያ አማቶቹን አክብሮ ቀበራቸው፤

ወተዋረሰሙ ኵሎ ንዋዮሙ፣

ገንዘባቸውንም ወረሰ፤

ወለጦቢትኒ አቡሁ፣

አባቱ ጦቢትንም ወረሰ፤

፲፬፤ ወሰምዐ ጦብያ ሙስናሃ ለነነዌ ዘእንበለ ይሙት በከመ ነገሮ አቡሁ፤

አባቱ እንደተናገረው ሳይሞት ጦብያ የነነዌን ጥፋት ሰማ፤

ወሰምዑ ናቡከደነፆር ወአሕሻዊሮስ ሙስናሃ ለነነዌ ወተፈሥሑ፤

ናቡከደነፆርና አሕሻዊሮስ የነነዌን ጥፋት ሰምተው ደስ አላቸው፤ እሊህማ አጥፊዎች አይደሉም ምነው ሰሙ አለ ቢሉ ሠራዊቶቻቸውን ሰጸው አስወግተዋቸው ነበርና ከሠራዊቶቻቸው የነነዌን ጥፋት ሰሙ አለ፤

፲፭፤ ወሞተ ጦብያ በ፻ወ፳ወ፯ቱ ዓመት በባጥና ዘሜዶን፣

ጦብያ የሜዶን አውራጃ በምትሆን በባጥና በመቶ ኻያ ሰባት ዓመት ሞተ፤

ወቀበርዎ በክብር፣

አክብረው ቀበሩት፤

ተፈጸመ መጽሐፈ ጦቢት በረከተ አምላኩ ትኩን ምስሌነ፤ ወስብሐት ለእግዚአብሔር እስከ ለዓለመ ዓለም አሜን::

የጦቢት ጉባዔ ፬ ነው::

# መጽሐፈ ዮዲት 

## መቅድም

ዮዲት ማለት የማናዊት ማለት ነው፤ ዮድ ማለት የማን እግዚአብሔር ማለት እንደሆነ፤ አንድም ኀይልት ዕንዕት ማለት ነው አንድም ተአማኒት ማለት ነው፤ ይህስ እንደ ምነው ቢሉ ፍሕዮስ ቂሮስ ምኑፍዮስ፤ ቂሮስ የሚባል የፋርስ ንጉሥ ነበረ፤ ገናና ነህ ስትሉ ናቡከደነፆር በሉኝ አለ ሆሎፎርኒስ የሚባል፤ ቢትወደድ ነበረው፤ አሥር እልፍ ከሁለት ሺሕ እግረኛ፣ ዐሥር እልፍ ከሁለት ሺሕ ፈረሰኛ፣ ዐሥር እልፍ ከሁለት ሺሕ ቀስተኛ ይዘህ ሂደሕ እየዞርህ አሳምን አለው፤ እየዞረ ሲያሳምን አሞን ደረሰ፣ የዓሞንን አለቃ አክዮርን አሳመነው፤ ያን ጊዜ እሥራኤል ቤጤልዋ የምትባል አምባ ቈርቁረው ተቀምጠው ነበር፤ አሻግሮ አይቶ ሁሉ ሲሰግድልኝ እነዚህ የማይሰግዱልኝ ምንድር ናቸው አለ፤ የዓሞን አለቃ አክዮር ጌታዬ የነዚህንስ ነገር ስማኝ፣ ልንገርህ አለ፤ ጥንቱን አባታቸውን ፃእ እምሀገርከ ወተፈለጥ እምአዝማዲከ ብሎ ከከላውዴዎን ወደካራን፣ ከካራን ወደ ከነዓን አወጣው:: ኋላ በምክንያተ ረሀብ ወደ ግብፅ ወረዱ በግብፅ ሁለት መቶ ዐሥራ አምስት ዘመን ኖሩ፤ ግብፃውያን አገዛዝ አጸኑባቸው፣ ግብፃውያንን ባሥር መቅሠፍት ባሥራ አንደኛ ስጥመት አጥፍቶ ከግብፅ አወጣቸው፣ በምድረ በዳ አርባ ዘመን መና ከደመና አውርዶ ውሀ ከደንጊያ አፍልቆ መገባቸው፣ ኋላም ከነዓንን አወረሳቸው፣ ኃጢአት ሠሩ፤ ጣኦት አመለኩ፤ የፋርስ የባቢሎን ሰዎች ማርከው ወሰዷቸው፤ ሰባ ዘመን ተገዙ፣ አሁን ከባቢሎን አውጥቶ ከዚህ አስቀምጧቸዋል፤ አሁንም ጌታዬ ፈጣሪያቸውን በድለው እንደሆነ ሁለት ሰዎች ብትሰድ ድል ይነሷቸዋል፣ ፈጣሪያቸውን አልበደሉ እንደሆነ አንተም ብትሄድ ድል አትነሳቸውም አለው፤ ሆሎፎርኒስም አንተኑ ገባኢሁ ለኤፍሬም፣ የኤፍሬም ወታደሩ ጠንቋዩ አንተ ነህን፣ የነዚያን ጥፋት ሳላሳይ አንተን አልገድልህም ብሎ የግርንግሪት አሥራችሁ በቆላተ ቤጤልዋ ጣሉት፤ አላቸው፤ የግርንግሪት አሥረው ወስደው በቆላተ ቤጤልዋ ጣሉት፤ እስራኤልም ጠላት የመጣብን መስሏቸው

www.ethiopianorthodox.org

ወአመርግሐ መርግሐ ይላል፣ መርጉን ይሰዱ ጀመረ፤ እኔ አክዮር ነኝ አላቸው፤ ካምባው ወርደው ፈትተው ይዘውት ገቡ፤ ገብሩ አላቸው፤ ቀን ስጠን አሉት፤ አምስት ቀን ሰጣቸው አልደፈ ርም ባይ ነውና፤ ወሰምዐት በኪያሆን መዋዕል ዮዲት ወለተ ሚራሪ፤ በዚያ ወራት ዮዲት ወለተ ሜራሪ ይህንን ነገር ሰማች፤ ይህች ዮዲት ባሏ ምናሴ ይባላል፤ ባሏ ከሞተ ጀምሮ ወገብረት ዐሪሰ እንዲል፣ ዳስ፣ ጐጆ ጉርጆ፣ ምግላል ቦታ፣ ጸመ በአት አበጅታ ትኖር ነበር፣ ምሳ ቀምሳ አታውቅም ነበረ፣ ቅዳሜ ቅዳሜ የሠርቀ ወርኀ ዋዜማ የሠርቀ ወርኀ ዕለት በበዓለ ሠዊት፣ በበዓለ መጸለት፣ በበዓለ ፋሲካ ነው እንጂ፤ ምሳ ቀምሳ አታውቅም ነበረ፤ እስከ አምስት ቀን ድረስ ፈጣሪያቸው ቢሰማቸው ሊሰማቸው፤ ባይሰማቸው ሊክዱት አይደለም ብላ ቀኖና ገብታ ነገር አግኝታ ተከላ ተቀብታ ስንቋን ለገረዷ አሸክማ ከሆሎፎርኒስ ከተማ የምሄድ ነኝና በሩን ክፈቱልኝ አለቻቸው፤ እነዚያም ሑሪ በሰላም ወእግዚአብሔር የሃሉ ምስሌኪ፣ እግዚአብሔር ካንቺ ጋራ ይኑር ብለው መርቀው ሰደዷት፤ ከዚህ በኋላ ደስ የሚያሰኝ ልብስ ለብሳ ጫማዋን አድርጋ ሄደች፤ ከዚያ ስትደርስ ዘበኞች ይህችስ ለንጉሥ ትገባለች ብለው ይዘዋት ገቡ፣ ሆሎፎርኒስ ለምን መጣሽ አላት፤ እሷም አንድ ነገር ልነግርህ መጣሁ አለችው እስራኤል በአሪት ይህን ብሉ ይህን አትብሉ ያላቸውን ተላልፈው ፈረሱን በቅሎውን ሊበሉ ጥቂት ቀርቷቸዋል፣ ፈጥኜ አጠፋቸዋለሁ አትበል፤ ፈጣሪያቸው ለአምላክነቱ ቀናዒ ነው፤ ያጠፋልሃል አለችው፣ ልድረስብሽ አላት፣ የነዚህን ጥፋት ሳላይ አይሆንም አለችው፤ ይልቁንስ ሌሊት እየወጣሁ የምጸልይ ነኝና ባልደረባ ስጠኝ አለችው፤ ባግዋ የሚባል ባልደረባ ሰጣት፤ እየወጣች ስትጸልይ ሰንበተች፣ ባራተኛው ቀን ምሳ አደረገ፣ እሷም ከያዘችው ከስንቋ ስትበላ ስትጠጣ ዋለች፣ እሱም እሷን እሷን እያየ ብዙ መጠጥ ጠጣ፤ እንቅልፍ መጥቶበት ተኛ ባግዋ ፈቃድ የተነሣበት መስሎት ሰውን አስወጥቶ ድንኳኑን ቆልፎ ሄደ፤ እሷም ተነሥታ



ትጸልይ ጀመረ፤ ጌታዬ በኃያላኑ በወንዶች አድረህ ሥራህን ብትሠራ አትደነቅም፣ በኔ በሴቲቱ በደካማዪቱ አድረህ ሥራህን ብትሠራ ትደነቃለህ እንጂ ብላ ጸሎትዋን ከፈጸመች በኋላ ከወደቀችበት ተነሣች፤ ከራስጌው መከድ ሰይፍ ነበረ፣ አንስታ አንገቱን አለችው፣ ሴት ደካማናትና ሳይቈረጥ ቀረ፣ ደገመችው ተቈረጠ፣ ይህ ጣዖታዊ ብላ ከዙፋኑ፤ ገልብጣ ከመሬት ጣለችው ወአዕረፈት ንስቲተ ጥቂት አርፋ ገረዷን ጠርታ ቸብቸቦውን በስንቋ አቅማዳ ከትታ፣ ገረዷን አሸክማ ተነሥታ ሄደች በሩን ከፍተውላት ገባች፣ ጠላታችሁን ገድዬላችሁ መጣሁ አለቻቸው፤ ሐሰትሽ ነው አሏት፤ አክዮር ያውቃልና መጥቶ ይየው አለች፣ አክዮር አይቶ እሱ ነው አለ፤ እስራኤልያን ጊዜ ሄደን እንውጋቸው አሉ፤ እሷ ግን አሁንስ ያለ መስሏቸው ጸንተው ይዋጓኋል፣ ሲነጋ አለቃ ሹማችሁ ቸብቸቦውን በተራዳ ላይ አድርጋችሁ ትዋጋላችሁ አለቻቸው፤ እነዚያም እሷ እንደመከረቻቸው አለቃ ሹመው ቸብቸቦውን በተራዳ አድርገው፤ ይዋጓቸው ጀመረ፣ እሉ፤ ዕብራውያን ተኃየሉ ወተታብዑ ብነ፣ ባግዋን እኒህ ዕብራውያን ጸንተው ይዋጉ ጀመረ፣ አንቅሆ ለእግዚእነ ባግዋን ጌታችንን ቀስቅስልን አሉት፤ ወለየየ ይላል ድንኳኑን ፈትቶ ቢገባ ወድቆ፤ አገኘው፤ ወጥቶ ዛቲ ዕብራዊት ገብረት ኃሣረ ላዕለ ቤተ ናቡከደነፆር አላቸው፤ ሸሹ እያሳደዱ ገድለዋችዋል፤ ሦስት ወር ተድላ ደስታ አድርገዋል እሷንም ዘንባባ ይዘው አመስግነዋታል፣ መዋዒት ነሽ ሲሉ የሟች ገንዘብ ለገዳይ ይገባል ብለው የሱን ገንዘብ ለሷ ሰጥተዋታል፤ እሷም በምትሞትበት ጊዜ የባሏን ገንዘብ ለባሏ ዘመዶች፤ የሷን ገንዘብ ለሷ ዘመዶች ሰጥታ ገረዷን ነፃ አውጥታ ሙታለች፤ ይህ አርዕስት ነው ነገሩን አመ ፲ቱ ወ፪ቱ ብሎ ያመጧል።

## ምዕራፍ ፩

፩፤ አመ ዐሠርቱ ወክልኤቱ ዓመተ መንግሥቱ ለናቡከደነፆር ዘነግሠ ለፋርስ በነነዌ ሀገር ዓባይ፣

ደግ ሀገር የምትሆን ነነዌን ከተማ አድርጎ ለፋርስ የነገሠ ናቡከደነፆር በነገሠ በዐሥራ ሁለት ዘመን፤

www.ethiopianorthodox.org

በመዋዕለ አርፋክስድ ዘነግሠ ለሜዶን በባጥና፤

ባጥናን ከተማ አድርጎ ለሜዶን በነገሠ በአርፋክስድ ዘመን፤

፪፡ ወነደቃ ለባጥና ዓውደ ዓረፍታ በዕብነ ውቅሮ፤

ባጥናን ዙሪያዋን በለዘበ ድንጊያ ቀጠራት፤

ጽፍሐ መሠረቱ ሠላሳ በዕመት ዘመንገለ ገጸማ ለሀገር፤

በከበሮ ቤት በኩል በሩ ከማዕዘን እስከ ማዕዘን ያለው ሠላሳ ክንድ ነው፤ አንድም ስፍሐ መሠረቱ ሲል ነው፤

ወዘመንገለ ገጸ ሀገር ስሳ በዕመት ጽፍሐ መሠረቱ፤

ያደባባዩ መውጫ በሩ ሰላሳ ክንድ ነው፤

ወገብረ ቆመ ዓረፍቱ ሰብዓ በእመት፤

ወደላይ ቁመቱ ሰባ ክንድ ነው፤

ወማዕዘኖ ዘኃምሳ በእመት፤

ደጀ ሰላሙ ኃምሳ ክንድ ነው፤

፫፡ ወዓቀመ ማኅፈዲሁ ኀበ አንቀጽ ዘዘ፻ በዕመት፤

አልፎ አልፎ ግምብ ሠራ፤ ለማማገቻ፤ አንድም ኃምሳ ክንድ ሠርቶ መረባ ጥሏል፤ ከዚያ በላይ ኃምሳ ክንድ ሠርቷል፤ ዘዘምዕት ማለቱ ግን ባራት ማዕዘን ነውና፤ አንድም ጉበኛ የሚያይበት ነው፤ ሁለት ክንድ ክንድቶ አንድ ቤት ይሠራል፤ መቶ ክንድ አልፎ አንድ ቤት ሠርቷል፤ እንዲህ እያደረገ በአምባው ዙሪያ ሠርቷል፤

ወመሠረቱ እማዕዘንት እስከ ማዕዘንት ፷ በዕመት፤

የበሩ ስፋት መሠረቱ ከማዕዘን እስከ ማዕዘን ድረስ ስስ ክንድ ነው፤

፬፡ ወገብረ ኆኅተ አናቅጺሃ ዘይትረኃው፤

የበሩን ደጃፍ ሳንቃ የሚከፈት የሚዘጋ አድርጎ ሠራ፤

፸ በእመት ቆሞን፤

ወደላይ ቁመታቸው ሰባ ክንድ ነው፤

ወርኅቦን ፵ በእመት፤

ወርዳቸው ሠላሳ ክንድ ነው፤

ኀበ ይበውኡ ኃያላኒሁ ወጽኑዓኒሁ ወሠራዊተ አጋርያኒሁ፤

ኃያላኑ ዓርበኞች የዓርበኞቹ ሠራዊት የሚገቡበት በሩን የሚከፈት አድርጎ ሠራው፤

፭፡ ወጸብዖ ናቡከደነጾር በእማንቱ መዋዕል ለአርፋክስድ ንጉሥ ዓቢይ ውስተ ገጸም ዓቢይ፤

በዚያ ወራት ናቡከደነጾር ገናና የሚሆን አርፋክስድን በሰፊ ምድረ በዳ ተዋጋው፤ እንዲህ እንዲህ የሚያደርግ አርፋክስ



ድን እንዲህ ባደረገበት ወራት ልውጋ ብሎ አሰበ፤ ይህ ፍሕዮስ፤ ቂሮስ ምንፍዮስ ነው፤ ገናና ንጉሥ ነኝ ሲል ናቡከደ ነፆር በሉኝ ብሏል፤

ወውእቱ ገጸም ውስተ ደወለ ራግው፤

ይኸውም ምድረ በዳ በራግው አውራጃ ያለ ነው፤

፮፡ ወተቀበልዎ ኵሉ እለ ይነብሩ ውስተ አድባር፤

በደጋ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ተቀበሉት፤

ወኵሎሙ ዘውስተ አድባረ ኢዮፍራ ጤዎን፤

በኢዮፍራጤዎን ደጋ የሚኖሩ ሁሉ ተቀበሉት፤

ወጤግራዎን ወሄድስጦጳን፤

በጤግራዎን በሄድስጦጳን የሚ ኖሩ ሁሉ ተቀበሉት፤

ወአሕቃለተ አርዮክ ንጉሠ ኤሴሜዮክ፤

ባሕረ ዔው ማለት ነው፤ ባሕረ ዔውን የሚገዛ የአርዮክ አውራጃ ሁሉ ተቀበሉት፤

ወተጋብኡ አሕዛብ ብዙኃን ጥቀ ከመ ይትቃተልዎሙ ለደቂቀ ካሌድ፤

የካሌድን ልጆች ይዋጓቸው ዘንድ እጅግ ብዙ የሆኑ አሕዛብ ተሰበሰቡ፤

፯፡ ወለአከ ናቡከደነጾር ንጉሠ ፋርስ ለኵሉ እለ ይነብሩ ደወለ ፋርስ፤

የፋርስ ንጉሥ ናቡከደነጾር በፋርስ አውራጃ ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ላከ፤

ወለኵሉ እለ ይነብሩ መንገለ ዓረቢሆሙ ለእለ ይነብሩ ውስተ ቄልቅያ፤

በቄልቅያ በሚኖሩ ሰዎች ግራ ላሉ ሁሉ ላከ፤

ወደማስቆ ወሊባኖስ፤

በደማስቆ በደጋ በሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ላከ፤

ወለኵሎሙ እለ ይነብሩ መንገለ ገጸ ጸራልያ፤

በጸራልያ አንጻር ላሉ ሰዎች ሁሉ ላከ፤

፰፡ ወለአሕዛብ እለ ይነብሩ ውስተ ቀርሜሎስ ወገለዓድ፤

በገለዓድ በቀርሜሎስ ለሚኖሩ አሕዛብ ሁሉ ላከ፤

ወላዕለ ገሊላ፤

በገሊላ ለሚኖሩ ሁሉ ላከ፤

ወዘዓቢይ ገጸም አስጸሬባም፤

ሰፊ በሚሆን በአስጸሬባም ገጸም ለሚኖሩ ላከ፤

፱፡ ወለኵሉ እለ ይነብሩ ሰማርያ፤

በሰማርያ ለሚኖሩ ሁሉ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእለ ውስተ አህጉሪሃ፣

በአውራጃዋ ለሚኖሩ ሁሉ፡

ወእለ ውስተ ማዕዶተ ዮርዳኖስ፣

በዮርዳኖስ ማዶ ለሚኖሩ፡

እስከ ኢየሩሳሌም፣

ኢየሩሳሌም ድረስ ላከ፡

ወቢሳጤኒ፣

በቢሳጤኒ ላሉ፣

ወበአክሉስ

በአክሉስ ላሉ ሁሉ ላከ፤

ወቃዴስ ወፈለገ ግብፅ፣

በቃዴስ በግብፅ ወንዝ ላሉ ሁሉ ላከ፤

ወጥፍናስ ወራሚስ፣

በጥፍናስ በራሚስ ላሉ ሁሉ ላከ፤

ወኵሉ ምድረ ጌሤም፣

በጌሤም ላሉ ሁሉ ላከ፤

፲፡ እስከ ይበጽሕ መልዕልተ ጣኔዎስ፣

እስከ ጣኔዎስ በላይ ድረስ፤

ወሜንፌዎስ፣

እስከ ሜንፌዎስ ድረስ፤

ወለኵሉ እለ ውስተ ግብፅ፣

በግብፅ ለሚኖሩ ሁሉ

እስከ ይበጽሕ ደወለ ኢትዮጵያ፣

እስከ ኢትዮጵያ አውራጃ ድረስ ላከ፤

፲፩፡ ወዐበዩ ኵሉ እለ ይነብሩ ውስተ ኵሉ ምድር ትእዛዞ ናቡከደነፆር ንጉሠ ፋርስ፣

በዚህ ዓለም የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ የፋርስ ንጉሥ የናቡከደነፆርን ትእዛዝ መስማት እምቢ አሉ፤

ወኢሖሩ ምስሌሁ ጸብዐ፡

ከሱ ጋራ ወደሰልፍ አልሄዱም፤

እስመ ኢፈርህዎ፣

አልፈሩትምና፤

ወኮነ ቅድሜሆሙ ከመ አሐዱ ብእሲ፣

በፊታቸው አንድ ሰው እንዲናቅ ተናቀ፤

ወገብኡ ሐዋርያቲሁ ዕራቃኒሆሙ በሐሣር እምቅድመ ገጾሙ፣

መልእክተኞቹ ሰው ሳይይዙ አፍረው ተመለሱ፤

፲፪፡ ወተምዐ ናቡከደነፆር ላዕለ ኵላ ይእቲ ምድር ጥቀ፣

ናቡከደነፆር በሀገሩ ሁሉ እጅግ ተቆጣ፤

ወመሐለ በመንበረ መንግሥቱ፣

መንግሥቴን ይንሣኝ ብሎ ማለ፤ አንድም መከዳውን መትቶ ማለ፤

ከመ ይትበቀል ኵሎ ደወለ ቂልቅያ፣

የቂልቅያን አውራጃ ሁሉ ተበቅሎ ያጠፋ ዘንድ፤



ወዘደማስቄኔስ፣

የደማስቆስን አውራጃ፤

ወዘሶርያ ከመ ይቅትሎሙ በሰይፍ፣

በሰይፍ ያጠፋቸው ዘንድ፤

ወለኵሉ እለ ይነብሩ ውስተ ምድረ ሞዓብ፣

በሞዓብ ያሉትን ሁሉ ያጠፋ ዘንድ፤

ወለደቂቀ አሞን፣

የአሞንን ልጆች ያጠፋ ዘንድ፤

ወለኵሎሙ ይሁዳ፣

በይሁዳ የሚኖሩትን ሁሉ ያጠፋ ዘንድ፤

ወለኵሉ እለ ውስተ ግብፅ፣

በግብፅ ያሉትን ሁሉ ያጠፋ ዘንድ፤

እስከ ይበጽሕ ደወለ ክልኤቱ ብሔር፤

እስከ ሁለቱ ሀገሮች አውራጃ ድረስ ያጠፋል ያልታወቁ ናቸው፤ አንድም ሞዓብ፣ አሞን ናቸው፤

፲፫፡ ወፀብዖ ምስለ ኃይሉ ለአርፋስክድ ንጉሥ አመ ፲ወ፯ዓመት፤

በነገሠ በዐሥራ ሰባተኛ ዘመን አርፋስክድን ከሠራዊቱ ጋራ ወጋው፤

ወሞአ፣

ድል ነሣው፤

ወአእተወ ኵሎ ኃይሎ፣

ሠራዊቱን፤ አንድም ገንዘቡን ወደሀገሩ አገባው፤

ወኵሎ አፍራሲሁ ወኵሎ ሠረገላቲሁ፣

ፈረሱን፣ ሠረገላውን ወደሀገሩ አገባው፤

፲፬፡ ወአስተጋብአ አህጉሪሁ፣

ሀገሩን ሁሉ እጅ አደረገ፤ አንድም ነሥተ፣ አጠፋ፤

ወሖረ እስከ ባጥና፣

እስከ ባጥና ድረስ ሄደ፤

ወነሥአ ማኅፈዲሆሙ፣

ግምባቸውን እጅ አደረገ፤

እስከ በርበረ ሀገራ ወነሥታ፣

ሀገሪቱን እስኪበዘብዛት እስኪ ያጠፋት ድረስ፤

፲፭፡ ወአኃዞ ለአርፋስክድ በደወለ ራግው ወረገዞ በኲናት፣

በራግው አውራጃ አርፋስክድን ይዞ በጦር ወጋው፤

ወሠረዎ ለዝሉፉ፣

ለዘለዓለሙ አጠፋው፤

፲፮፡ ወአተዉ ውእቱ ወእለ ምስሌሁ ኵሉ ብዙኃን ዕደው መስተቃትላን፣

እሱ፣ ከሱ ጋራ ያሉ አርበኞች ወደሀገራቸው ተመለሱ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወነበረ ሀየ ውእቱ ፲ተ ወ፰ ዕለተ እንዘ ይመክር፤

መቶ ሃያ ቀን እሱ ከዚያ ሲመክር ተቀመጠ፤

ወይሔሊ፤

ምክሩን ሲያወጣ ሲያወርድ ተቀመጠ።

## ምዕራፍ ፪

፩፤ ወአመ ፲ቱ ወ፰ቱ ዓመት፤

በዐሥራ ስምንተኛው ዘመን፤

በሰብዑ ለጽልመት፤

ጨረቃ ሠርቅ ባደረገች፣ ጨለ ማውን ባጣች ሕፀፅ ባደረገች ብርሃኗን ባጣች በሰባተኛው ቀን፤

ቀዳማይ ወርኅ ኮነ ነገር በቤተ ናቡከደነፆር ንጉሠ ፋርስ፤

በመጀመሪያ ወር በሚያዝያ በናቡከደነፆር ቤት ነገር ተነሣ፤

ከመ ይትበቀል ለኵሉ ምድር በከመ ይቤ፤

እሱ እንደተናገረ ዓለሙን ሁሉ ተበቅሎ ያጠፋ ዘንድ፤

፪፤ ወጸውአሙ ለኵሎሙ መገብቱ ወመላእክቲሁ፤

ሹማምንቱን፣ አለቆቹን ጠራ ቸው፤

ወተናገረ ምስሌሆሙ ምሥጢረ ምክሩ፤

መቶ ሐያ ቀን የመከረውን ምሥጢር ከነሱ ጋራ ተጫዋ ወተ፤

ወነበበ ኵሎ እኪተ ላዕለ ምድር፤

በዚህ ዓለም አደርገዋለሁ ያለውን ክፋውን ሁሉ ተናገረ፤

፫፤ ወእሙንቱ አሕለቁ ከመ ይሥ ርውዎ ለኵሉ ዘሥጋ ላዕለ እለ ኢተደለዉ በቃለ አፉሁ፤

እነዚህም በሱ አዋጅ ያልተዘ ጋጁ ሥጋዊን ደማዊን ሁሉ ያጠፋ ዘንድ ምክር ቆረጡ፤

፬፤ ወእምዝ ሶበ አኅለቀ ምክሮ፤

ምክሩን ከፈጸመ በኋላ፤

ጸውዖ ናቡከደነፆር ንጉሠ ፋርስ ለሆሎፎርኒስ መልአከ ኃይሉ ዘእምታሕቴሁ፤

ናቡከደነፆር ከሱ በታች ለሠ ራዊቱ ቢትወደድ አድርጎ የሾመውን ሆሎፎርኒስን ጠራው፤

፭፤ ወይቤሎ ከመዝ ይቤ ንጉሥ ዓቢይ እግዚአ ኵሉ ብሔር፤

የሀገሩ ሁሉ ጌታ የሚሆን ገናና ንጉሥ እንዲህ አለ አለው፤

ናሁ ትወፅእ እምቅድመ ገጽየ፤

እነሆ ከፊቴ ወጥተህ ትሄዳለህ፤



ወትነሥእ ምስሌከ ዕደወ ምዕመናነ በኃይሎሙ፤

በኃይላቸው የታመኑ ጉልማ ሶችን ካንተ ጋራ ይዘህ ሂድ፤

አጋራውያነ ፲ተ፼ ወ፳፻ተ፤

ዓሥር እልፍ ከሁለት ሽሕ አርበኛ፤

ወመስተፅዕናነ አፍራስ ምስለ አፍራ ሲሆሙ ፲ተ፼ ወ፳፻ተ

ዐሥር እልፍ ከሁለት ሽሕ ፈረሰኛ፤

ወሰብአ ሐፅ ፲ተ፼ ወ፳፻ተ

ዐሥር እልፍ ከሁለት ሽሕ ቀስተኛ እነዚህን ይዘህ፤

፮፤ ወትወፅእ እምኔየ ውስተ ኵላ ምድር እንተ መንገለ ዓረብ፤

ከኔ ተለይተህ በምዕራብ በኵል ወደ አለ አገር ትሄዳለህ፤

እስመ ዐበዩ ተአዝዞ ለቃለ አፉየ፤

እኔ በቃሌ ያዘዝሁትን ትእዛዝ እምቢ ብለዋልና፤

፯፤ ወትሰብክ ሎሙ ያስተዳልዉ ሊተ ብሔረ ወማየ፤

ወህውን ከበው ሀገሩን ይይዙ ዘንድ አዋጅ ንገርላቸው፤

እስመ እመጽእ በመዓትየ ላዕሌሆሙ፤

በመዓት በቁጣ እመጣባቸዋ ለሁና፤

ወእከድን ገጸ ለምድር በእግረ ኃይልየ፤

በሠራዊቶቼ ብዛት ምድርን እሸፍናታለሁ፤

ወእሬስዮሙ ሕብልየ ወበርበረ፤

እንዲበዘብዟቸው አደርጋለሁ፤

፰፤ ወአብድንቲሆሙኒ ይመልእ ውስተ ቈላቲሆሙ፤

ሬሳቸው በቈላው ሁሉ ይሞላል፤

ወውስተ አፍላግ ይመልዕ አብድን ቲሆሙ፤

ሬሳቸው በወንዙ ሁሉ ይሞላል፤

ወበተከዚኒ፤

በፈሳሹ ወህም ሬሳቸው ይመላል፤

፱፤ ወእዘርዎሙ ለፄዋሆሙ እስከ አጽናፈ ምድር፤

ምርኳቸውን ጽንፍ እስከ ጽንፍ እበትነዋለሁ፤

፲፤ ወአንተሰ ቅድም ወንሣእ ኵሎ ደወሎሙ ሊተ፤

አስቀድመህ አንተ አውራጃ ቸውን ያዝ፤

ወያገብኡ ርእሶሙ ኀቤከ፤

ወባት ይገቡልሃል፤ (እጃቸውን ይሰጡሃል)

ወዕቀቦሙ ሊተ እስከ ዕለተ እትቤቀሎሙ፤

እስከ ማጥፋበት ቀን ጠብቃ ቸው፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፩፡ እስመ ኢትምሕከሙ ዓይንከ ለእለ አጽረፉ፣

ግብር ለነሱ ለእነዚህ ዓይንህ አታዝንላቸውምና፡

ከመ ትቅትሎሙ ወትበርብሮሙ ውስተ ኵሉ ምድርከ፣

በሀገርህ ሁሉ ታጠፋቸው ትበዘብዛቸው ዘንድ፡

፲፪፡ እስመ ሕያው አነ ወጽኑዕ መንግሥትየ፣

ሕያው ነኝና መንግሥቴም ጽኑ ነውና፡

ከመ እግበር ዘንተ በእዴየ በከመ ነበብኩ፣

በቃሌ እንደተናገርኩ ይህንን አደርግ ዘንድ፡

፲፫፡ ወአንተኒ አልቦ ዘተሐድግ ወኢአሐተ እምቃለ እግዚእከ፣

አንተም እኔ ከተናገርኩት ነገር አንዲት የምትተወው አይኑር፡

አላ ገቢረ ግበር በከመ አዘዝኩከ፣

እንደአዘዝኩህ አድርግ እንጂ፡

ወኢታጕንዲ ገቢሮቶ፣

ፈጥነህ አድርግ እንጂ፡

፲፬፡ ወወፅአ ሆሎፎርኒስ እምቅድመ እግዚኡ፣

ሆሎፎርኒስ ከጌታው አስቀድሞ ወጣ፡ አንድም ከፊት ወጣ፣

ወጸውአሙ ለኵሎሙ ኃያላን ወለኵሎሙ መላእክት ወሠራዊት፣

ኃያላኑን አለቆችን ሁሉን ጠራ፡

ወሠራዊት፣

ሠራዊቱን ሁሉ ጠራ፡

ወሊቃናተ ኃይሉ፡

የሠራዊቱን አለቆች ጠራ፡

ወዘአሶር፣

ኃያላኑን ጠራ፡

፲፭፡ ወኈለቆሙ ለኅሩያን ዕደው መስተቃትላን፣

የተመረጡ አርበኞችን ቈጠራቸው፡

በከመ ነበበ እግዚኡ፣

ጌታው እንደተናገረ፡

አጋራውያን ፲ቱ፻፻ ወ፳፻ት፡

እግረኞች ዐሥር እልፍ ከሁለት ሺሕ ናቸው፡

ወሰብአ አፍራስ ፲ቱ፻፻ ወ፳፻ት፣

ዐሥር እልፍ ከሁለት ሺሕ ፈረሰኛ፡

ወሰብአ ሐጽ ፲ቱ፻፻ ወ፳፻ት፣

ዐሥር እልፍ ከሁለት ሺሕ ቀስተኛ ሆኑ፡

፲፮፡ ወአዘዞሙ ለኵሎሙ ከመ ይትቃትሉ ወከመ ይፃብኡ፡

ሁሉንም ወጥተው ይዋጉ ዘንድ አዘዛቸው፡



፲፯፡ ወነሥኡ አግማለ ወአዕዱገ ወአብቅለ ለስንቆሙ ብዙኀ ጥቀ፣

ለስንቅ መጫኛ ሊሆኑ እጅግ ብዙ የሆኑ ግመሎችን፣ በቅሎ ዎችን፣ አህዮችን ያዙ፡

ወአባግዓ ወአልሕምተ ወአጣሊ ለሲሳዮሙ ዘአልቦ ኈልቈ፡

ምግብ ሊሆናቸው ቁጥር ሥፍር የሌላቸው ላሙን፣ በጉን፣ ፍየሉን ተቀበሉ፡

፲፰፡ ወአስንቀ ለኵሉ ሰብኡ፣

ለሰዎቹ ሁሉ ስንቅ ሰጠ፡

ወለብዙኃን ወርቀ ወብሩረ እምቤተ ንጉሥ ብዙኃ ጥቀ፣

ከንጉሡ ቤት ለብዙ ሰዎች ብዙ ወርቅ ብር ሰጣቸው፡

፲፱፡ ወወፅአ ውእቱ ወኵሉ ኃይሉ፣

እሱ ሠራዊቱ ወጣ፡

ወጸብሀ፣ ቅድመ እምንጉሥ ናቡከደ ነፆር፣

ከንጉሡ አስቀድሞ ወጥቶ ተዋጋ፡

ወከመ ይክድን ኵሎ ገጸ ምድር መንገለ ዓረብ በሠረገላ ወበአፍራስ፣

በሠረገላ በፈረስ፣ በምዕራብ፣ በኩል፣ ምድርን ይሸፍናት ዘንድ፡

ወአጋርያን ኅሩያን፣

በአርበኞች በተመረጡት ሰዎች ምድርን ይሸፍኗት ዘንድ፡

፳፡ ወብዙኃን እለ ኅብሩ ምስሌሆሙ ከመ አንበጣ ወፅኡ ምስሌሆሙ፣

ከነዚያ ጋራ የተባበሩ ሰዎች እንደ አንበጣ በዝተው ወጡ፡

ወከመ ኆፃ ባሕር፣

እንደ ባሕር አሸዋ ብዙ ናቸው፡

ወአልቦሙ ኈልቍ እምነ ብዝኆሙ፡

ከብዛታቸው የተነሣ ቁጥር ሥፍር የላቸውም፡

፳፩፡ ወወፅኡ እምነ ነነዌ ምሕዋረ ሠሉስ ዕለት ውስተ ገጸ ገዳም ዘቤቄጤሌት፣

ከነነዌ ወጥተው በቤቄጤሌት ወዳለ ምድረ በዳ የሦስት ቀን ጐዳና ሄዱ፡

ወሖረ እምነ ቤቄጤሌት ዘገቦ ደብር ዘመንገለ ጸጋም ዘመልዕልተ ኪልቅያ፣

በተራራ አጠገብ ከቤቄጤሌት ከኪልቅያ በላይ ወዳለ ግራ ግራውን ሄደ፡

፳፪፡ ወነሥአ ኵሎ ኃይሎ አጋርያነ፣

ሠራዊቱን ሁሉ፣ አርበኞችን ሁሉ ይዞ፡

ወሰብአ አፍራስ፣

ፈረሰኞችን፡

ወሠረገላቲሁ፣

ሠረገላውን ይዞ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወሖረ እምህየ መንገለ አድዋሊሆሙ፣

ከዚያ ተነሥቶ ወደ አውራ ጃቸው ሄደ፤

፳፫፤ ወቀተሎሙ ለፌድ ወለሉድ፣

ፌድን፣ ሉድን አጠፋቸው፤

ወፄወዎሙ ለኵሎሙ ደቂቀ ሬስስ፣

የሬስስን ልጆች ሁሉንም ማረካቸው፤

ወለደቂቀ እስማኤል እለ ውስተ ገጻም ዘመንገለ ገጸ አዜብ ዘኤሌዎን፤

የእስማኤልን ልጆች በኤሌዎን ግራ ባለ በምድረ በዳ አጠፋቸው፤

፳፬፤ ወአደወ ኤፍራጥስ፣

ኤፍራጥስን ተሻገረ፤

ወኃለፈ እመስጴጦምያ፣

ከመስጴጦምያ ተንሥቶ ሄደ፤

ወነሠተ ኵሎ አህጉሪሆሙ ዓበይተ ዘመልዕልተ አህጉረ አርባዐኔ፣

ከአርባ አኔ በላይ ያሉ ደጋጉን ሀገራቸውን አጠፋ፤ አንድም አርብዓ ይላል፣ ያልታወቁ አራት ሀገሮችን አጠፋ፤ አንድም ጢሮስ፣ ሲዶና፣ ሞዓብ፣ አሞን ናቸው፤

እስከ በጽሐ ኀበ ብሔር፣

ወደሀገሩ እስኪደርስ ድርስ

፳፭፤ ወረከበ ደወለ ቂልቅያ

የቂልቅያን አውራጃ ያዘ፤

ወቀተለ ኵሉ ዐሮ፣

ጠላቱን ሁሉ ገደለ

ወሖረ እስከ ደወለ ያፌት ዘመንገለ አዜብ ዘገጸ አረብ፣

በምዕራብ አጠገብ ባለች በአዜብ በኩል እስከ ያፌት ዕፃ ድረስ ሄደ፤

፳፮፤ ወአገቶሙ ለኵሎሙ ደቂቀ ምድያም፣

የምድያምን ልጆች ሁሉ ከበባቸው፤

ወማኅረከ እንስሳሆሙ፣

ከብታቸውን ሁሉ ማረከ፤

ወአውዐየ አብያቲሆሙ፣

ቤታቸውን አቃጠለ፤

፳፯፤ ወወረደ ውስተ ገዳም ዘደማስቆ በጊዜ ማዕረረ ሥርናይ፣

በስንዴው መከር ጊዜ ወደ ደማስቆ ምድረ በዳ ወረደ፤

ወአውዐየ ኵሎ ገራውሂሆሙ፣

አዝመራቸውን ሁሉ አቃጠለ፤

ወአባግዒሆሙሰ ወመራዕይሆሙ አዘዘ የሐብልዩ፣

በጎቻቸውንና መንጋቸውን ሁሉ ይበዘብዙ ዘንድ አዘዘ፤

ወነሠተ አህጉሪሆሙ፣

አገራቸውን አጠፋ፤



ወደቂቆሙኒ ነሥአ፣

ልጆቻቸውን ማርኮ ወሰደ፤

ወቀተለ ኵሎ ወራዙቶሙ በአፈ ሐፂን፣

ጐልማሶችን በጦር አጠፋቸው፤

ወወድቀት ፍርሃተ ዚአሁ፣

የሱ መፈራት በሁሉ ደረሰች፤

፳፰፤ ወድንጋፄ ላዕለ እለ ይነብሩ ውስተ ጸራልያ፣

በጸራልያ በሚኖሩ ሰዎች ድንጋፄ መጣባቸው፤

ወእለ ውስተ ሲዶና ወጢሮስ፣

በጢሮስ በሲዶና የሚኖሩ፤

ወኵሎሙ እለ ይነብሩ ውስተ ሴይር ወአቂና፣

በሴይር በአቂና የሚኖሩ፤

ወኵሎሙ እለ ይነብሩ ውስተ ደማናሆን፣

በደማናሆን የሚኖሩ ሁሉ፤

ወእለ ውስተ አዛጦን ወአስቀሎና፣

በአዛጦን በአስቀሎና የሚኖሩ፤

ፈርሁ ጥቀ እምኔሁ፣

ከሱ የተነሳ እጅግ ፈሩ።

## ምዕራፍ ፫

፩፤ ወፈነዉ መልእክተ በቃለ ሰላም፣

በፍቅር አነጋገር መልእክተኞችን ሰደዱ፤

፪፤ እንዘ ይብሉ ናሁአ ንሕነ አግብርቲሁ ለናቡከደነፆር ንጉሥ ዓቢይ፣

እነሆ እኛ የገናና ንጉሥ የናቡከደነፆር ባሮች ነን ብለው፤

ሀለውነ ቅድሜከ፣

በፊትህ አለን፤

ወረስየነ በከመ ፈቀድከ በቅድመ ገጽከ፣

በፊትህ እንደወደድህ አድርገን፤

፫፤ ወናሁ አህጉሪነ ወኵሉ በሐውርቲነ፤

አገራችን መንደራችን ሁሉ፤

ወኵሉ ገራውሂነ፤

እርሻችን ሁሉ፤

ወመራዕይነ፤

ከብታችን፤

ወኵሉ አዕፃዳተ ወፍርነ፣

የመሰምሪያችን ቦታ ሁሉ፤

ወአባግዒነ፣

በጎቻችን፤

ለከ ቅድመ ገጽከ፣

በፊትህ ናቸው፤

ወግበር ዘፈቀድከ፣

የወደድከውን አድርግ፤

፬፤ ወናሁ አህጉሪነ ዓበይት፣

ደጋግም የሆኑ አገሮቻችን፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእለ ይነብሩ ውስቴቶን፣

በዚያ የሚኖሩ፡

አግብርቲከ እሙንቱ፣

ባሮችህ ናቸው፡

ወነዓ ረሲ ዘከመ ፈቃድከ፣

መጥተህ እንደወደድህ አድርግ፡

፭፡ ወበጽሑ እሙንቱ ዕደው ኀበ ሆሎፎርኒስ፣

እኒህ ሰዎች ከሆሎፎርኒስ ዘንድ ደረሱ፡

ወዜነውዎ ዘንተ ነገረ፣

ይህን ነገር ነገሩት፡

፮፡ ወወረደ ውስተ በሐውርቲሆሙ ውእቱ ወኃይሉ፣

እሱ ሠራዊቱ ወደሀገራቸው ወረደ፡

ወአዕቀበ አህጉሪሆሙ ዓበይተ፡

ደጋግ የሚሆኑ አገራቸውን አስጠበቀ፡

ወነሥአ እምኔሆሙ ዕደወ ኅሩያነ እለ ያስተታልዎሙ፣

ከነዚያ የሚረዱት የተመረጡ ሰዎችን ያዘ፡ አንድም ጐዳና የሚያሳዩትን ሰዎችን ያዘ፡

፯፡ ወተቀበልዎ እሙንቱኒ ወኵሉ በሐውርቲሆሙ፣

እነዚያም ሀገሩ ሁሉ ተቀበሉት፡

በአክሊላት፣

አክሊል ደፍተው፡

ወበማኅሌት፣

ዘፈን እየዘፈኑ፡

ወበመዝሙር፣

በገና እየደረደሩ፡

ወበከበሮ፣

ከበሮውን እየመቱ ተቀበሉት፡

፰፡ ወፆደ ውስተ ደወሎሙ፣

ሀገራቸውን ተመራ፡

ወሠበረ ምስላቲሆሙ፣

ጣዖታቸውን ሰበረ፡

ወእዙዝ ውእቱ ከመ ያጥፍእ ኵሎ አማልክተ ሰብእ፣

ከዚህ አስቀድሞ በሰው አምሳል የተሠራውን ጣኦት ያጠፋ ዘንድ ታዝዞ ነበረ፡

ወያምልክዎ ለናቡከደነፆር ሎቱ ለባሕቲቱ፡

ናቡከደነፆርን ብቻ ያመልኩት ዘንድ፡

ወኵሉ አሕዛብ፣

አሕዛብ ሁሉ፡

ወኵሉ በሐውርት፣

ሀገሩ ሁሉ፡

ከመ ይበልዎ እግዚአብሔር፣

እግዚአብሔር ይሉት ዘንድ፡



፱፡ ወመጽአ ውስተ ኵሉ ገጸ ኤስድሬሎም ዘገባይያ፣

የገባይያ አውራጃ ወደሚሆን ወደኤስድሬሎም መጣ፡

ዘቅድመ ጸርያኖስ ዓቢይ ዘይሁዳ፣

የይሁዳ ዕፃ በሚሆን በጸርያኖስ አንጻር ያለ፡

፲፡ ወሖረ ማዕከለ ገዳመ ጤቦን፣

በጤቦን ምድረ በዳ መካከል ሄደ፡

ወአሕጉረ ሴቅቶን፡

በሴቅቶን አውራጃ መካከል ሄደ፡

ወነበረ ህየ አሐደ ወርኃ ያስተጋብእ ስንቀ ለአሕዛቢሁ፣

ለሠራዊቱ ስንቅ ያዘጋጅ ዘንድ አንድ ወር ከዚያ ተቀመጠ።

## ምዕራፍ ፬

### ጉባዔ

፩፡ ወሰምዑ ደቂቀ እሥራኤል ወእለ ይነብሩ ውስተ ይሁዳ፣

የእሥራኤል ልጆች በይሁዳ የሚኖሩ ሁሉ፡

ኵሎ ዘገብረ ሆሎፎርኒስ ላዕለ አሕዛብ መልአከ ኃይሉ ለናቡከደነፆር ንጉሠ ፋርስ፣

የፋርስ ንጉሥ የናቡከደነፆር ቢትወደድ ሆሎፎርኒስ በአሕዛብ ላይ ያደረገውን ሁሉ ሰሙ፡

ዘከመ አማሰነ ኵሎ ደወሎሙ፣

አውራጃቸውን ሁሉ እንዳጣፋ ሰሙ፡

ወዘከመ አጥፍአሙ፣

እንዳጠፋቸው ሰምተው፡

፪፡ ወፈርሁ ጥቀ ፈድፋደ እምቅድመ ገጹ፣

ከፊቱ የተነሣ እጅግ ፈሩ፣

ወበእንተ ኢየሩሳሌም፣

ስለ ኢየሩሳሌም፡

ወበእንተ ቤተ እግዚአብሔር አምላኮሙ፡

የፈጣሪያቸው የእግዚአብሔር ማደሪያ ስለ ምትሆን ስለ ቤተ መቅደስ ፈሩ፡

፫፡ እስመ ግብተ ሀለዉ እምኅበ ዐርጉ እምድኅረ ተዔወዉ ኵሉ ኅሩያን ሕዝብ ዘእምነገደ ይሁዳ፡

ከነገደ ይሁዳ የተወለዱ የተመረጡ ወገኖች ከተማረኩ በኋላ ከተራራው ላይ ድንገት ወጥተው ቁጭ ቁጭ ብለው ነበረና ፈሩ፡ አንድም ሆሎፎርኒስ ድንገት መጥቶባቸው ፈሩ፡

ወበእንተ ንዋየ ቅድሳት፡

ስለ ንዋየ ቅድሳቱ፡

ወምሥዋዕ፣

ስለ ምሥዋዑ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወበእንተ ቤተ መቅደስ።

ስለ ቤተ መቅደስ ፈሩ፤

እስመ እምድኅረ ተገመነ ቀደስዎ።

ከተዳደፈ በኋላ አንጽተው አክብረውታልና ፈሩ፤

፬፡ ወለአከ ውስተ ኵሉ ደወለ ሰርያ፡

ወደሰርያ አውራጃ ሁሉ ላከ፤

ወቆናስ ወቤቶሮ ወቤልሞን ወኢያሪኮ ወአስኮባን ወአሥራ ወአውሊናሴሌም።

ይህ ሁሉ የሀገር ስም ነው ወደነዚህ ሁሉ ላከ።

፭፡ ወበጽሐ ውስተ ኵሉ አርእስተ አድባሪሆሙ ልዑላን።

ከፍ ወዳለ ወዳምባቸው አጠገብ ደረሰ፤

ውነደረ ላዕለ አህጉር እለ ውስቴቶሙ።

እነዚያ ባሉበት ሀገር ሁሉ ሠፈረ፤

ወነሥኡ ሎሙ ስንቀ ለፀብእ።

ለሰልፍ የሚሆናቸውን ስንቅ ያዙ፤

እስመ ግብተ ከኖሙ ማዕረሮሙ።

መከራቸው ድንገት ደርሶላቸዋልና፤ አንድም እስመ ግብተ በጽሐሙ አመ ማዕረሮሙ ይላል፤ በመከራቸው ጊዜ ሆሎፎርኒስ ድንገት ደርሶባቸዋልና፤

፮፡ ወጸሐፈ ኢዮአቄም ካህን ዓቢይ ዘሀለወ በኪያሆን መዋዕል ውስተ ኢየሩሳሌም።

በውእቶን መዋዕል ሲል ነው፤ በዚያ ወራት በኢየሩሳሌም የነበረ ደግ ካህን ኢዮአቄም፤

ለእለ ይነብሩ ውስተ ቤጤልዋ፡

በቤጤልዋ ለሚኖሩ ጻፈ፤

ወቤጠሚስታም እንተ ቅድመ ኢያሪኮ።

በኢያሪኮ አንፃር ባለች በቤጠሚስታም ላሉ ጻፈ፤

ውስተ ገጸ ገዳም ዘገቦ ዶታይም።

በዶታይም አጠገብ ወዳለ ወደምድረ በዳው ጻፈ፤

፯፡ እንዘ ይብል አጽንዑ ፍትሐታተ አድባር።

ከተራራ ላይ ያለ ምሽጉን አጥኑ፤ አንድም ፍሰሐታተ አድባርም ይላል፤ አንድም ስፍሐታተ አድባርም ይላል፤

ኮረብታውን አጥኑ፤

እስመ እንተ ህየ ቦቱ ሙባዕ ላዕለ ይሁዳ።

በይሁዳ በኩል መግቢያ አለውና፤

ከመ ትክልእዎሙ ኃሊፈ።

ወደይሁዳ እንዳይሄዱ ትከለክሏቸው ዘንድ፤



እስመ ጸባብ ሙባዒሁ ወፍናዊሁ ዳዕሙ ምኅላፈ ክልኤቱ ዕደው ኮለንታሁ።

የሁለት ሰው መንገድ ብቻ የሚሆን በሩ ጐዳናው ጠባብ ነውና አጽኑ፤ አንድም ጠባብ የሚሆን በሩ፤ መንገዱ የሁለት ሰው መንገድ ነውና፤ ያንዱን ትታችሁ ያንዱን ናዱት፤

፰፡ ወገብሩ ደቂቀ እሥራኤል በከመ አዘዞሙ ኢዮአቄም ካህን ዓቢይ።

የእሥራኤል ልጆች ደግ ካህን ኢዮአቄም እንዳዘዛቸው አደረጉ፤

ወኵሉ ሊቃውንተ እሥራኤል እለ ይነብሩ ኢየሩሳሌም።

በኢዮሩሳሌም የሚኖሩ የእስራኤል አለቆች ሁሉ እንዳላቸው አደረጉ፤

፱፡ ወጸርሑ ኵሎሙ ደቂቀ እስራኤል ኀበ እግዚአብሔር በዓቢይ ቃል።

የእስራኤል ልጆች ቃላቸውን አሰምተው ወደ እግዚአብሔር ጮሁ፤

ወአሕመሙ ነፍሶሙ በዓቢይ ሕማም።

በጽኑ ኃዘን ልቡናቸውን አሳዘኑ፤

፲፡ ወእሙንቱኒ ወአንስቲያሆሙኒ።

ወንዶችም ሴቶችም፤

ወደቂቆሙኒ ወእንስሳሆሙኒ፡

ልጆቻቸውም ከብቶቻቸውም፤

ወኵሉ ፈላሲ።

መጻተኛ፤

ወአሳብ።

ምንደኛ፤

ወዘበሤጥ።

በወርቅ የተገዛ ባሪያ፤

ለሀዉ።

እነዚህ ሁሉ አዘኑ፤

ወለብሱ ሠቀ።

ምንጣፍ ለበሱ፤

፲፩፡ ወኵሉ ሰብአ እስራኤል።

የእሥራኤል ሰዎች፤

ወአንስቲያሆሙ።

ሚስቶቻቸው፤

ወደቂቆሙ እለ ይነብሩ ኢየሩሳሌም።

በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ልጆቻቸው ሁሉ፤

ወድቁ ውስተ ቤተ መቅደስ።

ከቤተ መቅደስ ገብተው ተንከባለሉ፤

ወደዩ ሐመደ ዲበ ርእሶሙ፤

በራሳቸው ላይ አመድ ነሰነሱ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወሰፍሑ ሠቃቲሆሙ ቅድመ እግዚአብሔር።

በእግዚአብሔር ፊት ምንጣፍ መልበሳቸውን አሳዩ፤

ወአልበሱ ምሥዋዓ ሠቀ።

ምሥዋዑን ምንጣፍ አለበሱት፤ ዛሬ እኛ በዕለተ ዓርብ ጥቁር ልብስ እንደምንለብስ፤

፲፪፤ ወጸርሑ ኀበ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ኅቡረ በሕቁ።

ወደ እስራኤል ፈጣሪ አንድ ሁነው ፈጽመው ጮሁ፤

ከመ ኢይትመሠጡ ደቂቆሙ።

ልጆቻቸው እንዳይማረኩ፤

ወከመ ኢይዔወዋ አንስቲያሆሙ፤

ሚስቶቻቸው እንዳይማረኩ፤

ወከመ ኢያጥፍኡ አህጉረ ርስቶሙ።

የርስታቸውን አውራጃ እንዳ ያጠፉ፤

ወኢያገምኑ መቅደሶሙ።

ቤተ መቅደስን እንዳያረክሱ፤

ወኢይሬስይዎ ተውኔተ ለአሕዛብ።

ለአሕዛብ መዘባበቻ እንዳያ ደርጉት፤

፲፫፤ ወርእየ እግዚአብሔር ሕማሞሙ።

እግዚአብሔር መከራቸውን አየ፤

ወሰምዐ ቃሎሙ።

ልመናቸውን ሰማ፤

ወጸመ ሕዝብ ብዙኃ መዋዕለ በኵሉ ይሁዳ ወበኢየሩሳሌም።

በይሁዳ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሕዝብ ብዙ ዘመን ጾሙ፤

በቅድመ መቅደሱ ለእግዚአብሔር ዘኵሉ ይመልክ።

ሁሉን በሚገዛ በእግዚአብሔር ማደሪያ በቤተ መቅደስ ጾሙ፤

፲፬፤ ወኢዮአቄምሰ ካህን ዓቢይ ወኵሎሙ እለ ይቀውሙ ካህናት ቅድመ እግዚአብሔር።

ደገ ካህን ኢዮአቄም ግን በእግ ዚአብሔር ፊት የሚቆሙ ካህናቱም ሁሉ፤

ወእለ ይገብሩ ግብረ እግዚአ ብሔር።

የእግዚአብሔርን ሥራ የሚሠሩ የሚያርዱ የሚያወራርዱ፤

ቀነቱ ሠቃተ ውስተ ሐቌሆሙ።

በወገባቸው ሠቅ ምንጣፍ ታጠቁ፤

ወአብኡ መሥዋዕተ ዘዘልፍ።

ሁልጊዜ የሚሠዉትን መሥዋ ዕት አቀረቡ፤

ወዘብፅአት።

የሥለቱን መሥዋዕት፤

ወዘበፈቃዶሙ ዘያበውኡ ሕዝብ።

ሕዝቡ በፈቃዳቸው የሚያቀ ርቡትን መሥዋዕት አቀረቡ፤



፲፭፤ ወወደዩ ሐመደ ውስተ አርእስቲሆሙ።

በራሳቸው ላይ አመድ ነሰነሱ፤

ወጸርሑ ኀበ እግዚአብሔር በኵሉ ኃይሎሙ።

በፍጹም ዕውቀታቸው ጮኸው ወደእግዚአብሔር ለመኑ፤

ወይቤሉ ነጽር ላዕለ ቤተ እስራኤል በሠናይ።

የእሥራኤልን ወገኖች በዓይነ ምሕረት ተመልከታቸው።

## ምዕራፍ ፭

፩፤ ወዜነውዎ ለሆሎፎርኒስ መልአከ ኃይሉ ለአሶር።

ለናቡከደነፆር ቢትወደድ ለሆሎፎርኒስ ነገሩት፤

ወይቤልዎ ተደለዉ ደቂቀ እስራኤል ለፀብእ።

የእሥራኤል ልጆች ለሰልፍ ተዘጋጁ ብለው ነገሩት፤

ወዐፀዉ ፍኖተ አድባር።

ምሽጉን ዘጉ፤

ወሐፀሩ አርእስተ አድባር ነዋኃት።

የረጅሙን ተራራ ራስ በጦር አጠሩት፤

ወገብሩ ፍናዋተ መብዕስ።

ጎዳናውን ጌፃጌፅ አደረጉት፤

፪፤ ወተምዐ መዓተ ጥቀ።

ፈጽሞ ተቈጣ፤

ወጸውዖሙ ለመላእክተ ሞዓብ።

የሞዓብን አለቆች፤

ወለመሳፍንተ አሞን።

የአሞንን መሳፍንት፤

ወለመላእክተ ጸራልያ።

የጸራልያን አለቆች ጠርቶ፤

፫፤ ወይቤሎሙ ንግሩኒ ደቂቀ ከነዓን።

እናንት የከነዓን ልጆች ንገሩኝ አላቸው፤

ምንት እሉ ሕዝብ እለ ይነብሩ ውስተ አድባር።

ከተራራው ላይ ቁጭ ቁጭ ብለው የሚያቸው እሊህ ምንድን ናቸው፤

ወምንት እልክቱ እለ ይነብሩ።

ከዚያ ላይ ተቀምጠው የሚያ ቸው እነዚያስ ምንድናቸው፤

ወበዝኑ ኃይሎሙ።

ሠራዊታቸው የበዛ፤

ወምንት አጽንኦሙ።

ያጸናቸው ምንድር ነው፤

ወመኑ ንጉሥ ዘቆመ እምኔሆሙ፤

ከሳቸው ወገንስ የነገሠላቸው ማነው?

www.ethiopianorthodox.org

አው መስፍን፤

መስፍን የሾመላቸው፡

አው መልአከሙ፤

አለቃቸውስ ማነው?

፬፡ ወእፎ ኢይመጽኡ ከመ ይትቀበሉኒ፤

ይቀበሉኝ ዘንድ እንደምን አይመጡም?

እምነ ኵሉ እለ ይነብሩ መንገለ ዓረብ፤

በምዕራብ በኩል ከሚኖሩ ሰዎች ተለይተው ለምን አልመጡም፤

፭፡ ወይቤሎ አኪዮር መስፍኖሙ ለኵሉ ደቂቀ አሞን፤

የአሞን ልጆች ሁሉ አለቃ የሚሆን አኪዮር እንዲህ አለው፤

ስማዕ እግዚእየ ቃለ እምነ አፉሁ ለገብርከ፤

ጌታዬ ከኔ ከባሪያህ የሚወጣ ቃልን ስማ፤

ወእነግረከ ጽድቀ በበይነ ዝንቱ ሕዝብ እለ ይነብሩ ውስተ አድባር፤

በተራራ ላይ ተቀምጠው ስለሚኖሩ ወገኖች የነዚህን ነገር እውነት ነገር እነግርሃለሁ፤

ወቅሩበከ ሀለዉ፤

ባጠገብህ ያሉ፤

እስመ ሐሰት ኢይወፅዕ እምአፉሁ ለገብርከ፤

ከኔ ከባሪያህ አንደበት ሐሰት አይወጣምና፤

፮፡ እሉ ሕዝብ እምነ ከላውዴዎን ወጽኡ፤

እኒህ ወገኖች ጥንቱን ከከላውዴዎን ወጡ፤

፯፡ ወነበሩ ቀዲሙ ውስተ መስጴጦምያ፤

ከከነዓን አስቀድሞ በሶርያ ተቀመጡ፤

እስመ ኢይፈቅዱ ይትልዉ አማልክተ አበዊሆሙ እለ ኮኑ በምድረ ከላውዴዎን፤

በከላውዴዎን የነበሩ ያባቶቻቸውን ጣዖት ይከተሉ ዘንድ አይወዱምና፤

፰፡ ወኃደጉ ፍኖተ አዝማዲሆሙ፤

የዘመዶቻቸውን ሥራ ተዉ፤

ወሰገዱ ለአምላከ ሰማይ፤

ሰማይን ለፈጠረ አምላክ ሰገዱ፤

ለእግዚአብሔር ዘአእመሩ፤

ለሚያውቁት ለእግዚአብሔር ሰገዱ፤

ወዘአውፅአሙ እምቅኔ አማልክቲሆሙ፤

ለጣኦት ከመገዛት ላወጣቸው ለእግዚአብሔር ሰገዱ፤



ወጐዩ ውስተ መስጴጦምያ፤

ወደሶርያ ሸሹ፤

ወነበሩ ህየ ብዙኀ መዋዕለ፤

ብዙ ዘመን ከዚያ ተቀመጡ፤

፱፡ ወይቤሎሙ አምላኮሙ ይፃኡ እምኀበ ፈለሱ፤

ተሰደው ከሄዱበት ሀገር ወጥተው፤

ወይሑሩ ምድረ ከነዓን፤

ወደከነዓን ይሄዱ ዘንድ አዘዛቸው፤

ወሖሩ ምድረ ከነዓን፤

ወደከነዓን ሄዱ፤

ወነበሩ ህየ ብዙኀ መዋዕለ፤

ብዙ ዘመን ከዚያ ተቀመጡ፤

ወአብዝኁ ወርቀ ወብሩረ፤

ብሩን ወርቁን አበዙ፤

ወእንስሳ ብዙኀ ጥቀ፤

ብዙ ከብት ሰበሰቡ፤

፲፡ ወወረዱ ውስተ ምድረ ግብፅ፤

ወደ ግብፅ ወረዱ፤

እስመ ከደነ ገጸ ምድረ ከነዓን ረኃብ፤

በከነዓን አውራጃ ሁሉ ረሀብ ሁኗልና፤

ወነበሩ ህየ እስከ አመ ተሴሰዩ፤

ከግብፅ ወጥተው በሙሴ እጅ መናውን እስኪመገቡ ድረስ፤ አንድም በዮሴፍ እጅ እስኪ መገቡ ድረስ፤

ወበዝኁ በህየ ወመልኡ፤

በዚያ በዙ ሀገሩን ሁሉ መሉ፤

ወአልቦሙ ኍልቈ ለዘመዶሙ፤

ለወገናቸው ስፍር ቁጥር አልነበረውም፤

፲፩፡ ወተንሥአ ላዕሌሆሙ ንጉሠ ግብፅ፤

የግብፅ ንጉሥ ፈርዖን በጠላትነት ተነሥቶ፤

ወተጠበቦሙ፤

ተተነኮለባቸው፤

ወአሕመሞሙ፤

መከራ አጸናባቸው፤

ወቀነዮሙ በግንፋል፤

ጡብ በማሠራት ገዛቸው፤

ወረሰዮሙ አግብርተ፤

ባሮች አደረጋቸው፤

፲፪፡ ወጸርሑ ኀበ አምላኮሙ፤

ከፈጣሪያቸው ዘንድ ጮሁ፤

ወቀተለ ኵሎ ምድረ ግብፅ በመቅሠፍት ዘአልቦ ፈውስ፤

ድኅነት በማይገኝበት በመቅሠፍት ግብፅን ሁሉ አጠፋ፤

ወአውፅአሙ እምግብፅ እምቅድመ ገጾሙ፤

ከግብፅ በፊታቸው አወጣቸው፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፫፡ ወአይበሳ እግዚአብሔር ለባሕረ ኤርትራ እምቅድሜሆሙ፤

እግዚአብሔር የኤርትራን ባሕር ከሁለት ከሦስት ከፈላት፡

፲፬፡ ወወሰዶሙ ውስተ ሲና ወቃዴስ በርኔ፤

ወደደብረ ሲና ወደቃዴስ በርኔ ወሰዳቸው፡

ወአውፅኦሙ ለኵሎሙ እለ ይነብሩ ውስተ ገዳም፤

በምድረ በዳ የሚኖሩትን ሁሉ አወጣቸው፡

፲፭፡ ወነበሩ ውስተ ምድረ አሞሬዎን፤

በአሞሬዎን ሀገር ተቀመጡ፡

ወአጥፍኦሙ ለኵሉ ሐሴቦን በኃይሉ፤

በኃይሉ በሐሴቦን የሚኖሩትን አጠፋቸው፡

ወአደዉ ዮርዳኖሰ ወተዋረሱ ኵሎ ደወሎሙ፤

ዮርዳኖስን ተሻግረው ሀገሩን ሁሉ ወረሱ፡

፲፮፡ ወአውፅኦሙ እምቅድመ ገጾሙ ለከናኔዎን ወፌርዜዎን ወኢያቡሴዎን ወኬጤዎን ወሴኬም፤

ከናኔዎንን፤ ፌርዜዎንን፤ ኢያቡሴዎንን፤ ኬጤዎንን፤ ሴኬምን ከእስራኤል ፊት አወጣቸው፡

ወኵሉ ጌርጌሴዎን፡

ጌርጌሴዎንን ሁሉ፡ አወጣቸው፡

ወነበሩ ህየ ብዙኃ መዋዕለ፤

ብዙ ዘመን ከዚያ ተቀመጡ፡

፲፯፡ ወአምጣነ ኢአበሱ ቅድመ አምላኮሙ፤

ፈጣሪያቸውን ሳይበድሉ የኖሩ ትን ያህል፡

ወነበረት ምስሌሆሙ ኵላ ሠናይት፤

ተድላ ደስታ ከነዚያ ጋራ ትኖር ነበረች፡

እስመ እግዚአብሔር ጸላኤ ዓመፃ ሀሎ ምስሌሆሙ፤

ኃጢአትን የሚጠላ እግዚአብ ሔር በረድኤት ከነዚያ ጋራ ነበረና፡

፲፰፡ ወአመ ባሕቱ ኃደጉ ፍኖቶ እንተ አዘዞሙ፤

ያዘዛቸውን ሥራ በተዉ ጊዜ ግን፡

አጥፍኦሙ ወሠረዎሙ በብዙኅ አዕባእት ወፈድፋደ ጥቀ፤

በሠራዊት ብዛት ፈጽሞ አጠ ፉቸው፡

ወተዴወዉ ውስተ ብሔረ ባዕድ፤

ወደባዕድ ሀገር ተማርከው ሄዱ፡

ወቤተ አምላኮሙ መዝበረ፤

የፈጣሪያቸው ማደሪያ ቤተ መቅደሱ ፈረሰ፡

ወምድረ ኮነ፤

ምድረ በዳ ሆነ፡



ወአህጉሪሆሙኒ ነሥእዎሙ ፀሮሙ፤

ሀገራቸውን ጠላቶቻቸው ወር ሰውት ነበረ፡

፲፱፡ ወይእዜሰ ተመይጡ ኀበ አም ላኮሙ፤

ዛሬ ግን በአምልኮት ወደፈጣ ሪያቸው ተመለሱ፡

ወተጋብኡ ህየ እምነበ ተዘርዉ ወነበሩ ኢየሩሳሌም ኀበ ሀለወ መቅደሰሙ፤

ከተበተኑበት ሀገር ተሰብስበው መቅደሳቸው ካለበት በኢየሩ ሳሌም ተቀመጡ፡

ወውስተ አድባርኒ ነበሩ እስመ ሐቅል ውእቱ፤

ሀገራቸው ጠፍቶ ነበርና፡ ዛሬም ከዚህ ከተራራው ላይ ተቀምጠዋል፡

፳፡ ወይእዜኒ እግዚኦ አመ አበሱ እሉ ሕዝብ፤

አሁን እነዚህ ወገኖች በድለው እንደሆነ፡

ወቦ ዘአበሱ ለአምላኮሙ፤

ፈጣሪያቸውን የበደሉት በደል አለ እንደሆነ፡

ንጠይቅ ምዕረ፤

አንድ ጊዜ እንጠይቅ፡

እስመ ዝንቱ እቅፍቶሙ፡

አጥፊያቸው ይህ ነውና፡

ወእምዝ ነዐርግ ወንትቃተሎሙ፤

ከዚህ በኋላ ዘምተን እንዋጋ ቸዋለን፡

፳፩፡ ወአመሰ አልቦሙ ለእሉ ሕዝብ አበሳ ኢትትአደዎሙ እግዚእየ፤

እኒህ ወገኖች የበደሉት የለ እንደሆነ ጌታዬ አትሂድባቸው፡

ዮጊ ያጸንዖሙ እግዚአብሔር፤

ወይ እግዚአብሔር ያጠናቸው ይሆናል፡

ወአምላኮሙ ይቀውም ሎሙ፤

ፈጣሪያቸው ጠበቃ ሁኖ ይቆምላቸዋል፡

ወንከውን ኃፍረተ ውስተ ኵሉ በሐውርት፡

በሀገሩ ሁሉ መዘባበቻ እንሆናለን፡

፳፪፡ ወእምዝ ሶበ አኅለቀ ነቢበ አኪዮር ዘንተ ነገረ፡

አኪዮር ይህን ነገር ከተናገረ በኋላ፡

ወአንጐርጐሩ ኵሉ ሕዝብ እለ ይቀውሙ ዓውደ ትዕይንት፡

በሠፈሩ ዙሪያ የቆሙ ሰዎች አንጐራጐሩ፡

ወይቤልዎ መሳንፍቲሁ ለሆሎፎ ርኒስ፤

ሹማምንቱ ሆሎፎርኒስን እንዲህ አሉት፡

www.ethiopianorthodox.org

ወኵሉ እለ ይነብሩ ውስተ ጰራልያ ወሞዓብ ከመ ይቅትልዎ፣

በሞዓብ በጰራልያ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ሆሎፎርኒስን እንዲህ አሉት፤ አክዮርን ይገድሉት ዘንድ እንግደለው አሉ፤

፳፫፤ ወይቤሉ ዘአኮ ንፈርሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ሕዝብ እለ አልቦሙ ኃይል ወዕንዕ ከመ ይትቃተሉ ምስለ ጸባዒት ጽንዕት፣

ካርበኞች ጋራ ይዋጉ ዘንድ ኃይል ጽንዕ የሌላቸው የእስራ ኤልን ልጆች የምንፈ ጃቸው አይደለም?

፳፬፤ ወንዕርግ ባሕቲ፣

ነገር ግን እንዝመት፤

ወይኩኑ ለሲሳየ ኵሉ ሐራከ እግዚ እነ ሆሎፎርኒስ፣

ጌታችን ሆሎፎርኒስ የጭፍሮ ችህ ምግብ ይሆኑ ዘንድ እንዝ መት።።

## ምዕራፍ ፯

፩፤ ወእምዝ ሶበ አርመሙ እልክቱ ዕደው እለ ዓውደ እንግልጋ፣

ከዚህ በኋላ ባደባባይ የተሰ በሰቡ ሰዎች ሁሉ ዝም ባሉ ጊዜ፤

ይቤሎ ሆሎፎርኒስ መልአከ ኃይሉ ለአሶር ለአክዮር በቅድመ ኵሉ ሕዝበ ኢሎፍሊ፣

የናቡከደነፆር ቢትወደድ ሆሎፎርኒስ በኢሎፍላውያን ወገኖች ሁሉ ፊት አክዮርን እንዲህ አለው፤

ውነበ ኵሉ ደቂቀ ሞአብ፤

በሞዓብ ልጆች ሁሉ ዘንድ፤

፪፤ ገባዒሁ ለኤፍሬም ከመ ትትነ በይ ለነ ዮም፣

ዛሬ ለኛ ትነግረን ዘንድ ለኤፍ ሬም ወታደሩ አንተ ነህ? አንድም ጠንቋዩ አንተ ነህ? አንድም ወሬ የምታወ ራለት አንተ ነህ?

ወትብለነ ኢትዕብዕዎሙ ለደቂቀ እስራኤል፣

የእስራኤልን ልጆች አትው ጓቸው የምትለን አንተ ነህ?

እስመ እግዚአብሔር ያጸንዖሙ፣

እግዚአብሔር ያጸናችዋልና፤

መኑ ውእቱ እግዚአብሔር ዘእን በለ ናቡከደነፆር፣

ከናቡከደነፆር በቀር እግዚአ ብሔር ማነው?

፫፤ ውእቱ ይፌኑ መልእክቶ ወያ ጠፍአሙ፣

እሱ መልእክተኛውን ሰዶ ያጠ ፋቸዋል፤



ወይዘርዎሙ እምገጸ ምድር፣

ከዚህ ዓለም ያጠፋቸዋል፤

ወኢያድኅኖሙ አምላኮሙ፤

ፈጣሪያቸው አያድናቸውም፤

ወንሕነሰ አግብርቲሁ ለናቡከደነፆር ንሴርዎሙ፤ ከመ አሐዱ ብእሲ፣

የናቡከደነፆር ባሮች እኛ አንድ ሰው ሲያጠፉት እንዳያስቸግር ሳያስቸግሩን እናጠፋቸዋለን፤

ወኢይትቃወምዎ ለኃይለ አፍራ ሲነ፣

የፈረሶቻችንን ኃይል አይቃ ወሙትም፤

፬፤ እስመ ቦቱ ንከይዶሙ፣

ከዚህ እናጠፋቸዋለንና፤

ወአድባሪሆሙኒ ይሰክሩ በደሞሙ፣

ተራሮቻቸው ሁሉ በደማቸው ይታለላሉ፤

ወይበዝኅ አብድንቲሆሙ፣

ሬሳቸው ይበዛል፤

ወደቂቆሙ ኢይቀውሙ በሰኰና እግሮሙ፣

ልጆቻቸውም በነዚያ እግር አይቆሙም፤ ማለት ጠንተው አይዋጉም፤ አንድም ልጆቻ ቸው በእግራቸው አይተኩም፤

በቅድመ ገጽነ አላ ጠፊአ ይጠፍኡ እምነ ምድር፣

በፊታችን ከዚህ ዓለም ፈጽመው ይጠፋሉ እንጂ፤

ይቤ ንጉሥ ናቡከደነፆር እግዚአ ለኵላ ምድር፣

የዓለም ሁሉ ጌታ ናቡከደነፆር እንዲህ አለ፤

እስመ ይቤ ከመ ኢይኩን ቃሉ፣

ነገሩ ከንቱ እንዳይሆን እንዲህ ብሏልና፤

፭፤ ወአንተሰ አኪዮር ገባዒሁ ለአሞን ዘነበብከ ዘንተ ቃለ፣

የአሞን ወታደሩ፤ አንድም ጠንቋዩ የምትሆን ይህን ነገር የተናገርህ አኪዮር፤

ዮም ኢትሬኢ ገጽየ፣

ዛሬ ፊቴን አታየውም፤

እምዮም እምይእቲ ዕለት በኃጢ አትከ፤

ከዚች ቀን ከዛሬ ጀምሮ በኃጢ አትህ ፊቴን አታየውም፤

እስከ አመ እትቤቀሎሙ ለእለ ወጽኡ እምድረ ግብፅ፣

ከግብፅ የወጡ እሥራኤልን ተበቅዬ እስከ አጠፋቸው ድረስ፤

፯፤ ወውእተ አሚረ ይበውእ ኃጺኖሙ ለሐራየ ወዘሕዝብየ ውስተ ገቦከ፣

ያን ጊዜ የወገኖቼ፣ የጭፍሮቼ ጦራቸው ወደጐንህ ይገባል፤

ወትወድቅ ምስለ አብድንቲሆሙ፣

ከሬሳቸው ጋራ ትወድቃለህ፤

www.ethiopianorthodox.org

፯፡ ወሶበ ገባእኩ ይወስዱከ አግብርትየ ውስተ አድባሪሆሙ፤

በተመለስሁ ጊዜ ባሮቼ ወደአምባቸው ይወስዱሃል፡

ወያነብሩከ ውስተ አሐቲ እምአህጉሪሆሙ እለ ውስተ ዓቀብ፤

በተራራ አጠገብ ካሉ ተራራዎች በአንዲቱ ያኖሩሃል፡

፰፡ ወኢይቀትሉከ እስከ አመ እሜርዎሙ፤

እነዚያን እስካጠፋቸው ድረስ አይገድሉህም፡

፱፡ እስመ ትትአመን በልብከ ከመ ኢንክሎሙ፤

በልቡናህ እንዳንችላቸው ትታመናለህና፡

ኢትወድቅ ገጽከ፡

ዛሬ አትሞትም፡

እስመ አንሰ ነበብኩ ወአልቦ ዘይወድቅ እምነ ቃልየ፤

እኔ ተናግሬያለሁና ከተናገርሁት አንድ የሚቀር የለምና፡

፲፡ ወአዘዞሙ ሆሎፎርኒስ ለአግብርቲሁ እለ ይቀውሙ ቅድሜሁ ውስተ ደብተራሁ፤

ሆሎፎርኒስ በድንኳኑ ተቀምጦ ሳለ በፊቱ የሚቆሙ ባሮችን አዘዛቸው፡

ከመ ይንሥእዎ ለአኪዮር ወይሰድዎ ቤጤልዋ፤

አኪዮርን ይዘው ወደቤጤልዋ ይወስዱት ዘንድ፡

ወያወፍይዎ ለደቂቀ እስራኤል ኪያሁ፤

እሱን ለእስራኤል ልጆች ይሠጡት ዘንድ፡

፲፩፡ ወነሥእዎ፡ አግብርቲሁ ወወሰድዎ አፍአ እምትዕይንት ውስተ ገዳም፤

ባሮች እግሩን ፈትተው እጁን አሥረው ይዘው ከከተማው ውጭ ወደምድረ በዳ ወሰዱት፡

ወሖሩ እምነ ማዕከለ ገዳም ውስተ አድባር፤

ከምድረ በዳው መካከል ወደተራራው ሄዱ፡

ጉባዔ

ወእምዝ በጽሑ ኀበ አንቅዕት ዘመትሕተ ቤጤልዋ፤

ከዚህ በኋላ ከቤጤልዋ በታች ካለው ምንጭ ደረሱ፡

፲፪፡ ወሶበ ርእይዎሙ ሰብአ ይእቲ ሀገር ውስተ ርእሰ ደብር ነሥኡ ንዋየ ሐቅሎሙ፤

የዚያች ሀገር ሰዎች ከተራራ ላይ ሆነው ባዩአቸው ጊዜ ጋሻ ጦራቸውን አነሱ፡

ወሖሩ አፍአ እምነ ሀገር ውስተ ርእሰ ደብር፤

ከሀገሩ ውጭ ወደሚሆን ወደተራራው ራስ ሄዱ፡



ወኵሉ ሰብአ ሞጻፍ ዓቀቡ ፍሥሐታተ፡

ምድር ነጐድ የያዙ ሰዎች ምሽጉን ጠበቁ፡

ወአመርግሐ ዕብነ ላዕሌሆሙ፤

በላያቸው ላይ መርጉን ደንጊያ እየፈነቀሉ ይሰዱ ጀመረ፡

፲፫፡ ወፈትሕዎ ማኅሜሁ ለአኪዮር ወአሠርዎ ጕንደ ደብር፡ ወኀደግዎ ህየ መትሕተ ደብር ግዱፈ፡

ከዚያ ከተራራው በታች፡ አኪዮርን እጁን ፈትተው እግሩን አሥረው ከተራራው ስር ጥለውት ሄዱ፡

ወአተዉ ኀበ እግዚኦሙ፤

ወደጌታቸው ተመለሱ፡

፲፬፡ ወወረዱ ደቂቀ እሥራኤል እምነ አህጉሪሆሙ፤

የእሥራኤል ልጆች ከተራራው ላይ ወርደው፡

ወሖሩ ኀቤሁ፡

ወደሱ ሄዱ፡

ወፈትሕዎ ወወሰድዎ ብሔረ ቤጤልዋ፤

ፈትተው ወደቤጤልዋ ወሰዱት፡

ወሤምዎ ውስተ መላእክተ አህጉሪሆሙ፤

በሀገሮቻቸው አለቆች ላይ ሾሙት፡

፲፭፡ እለ ሀለዉ በኪያሆን መዋዕል፡

በውእቶን መዋል ሲል ነው፡ በዚያ ወራት በነበሩ፡

ያዝያስ ወልደ ሚካ ዘእምነገደ ስምዖን ወክብሪስ ወልደ ጎቶንያል፤

በጎቶንያል ልጅ በክብሪስና ከነገደ ስምዖን በተወለደ በያዝያስ መካከል አስቀመጡት፡

፲፮፡ ወጸውኡ ኵሎ ሊቃውንተ አህጉሪሆሙ፤

የሀገሮቻቸውን አለቆች ጠሩ፡

ወሮጹ ኵሉ ወራዙቶሙ፤

ጐልማሶች ሁሉ ፈጥነው ሄዱ፡

ወአንስቲያሆሙኒ ውስተ ምንግላ ጊሆሙ፤

ሚስቶቻቸውም ወደ አደባባይ ሄዱ፡

ወአቀምዎ ለአኪዮር ማእከለ ኵሎሙ፤

አኪዮርን በመካከላቸው አቆሙት፡

ወተስእሎ ያዝያስ ኵሎ ዘከመ ኮነ፤

ያዝያስ የሆነውን ሁሉ ነገር ጠየቀው፡

፲፯፡ ወአውሥአሙ ወአይድአሙ ነገሮ ለሆሎፎርኒስ ኵሎ ዘከመ አንገለጉ፤

እንደ ተሰበሰቡ የሆሎፎርኒስን ነገር ሁሉ ነገራቸው፡

www.ethiopianorthodox.org

ወኵሎ ቃሎሙ ዘከመ ይቤሉ በማዕከለ መላእክቲሆሙ ለደቂቀ አሶር፤

በኃያላኑ ልጆች አለቆች መካከል የተናገሩትን ቃላቸ ውን ሁሉ ነገራቸው፤

ወመጠነ አዕበየ አፉሁ ሆሎፎርኒስ ላዕለ ቤተ እስራኤል፤

ሆሎፎርኒስ በእስራኤል ወገኖች ላይ ቃሉን ከፍ ከፍ አድርጎ የተናገረውን ያህል ነገራቸው፤

፲፰፡ ወወድቁ ኵሉ ሕዝብ ወሰገዱ በገጾሙ ለእግዚአብሔር፤

ሕዝቡ ሁሉ በግንባራቸው ወድ ቀው ለእግዚአብሔር ሰገዱ፤

፲፱፡ ወጸርሑ ወይቤሉ እግዚእ አምላከ ሰማይ ርኢ ትዕይርቶሙ፤

ጮኸው እንዲህ አሉ፤ ሰማይን የፈጠርህ አምላክ ትዕቢታ ቸውንእይ ተመልከት አሉ፤

ወአስተምሕር ሕማሞሙ ለዘመድነ፤

የወገኖቻችንን መከራቸውን አይተህ እዘንላቸው፤

ወነጽር ላዕለ መቅደስከ በሠናይ በዛቲ ዕለት፤

በዚች ቀን ማደሪያህ ቤተ መቅደስን በዓይን ምሕረት ተመልከት፤

፳፡ ወአስተፍሥሕዎ ለአኪዮር፤

አኪዮርን ደስ አሰኙት፤

ወአእኰትዎ ጥቀ፤

እጅግ አከበሩት፤

፳፩፡ ወነሥኦ ዖዝያስ እምነበ አንገለጉ ወአእተዎ ቤቶ፤

ዖዝያስ ከዚያ ከተሰበሰቡበት ወስዶ ከቤቱ አገባው፤

ወገብረ በዓለ ለሊቃናት፤

ላለቆች በዓል አደረገ፤

ወጸውዕዎ ለአምላከ እስራኤል ኵላ ይእተ ሌሊተ ከመ ይርድኦሙ፤

ይረዳቸው ዘንድ ሌሊቱን ሙሉ የእስራኤልን ፈጣሪ ለመኑ።።

## ምዕራፍ ፯

፩፡ ወበሳኒታ አዘዘ ሆሎፎርኒስ ለኵሉ ሐራሁ ወለኵሉ ሕዝቡ እለ ፀብዑ ምስሌሁ፤

በማግሥቱ ሆሎፎርኒስ ከሱ ጋራ ወደሰልፍ የወጡ ሕዝቡ ንም ጭፍሮችንም አዘዛቸው፤

ከመ ይግዓዙ ቤጤልዋ፤

ወደቤጤልዋ ይሄዱ ዘንድ፤

ወይሑሩ ይቅድሙ ውስተ ፍትሐ ታተ አድባር፤

አስቀድመው ሄደው ምሽጉን ይይዙት ዘንድ፤ አንድም ፍሥ ሐታተ አድባር ቢል በተራራው ራስ ያለ ኮረብታውን ይቀ ድሙ ዘንድ፤



ወይትቃተልዎሙ ለደቂቀ እስራኤል፤

የእስራኤልን ልጆች ይዋጓቸው ዘንድ፤

፪፡ ወወረዱ ይእተ አሚረ ኵሉ ብእሲ ጽኑዓኒሆሙ ወኃያላኒሆሙ ዕደው መስተ ቃትላን፤

ያን ጊዜ ኃያላኑ ጽኑዓኑ አርበኞች ሰዎች ሁሉ ወረዱ፤

፲ቱ ወ፯ቱ ፻ ዘበእግር፤

አሥራ ሰባት እልፍ እግረኛ፤

ወዘፈረስ ፻ ወ፳፻፤

እልፍ ከሁለት ሽሕ ፈረሰኛ፤

ዘእንበለ ምስለ ንዋይ፤

ከጓዝ ጠባቂው ሌላ፤

ወዘእንበለ ዕደው እለ ኢሮዱ አጋርያን ብዙኃን ጥቀ፤

አምባውን ታልከበቡት ሰዎች ሌላ ብዙዎች ነበሩ፤

፫፡ ውነደሩ ውስተ ዓውሎንያ ገቦሃ ለቤጤልዋ ኀበ ነቅዕ፤

ምንጭ ካለበት በቤጤልዋ አጠገብ በአውሎንያ ሰፈሩ፤

ወበጽሐ ተዓይኒሆሙ ኑኁ እስከ ዶታይም ወእስከ ቤልሜም፤

የሰፈራቸው ቁመት ከዶታይም እስከ ቤልሜም ደረሰ፤

ወግድሙ እስከ ቀያስም እምነ ቤጤልዋ እንተ እምቅድመ አስዲራሎም፤

ወርዱም በአስዲራሎም አንጻር ካለች ከቤጤልዋ ጀምሮ እስከ ቅያስም ድረስ ነው፤

፬፡ ወሶበ ርእዩ ብዝኆሙ ደቂቀ እስራኤል ደንገጹ ጥቀ፤

የእስራኤል ልጆች ብዛታቸውን ባዩ ጊዜ ፈጽመው ደነገጡ፤

ወተበሀሉ በበይናቲሆሙ የአጽውዎ ይእዜ ለኵሉ ገጸ ምድር እሉ፤

እርስ በርሳቸው፤ እንዲህ ተባባሉ፤ እኒህ ሀገሩን ሁሉ ይዘጉታል አሉ፤

ወአልቦ ዘይክል ፀዊረ ክበዶሙ፤

ብዛታቸውን የሚችል የለም፤

ኢአድባር ወኢአውግር፤

ተራራውም ኮረብታውም ሁኖ፤

ወኢቈላት፤

ቆላውም ሆኖ ብዛታቸውን አይችልም፤

፭፤ ወነሥኡ ኵሎሙ ንዋየ ሐቅሎሙ፤

ሁሉም ጋሻ ጦራቸውን ያዙ፤

ወአንደዱ እሳተ ውስተ ማኅፈዲሆሙ ወነበሩ የዓቅቡ ኵላ ይእተ ሌሊተ፤

እሳቱን ከግምቡ ላይ አንድደው ሌሊቱን ሙሉ ሲጠብቁ አደሩ፤

www.ethiopianorthodox.org

፮፡ ወበሳኒታ ዕለት አውዕአ ሆሎፎርኒስ ኵሎ አፍራሲሁ ቅድሜሆሙ ለደቂቀ እስራኤል እለ ውስተ ቤጤልዋ፤

በማግሥቱ ሆሎፎርኒስ በቤጤልዋ ለሚኖሩ ለእስራኤል ልጆች የፈረስ ግብዓት አሳያቸው፤

፯፡ ወፈነወ ሰብአ ዓይን ይርአዩ ፍሥሐታተ አህጉሪሆሙ፤

የሀገራቸውን ምሽግ ያዩ ዘንድ ጉበኛ ሰደደ፤

ወይዑዱ አንቅዕተ ማያቲሆሙ ይቅድምዎ በጺሐ ህየ፤

ከዚያ አስቀድመው ሂደው ምንጮን ይከቡ ዘንድ፤

ወይትዐየንዎሙ ዕደው መስተቃትላን፤

አርበኞች ሰዎች ይከቧቸው ዘንድ፤

ወውእቱሰ ሮፀ ምስለ ሕዝቡ፤

እሱም ከወገኖቹ ጋራ ፈጥኖ ሄደ፤

፰፡ ወመጽኡ ኀቤሁ ኵሉ መላእክተ ደቂቀ ኤሳው፤

የኤሳው ልጆች አለቆች ሁሉ ወደሱ መጡ፤

ወኵሎሙ መሳፍንተ ቤተ ሞዓብ፤

የሞዓብ ወገኖች መሳፍንት ሁሉ፤

ወመኳንንተ ጳራልያ፤

የጳራልያ መኳንንት፤

፱፡ ወይቤልዎ ስማዕ እግዚኦ ቃለነ ከመ ኢይኩን ሙስና ላዕለ ሕዝብከ፤

በወገኖችህ ላይ ጥፋት እንዳ ይመጣ አቤቱ ነገራችንን ስማን፤

፲፡ እስመ ዝንቱ ሕዝበ ደቂቀ እስራኤል፤

ይህ የእስራኤል ልጅ ወገን፤

አኮ በኲናቶሙ ዘይትዌከሉ፤

በጦራቸው የሚታመኑ አይ ደለም፤

አላ በላዕለ አጽዋኒሆሙ ወአድባሪሆሙ እለ ይነብሩ ውስቴቶሙ፤

በሚኖሩባቸው ባምባቸው ነው እንጂ፤

እስመ አልቦ ምዕራግ ለአድባሪሆሙ፤

አምባቸው መውጫ የለውምና

፲፩፡ ወይእዜኒ እግዚኦ ኢትትቃተሎሙ በሕገ ቀትል፤

በፈረስ ተቀምጨ ጋሻ መክቼ እዋጋለሁ አትበል፤

ወአልቦ ዘይመውት እምነ ሰብእከ ወኢአሐዱ ብእሲ፤

እኛ እንደነገርንህ ያደረግህ እንደሆነ ፤ ከሰዎችህስ እንኳ አንድ ሰው የሚሞት የለም፤

፲፪፡ ወባሕቱ ጽንሓሙ ምስለ ተዓይኒከ፤

ነገር ግን ከሠራዊቶችህ ጋራ ጠብቃቸው፤



ወይዕቀቡ ኵሎ ዕደወ ኀይልከ ወደቂቅከ ኵሎ አንቅዕተ ማያቲሆሙ ዘይነቅዕ እምጕንደ ደብር ያጽንዑ፤

ብላቴኖችህ ኃይል ያላቸው ሰዎች ሁሉ ከተራራው ስር ያለውን ምንጭ አጽንተው ይጠብቁ ዘንድ፤

፲፫፡ እስመ እምህየ ይቀድሑ ኵሎሙ እለ ይነብሩ ቤጤልዋ፤

በቤጤልዋ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ከዚያ ይቀዳሉና፤

ወይቀትሎሙ ጽምዕ ወየገብኡ ድኅሬሆሙ፤

ውሀ ጥም ይገድላቸዋል፤ ሀገራቸውን አሳልፈው ለኛ ይሰጣሉ፤

ወንሕነኒ ወሕዝብነኒ ነዓርግ ኀበ ቅሩበ አጽዋኒሆሙ ወአርእስተ አድባሪሆሙ፤

እኛም ወገኖቻችንም ወዳምባቸው አጠገብ ወደተራራው ራስ እንወጣለን፤

ወነኀድር ህየ ወነዓቅቦሙ፤

ከዚያ ሰፍረን እንጠብቃቸዋለን፤

ከመ አልቦ ዘይወጽእ እምኔሆሙ ወኢሐዱ ብእሲ እምውስተ አህጉሪሆሙ፤

ከሀገራቸው አንድ ሰውስ እንኳ ከነዚያ ወገን የሚወጣ እንዳይኖር፤

፲፬፡ ወይጠፍኡ በረሀብ እሙንቱኒ ወአንስቲያሆሙኒ ወውሉዶሙኒ ዘእንበለ ይትቃተልዎሙ፤

ሳይዋጓቸው ልጆቻቸውም ሚስቶቻቸውም እነሱም በረሀብ ያልቃሉ፤

ወይትነጽሑ በውስተ ፍናወ አህጉሪሆሙ፤

በሀገራቸው ጎዳና ይወድቃሉ፤

፲፭፡ ወትትቤቀሎሙ እኩየ በቀለ፤

በረሀብ ታጠፋቸዋለህ፤

እስመ አዕረሩ፤

ግብር ነስተዋልና፤

ወኢተቀበሉከ በሰላም፤

በፍቅር በደስታ አልተቀበሉ ህምና፤

፲፮፡ ወአደመ ቃሎሙ በቅድሜሁ ለሆሎፎርኒስ፤

ነገራቸው ሆሎፎርኒስን በፊቱ ደስ አሰኘው፤

ወቅድመ ኵሉ ሰብኡ፤

በሰዎቹ ፊት ደስ አሰኘው፤

ወአዘዘ ይግበሩ በከመ ይገብሩ፤

እንዳሉ ያደርጉ ዘንድ አዘዘ፤

፲፯፡ ወግዕዙ ተዓይኒሆሙ ለደቂቀ አሞን፤

የዓሞን ልጆች ሠራዊታቸውም ተጓዙ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወምስሌሆሙ ፶፻ ደቂቀ አሶር፣

የኃያላኑ ልጆች አምስት ሽሕ ሰዎች ከነዚያ ጋር አብረው ነበሩ፤

ወኃደሩ ውስተ ዓውሎኒ፣

በዓውሎኒ ሰፈሩ፤

ወቀደሙ አጽንአ ማያቲሆሙ ወአንቅዕቲሆሙ ለደቂቀ እስራኤል፣

የእስራኤልን ልጆች ምንጫቸውን ውሃቸውን አጽንተው ያዙ፤

፲፰፤ ወዐርጉ ደቂቀ ኤሳው ወደቂቀ አሞን፣

የኤሳው ልጆችና የአሞን ልጆች ወጡ፤

ወኃደሩ ውስተ አድባር አንፃረ ዶታይም፣

በዶታይም አንፃር ከተራራው ላይ ሰፈሩ፤

ወፈነዉ እምውስቴቶሙ እለ መንገለ ዓረብ ዘአዜብ፣

ከሳቸው ወገን በአዜብ አቅራቢያ ወደምትሆን ወደምዕራብ ሰደዱ፤

ወኤጼልዮጤን ዘአንፃረ ኤጼራቤል ዘገቦ ኩሲ በኀበ ፈለገ ምኩር፣

ምኩር በሚባል ወንዝ ዘንድ በኩሲ አጠገብ በኤቄልቤል አንፃር ወዳለ ወደኤጼልዮጤንም ላኩ፤

ወዘተርፈ ሠራዊቶሙ ለፋርስ ተዓየኑ ውስተ ገዳም፣

የፋርስ ሰዎች የቀረው ሠራዊታቸው በምድረ በዳ ሠፈሩ፤

ወከደኑ ውስተ ኵሉ ገጸ ምድር፣

ምድሩን ሁሉ ሸፈኑት፤

ወእምዝ ዓግአዙ ተአይኒሆሙ፣

ከዚህ በኋላ ሠራዊቶቻቸው ተነሡ፤

ወንዋዮሙኒ ብዙኃ፣

ብዙ ገንዘባቸውን ይዘው ተነሡ፤

ሰብአ ጥቀ ዘአልቦ ዘይበዝኆሙ፣

ስፍር ቁጥር የሌለው ብዙ ሰው ነበር፤

፲፱፤ ወጸርሑ ደቂቀ እስራኤል ኀበ እግዚአብሔር አምላኮሙ፣

የእስራኤል ልጆች ከፈጣሪያቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ ጮሁ፤

እስመ አንበዘት ነፍሶሙ፣

አእምሯቸው እለይ እለይ ብላለችና፤

እስመ አገትዎሙ ኵሉ ፀሮሙ፣

ጠላቶቻቸው ስለከበቧቸው፤

ወአልቦሙ ሙፃእ እምነ ማዕከሎሙ፣

ከመካከላቸው መውጫ ስለሌላቸው፤



፳፤ ወነበሩ ደቂቀ አሶር ምስለ ኵሉ ተዓይኒሆሙ የዓግትዎሙ፣

የኃያላኑ ልጆች ከሠራዊታቸው ጋራ ይጠብቋቸው ነበረ፤

አጋሮሙኒ፣

አርበኞቻቸው፤

ወሰብአ ሠረገላትኒ፣

በሠረገላ የተቀመጡ ሰዎች፤

ወሰብአ አፍራስኒ፣

በፈረስ የተቀመጡ ሰዎች ሠለሰ ወረቡዓ መዋዕለ፤

ሦስት ቀንም ቢሆን አራት ቀንም ቢሆን ከበዋቸው ነበር፤ አንድም ሦስትና አራት ሰባት ነው፤ ሰባት ቀን የከበበ አለ፣

ወኃልቀ ኵሉ ሙዳየ ማዮሙ ለእለ ይነብሩ ቤጤልዋ፣

ማየ ሙዳዮሙ ሲል ነው፤ በቤጤልዋ የሚኖሩ ሰዎች ባቅማዳ በማድጋ ያመጡት ውሃቸው አለቀ፤

፳፩፤ ወአልቦ ዘይሰትዩ ማየ ወዘያረውዮሙ፣

አንዲት ቀን የሚያረካቸው የሚጠጡት ውሀ አልነበራቸውም፤

ወበመስፈርት ገብኡ ይስተዩ፣

በመጠን ይጠጡ ጀመረ፤

፳፪፤ ወሐሙ ደቂቆሙ ወአንስቲያሆሙ ወወራዙቶሙ፣

ልጆቻቸው ሚስቶቻቸው ሕፃናት መከራ ተቀበሉ፤

ወሐልቁ በጽምዕ፣

በጥም አለቁ፤

ወይወድቁ ውስተ መርህበ ሀገር፣

በአደባባይ ላይ ይወድቁ ጀመረ፤

ወውስተ ፍናወ አናቅጽ፣

በየበሩ ጐዳና ላይ ይወድቃሉ፤

ወአልቦሙ ኃይል እንከ፣

ኃይል አልነበራቸውም፤ አንድም እውቀት አልነበራቸውም፤

፳፫፤ ወተጋብኡ ኵሉ ሕዝብ ላዕለ የዝያን ወመላእክተ ሀገርኒ፣

ሕዝቡ ሁሉ የሀገር አለቆችም ከየዝያን ዘንድ ተሰበሰቡ፤

ወወራዙትኒ ወአንስትኒ ወደቂቅኒ፤

ጐልማሶችም ሴቶችም ልጆችም፤

ወጸርሑ በዓቢይ ቃል፣

ቃላቸውን አሰምተው ጮሁ፤

ወይቤሉ በቅድመ ኵሉ ሊቃውንቲሆሙ፣

ባለቆቻቸው ፊት እንዲህ አሉ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፬፡ ይፍታሕ እግዚአብሔር ማዕከሌነ ወማዕከሊክሙ፤

በኛና በናንት መካከል እግዚአብሔር ይፍረድ፤

ከመ ትግበሩ ላዕሌነ ዓቢየ ግፍዐ ዘኢተናገርክሙ ዳህነ በሰላም ምስለ ደቂቀ አሶር፤

በኛ ላይ ጽኑ በደል ታደርጉ ዘንድ ከኃያላኑ ልጆች ጋራ በፍቅር ይህን ነገር ያልተናገራችሁ፤

፳፭፡ ወይእዜሰ ኃጣእነ ዘይረድአነ፤

ዛሬ ግን የሚረዳን አጣን፤

ሤጠነ እግዚአብሔር ውስተ እዴሆሙ ከመ ንደቅ ቅድሜሆሙ በጽምዕ በዓቢይ ኃጕል፤

በጽኑ ጥፋት በጥም ከፊታቸው እንወድቅ ዘንድ እግዚአብሔር በእጃቸው ጣለን፤

፳፮፡ ወይእዜኒ ግርሩ ሎሙ፤

አሁንም ተገዙላቸው፤

ወአግብኡ ኵሎ አህጉሪክሙ፤

ሀገራችሁን ሁሉ ስጧቸው፤

ወይበርብሩ ሕዝበ ሆሎፎርኒስ ወኵሉ ኃይሉ፤

የሆሎፎርኒስ ወገኖች ሠራዊቱን፤ ሕዝቡን ይማርኩ፤ አንድም ወይበርብሩ ሕዝበ ሆሎፎርኒስ ወኵሉ ኃይሉ ሆሎፎርኒስ ሠራዊቱ ሕዝቡን ይማርኩ፤

፳፯፡ እስመ ይኄይሰነ ይበርብሩነ፤

ይበዘብዙን ዘንድ ይሻለናልና፤

ወንተቀነይ ሎሙ፤

እንገዛላቸው፤

ወትሕየው ነፍስነ፤

ሰውነታችን ትድን ዘንድ፤

ወኢንርአይ ሞተ ደቂቅነ በአዕይንቲነ፤

ባይናችን የልጆቻችንን ሞት እንዳናይ፤

እስመ ኀልቀት ነፍሶሙ ለአንስቲያነ ወደቂቅነ፤

የልጆቻችን የሚስቶቻችን፤ ሰውነታቸው እለይ እለይ ብላለችና፤

፳፰፡ ወናሁ ናሰምዕ ለክሙ ሰማየ ወምድረ፤

ሰማይንና ምድርን እናዳኝባችኋለን፤ ዝናም ለዘር፤ ጠል ለመከር እንዳትሰጥ ምድርም የዘሩባትን እንዳታበቅል፤ የተከሉባትን እንዳታጸድቅ፤

ወአምላከ አበዊነ ዘውእቱ ይኬንነነ በከመ ኃጣውኢነ ወበከመ ኃጣውኢሆሙ ለአበዊነ፤

በኛም ኃጢአት ባባቶቻችንም ኃጢአት የሚፈርድብን ያባቶቻችንን ፈጣሪ እናዳኝባችኋለን፤



ከመ ኢትግበሩ ዘንተ ነገረ ዮም በዛቲ ዕለት፤

በዚች ቀን ዛሬ ይህን ነገር እንዳታደርጉ፤

፳፱፡ ወኮነ ብካይ ዓቢይ በማዕከለ ማኅበሮሙ፤

በወገኖቻቸው መካከል ጽኑ ልቅሶ ሆነ፤

ወበከዩ ኵሎሙ ኅቡረ፤

ሁላቸውም አንድ ሁነው አለቀሱ፤

ወጸርሑ በዓቢይ ቃል ኀበ እግዚአብሔር፤

ቃላቸውን አሰምተው ከእግዚአብሔር ዘንድ ጮሁ፤

፴፡ ወይቤሎሙ አዝያስ ተአመኑ አኃዊነ ወተዓገሡ ዓዲ ሐሙሰ መዋዕለ፤

ዖዝያስ እንዲህ አላቸው፡ ወንድሞቼ እመኑ አላቸው፡ ዳግመኛ አምስቱን ቀን ታገሡ፡

እስከ ይመይጥ እግዚአብሔር አምላክነ ምሕረቶ መንገሌነ፤

ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ይቅርታውን ወደኛ እስኪመልስልን ድረስ፤

እስመ አኮ ለዝሉፉ ዘይገድፈነ፤

ፈጽሞ ሁልጊዜ በመከራ የሚጥለን አይደለምና፤

፴፩፡ ወእምከመ ኃለፉ እማንቱ መዋዕል፤

እነዚህ አምስቱ ዕለታት ካለፉ በኋላ፤

ወኢመጽአ ረድኤቱ ላዕሌነ፤

ረድኤቱ ወደኛ ካልመጣልን፤

ንገብር ዘከመ ትቤሉ፤

እንዳላችሁ እናደርጋለን፤

፴፪፡ ወዘረዎሙ ለሕዝብ ውስተ ትዕይንቶሙ ወውስተ ማኅፈዳሆሙ ወውስተ ዐረፍተ ሀገሮሙ፤

ሕዝቡን ወደሰፈራቸው፤ ወደቤታቸው፤ ወደሀገራቸው አደባባይ በተናቸው፡

ወሐሩ ወፈነዉ አንስቲያሆሙ፤

ሂደው ሚስቶቻቸውን ልጆቻቸውን ወደቤታቸው ሰደዱ፡

ወሕሙማን እሙንቱ ጥቀ ውስተ ሀገር፤

በሀገራቸው እጅግ አዝነው ነበር።

## ምዕራፍ ፰

፩፡ ወሰምዓት በኪያሆን መዋዕል ዮዲት ወለተ ሜራሪ፤

በውእቶን መዋዕል ሲል ነው፤ በዚያ ወራት የሜራሪ ልጅ ዮዲት ሰማች፤

www.ethiopianorthodox.org

ወልደ ሆክስ፣

ሜራሪን የሆክስ ልጅ አለው ሽቅብ ይቆጥራል፤

ወልደ ዮሴፍ፣

ሆክስን የዮሴፍ ልጅ አለው፤

ወልደ ያዝያን፣

ያዝያንን የዮሴፍ ልጅ አለው፤

ወልደ ሕልቅያ፣

ሕልቅያን የያዝያን ልጅ አለው፤

ወልድ አናንዩ፣

አናንዩን የሕልቅያ ልጅ አለው፤

ወልደ ጋዲዮን፣

ጋዲዮንን የሬዎን ልጅ አለው፤

ወልደ ራዎይል፣

ራዎይልን የጋዲዎን ልጅ አለው፤

ወልደ ሐቂቶ፣

ራዎይልን የሐቂቶ ልጅ አለው፤

ወልደ ኤልያስ፣

ሐቂቶንን የኤልያስ ልጅ አለው፤

ወልደ ኤልያብ፣

ኤልያስን የኤልያብ ልጅ አለው፤

ወልደ ናትናኤል፣

ኤልያብን የናትናኤል ልጅ አለው፤

ወልደ ሰላምያል፣

ናትናኤልን የሰላምያል ልጅ አለው፤

ወልደ ሰለስዳይ፣

ሰላምያልን የሰለስዳይ ልጅ አለው፤

ወልደ እሥራኤል፣

ሰለስዳይን የእስራኤል ልጅ አለው፤

፪፤ ወምታሰ ምናሴ ዘእምነገዳ ወእምህገራ፣

ከሀገሯ ከነገዷ ወገን የሚሆን ባሏ ግን ምናሴ ይባላል፤

ወሞተ በመዋዕለ ማዕረረ ሰገም፣

የገብስ መከር በደረሰበት ወራት ሞተ፤

፫፤ እስመ ወዐለ ገዳመ ኀበ እለ የአሥሩ ከላስስተ፣

ነዶውን ከሚያሥሩ ሰዎች ጋራ በምድረ በዳ ውሎ ነበርና፤

ወመጽአ ላዕለ ርእሱ ሐሩር፣

ሐሩር፣ ዋዕየ ፀሐይ ራሱን መታው፤

ወአድወዮ ወሰከበ፣

ልባልብ፣ ውርዋ፣ ሥራኤል የሚባል ደዌ አመመው ተኛ፤



ወሞተ በቤጤልዋ ህገሩ፣

በሀገሩ በቤጤልዋ ሞተ፤

ወቀበርዎ ምስለ አበዊሁ ውስተ አፀዶሙ ዶታይም ወበላሞን፣

ካባቶቹ ጋራ በቦታቸው በዶታ ይምና በበላሞን ቀበሩት፤

፬፤ ወነበረት ዮዲት መበለተ ውስተ ቤታ ሠለስ ወረቡዐ ዕለተ፣

ዮዲት ሦስት ቀንም ቢሆን አራት ቀንም ቢሆን በቤቷ ፈት ሁና ተቀመጠች፤ አንድም ሠለስተ ዓመተ ወአርባዕተ አውራኃም ይላል፤

፭፤ ወገብረት ላቲ ዐሪሠ ውስተ ናሕሰ ቤታ፣

በቤቷ አጠገብ ጎጆ፤ አንድም ጉርጅ ጸመ በዓት ምግላል ቦታ ሠራች፤

ወቀነተት ሠቀ ውስተ ሐቋሃ፣

በወገቧ ማቅ ታጠቀች፤

ወለብሰት አልባሰ መበለታ፤

የድህነቷን ልብስ ለበሰች፤

፮፤ ወትጸውም ኵሎ መዋዕለ መበለታ፣

በድህነት የኖረችበትን ቀን ሁሉ ትጾም ነበረ፤

እንበለ እንተ ቅድመ ሰንበት ወሰንበተኒ፣

የቅዳሜ ዋዜማ ቅዳሜ ነው እንጂ፤

ወእንተ ቅድመ ሠርቅ ወሠርቀኒ፣

የመባቻ ዋዜማ የመባቻ ዕለት ነው እንጂ፤

ወበዓላተኒ፣

በበዓለ መጸለት በበዓለ ሠዊት ነው እንጂ፤

ወትፍሥሕተ ቤተ እሥራኤል፣

በበዓለ ፋሲካ ነው እንጂ ምሳ ቀምሳ አታውቅም ነበረ፤

፯፤ ወሠናይት ይእቲ ራዕየ፣

መልከ መልካም ነበረች፤

ወላህይ ገጻ ጥቀ ፈድፋደ፣

ደም ግባቷ እጅግ ያማረ ነበር፤

ወኀደገ ላቲ ምናሴ ምታ ወርቀ ወብሩረ ደቀ ወአዋልደ፣

ምናሴ ባሏ ሴቷን ልጅ ወንዱን ልጅ ወርቁን ብሩን፤

እንስሳ ወገራውሀ፣

ከብቱን እርሻውን ትቶላት ሞተ፤

ወነበረት ላዕሌሆሙ፣

በእነዚያ ላይ እመቤት ሁና ኖረች፤

፰፤ ወአልቦ ዘያወጽእ ላዕሌሃ ቃለ ሕሱመ፣

በዝሙት ያማት የለም፤ አንድም ላግባሽ ያላት የለም፤

www.ethiopianorthodox.org

እስመ ትፈርሆ ለእግዚአብሔር ፈድፋደ፤

እግዚአብሔርን ፈጽማ ትፈራው ነበረችና፤

፱፤ ወሰምዐት ዘይቤሉ ሕዝብ ላዕለ መልአኮሙ እኩየ፤

ባለቃቸው ላይ ሕዝቡ ክፉ ነገር የተናገሩትን ሰማች፤

እስመ አንበዘት ነፍሶሙ በእንተ ዘኀልቀ ማይ፤

ውሀው ስላለቀ ሰውነታቸው አእምሮዋን አጥታለችና፤

ወሰምዐት ዮዲት ኵሎ ቃለ ዘይቤሎሙ ያዝያን፤

ዮዲት ያዝያን ያላቸውን ነገር ሰማች፤

ዘከመ መሐለ ሎሙ ከመ እምድኅረ ሐሙስ መዋዕል ያገብኡ ሀገሮሙ ለፋርስ፤

ካምስት ቀን በኋላ ሀገራቸውን ለፋርስ ሰዎች አሳልፈው ይሰጡ ዘንድ እንደማለላቸው ሰማች፤

፲፤ ወፈነወት ወጸውዓታ ለሐፃኒታ እንተ ተዐቅብ ኵሎ ንዋያ፤

ልካ ገንዘቧን የምትጠብቅ ሹሟን ጠራች፤

ወጸውዓቶሙ ለክብሪን ወለከርሚን ወለሊቃውንተ ሀገራ፤

የሀገሯን አለቆች፤ ክብሪንን ከርሚንን ጠራቻቸው፤

፲፩፤ ወመጽኡ ኀቤሃ፤

ወደሷ መጡ፤

ወትቤሎሙ ስምዑኒ መኳንንቲሆሙ ለእለ ይነብሩ ቤጤልዋ፤

በቤጤልዋ የምትኖሩ መኳንንቶች ስሙኝ አለቻቸው፤

እስመ ኢኮነ ጽድቀ ቃልክሙ ዘነበብክሙ በቅድመ ሕዝብ ዮም፤

ዛሬ በሕዝቡ ፊት የተናገራችሁት ነገር እውነት አይደለምና፤

ወአቀምክሙ በዝንቱ ዘነበብክሙ መሐላ ማዕከሌክሙ ወማዕከለ እግዚአብሔር፤

በዚህ በተናገራችሁት ነገር በእናንተና በእግዚአብሔር መካከል መሐላ አጸናችሁ፤

ከመ ታግብኡ ሀገረክሙ ለፀርክሙ ለእመ ኢረዳክሙ እግዚአብሔር በእላንቱ ሐሙስ መዋዕል፤

በነዚህ ባምስቱ ቀን እግዚአብሔር ባይረዳችሁ ሀገራችሁን ለጠላቶቻችሁ ትሠጡ ዘንድ በእናንተና በእግዚአብሔር መካከል መሐላን አጸናችሁ፤

፲፪፤ ወይእዜኒ ምንትኑ አንትሙ እለ ታሜክርዎ ለእግዚአብሔር ዮም በዛቲ ዕለት፤

በዚች ቀን እግዚአብሔርን የምትፈታተኑት እናንተ ምንድርናችሁ፤



ወቆምክሙ ማእከለ እግዚአብሔር ወማዕከለ ደቂቀ እጓለ እመሕያው፤

በሰውና በእግዚአብሔር መካከል በጠላትነት ለምን ትነሳላችሁ፤

፲፫፤ ወይእዜኒ የሐትት እግዚአብሔር ለሊሁ፤

አሁንም እሱ እግዚአብሔር መርምሮ ያውቃል፤

ወአንትሙሰ አልቦ ዘተአምሩ ለዝሉፉ፤

እናንተ ግን ፈጽማችሁ ምንም ምን የምትአውቁት የለም፤

፲፬፤ ዘእመቀ ልቡ ለእጓለ እመሕያው ኢተአምሩ፤

የሰውን የልቡናውን ጥልቅነት የማታወቁ፤

ወምክረ ሕሊናሁ ኢትሬእዩ፤

የሰውን የልቡናውን ምክር የማታውቁ፤

እፎ ለእግዚአብሔር ትትኃሠሥዎ ዘውእቱ ገብረ ዘንተ ኵሎ፤

ይህን ሁሉ የፈጠረ እግዚአብሔርን ለምን ትመረምሩታላችሁ፤

ወልበ ዚአሁ ትፈቅዱ ታእምሩ፤

የልቡናውን አሳብ ታውቁ ዘንድ እንደምን ትወዳላችሁ፤

ወምክረ ዚአሁ ተኃሥሡ ትርከቡ፤

የሱን ምክር ታገኙ ዘንድ እንደምን ትሻላችሁ?፤

ሐሰ ለክሙ አኃውየ፤

ወንድሞቼ ለናንት አገባባችሁ አይደለም፤

ኢታምዕዕዎ ለእግዚአብሔር አምላክነ፤

ፈጣሪያችን እግዚአብሔርን አታሳዝኑት፤

፲፭፤ እመኒ ፈቀደ ይርድአነ እስከ እማንቱ ሐሙስ መዋዕል፤

ዛሬ እስከ አምስት ቀን ድረስ ሊረዳን ቢወድ፤

ሥሉጥ ውእቱ በዘፈቀደ ያድኅነነ፤

ዛሬ ሊረዳን ባይወድ በሌላ ቀን ያጠፋን ዘንድ የሰለጠነ ነው፤ አንድም ኢፈቀደ ይላል፤ እስከ አምስት ቀን ድረስ ይረዳን ዘንድ ባይወድ፤ በሌላ ቀን ሊረዳን የሠለጠነ ነው፤

ወእመኒ በኵሉ መዋዕሊነ፤

ባለ በዘመናችን ሁሉ ይረዳን ዘንድ የሠለጠነ ነው፤

ወእመኒ ይሤርወነ በቅድመ ፀርነ፤

በጠላቶቻችን ፊት ያጠፋን ዘንድ ቢወድ የሠለጠነ ነው፤ አንድም ይሠውረነ ይላል፤ በጠላቶቻችን ፊት ከመከራ ይሠውረን ዘንድም የሠለጠነ ነው፤ አንድም ወእመኒ ፈቀደ ቢል፤ በዚህ በ፭ቱ ቀን ሊረዳንም ቢወድ ሥሉጥ ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፮፡ ወአንትሙሂ ዳዕሙ ኢታመክርዎ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ፣

ፈጣሪያችን እግዚአብሔርን እናንተ አትፈታተኑት እንጂ፤

እስመ አኮ እግዚአብሔር ከመ ሰብእ ዘይትሜአክ፣

እግዚአብሔር እንደ ሰው የሚበሳጭ አይደለምና፤

ወኢኮነ ከመ ወልደ እጓለ እመሕያው ዘይትቄየም፣

እንደ ሰው የሚቀየም አይደለምና፤

፲፯፤ ወባሕቱ ጽንሑ መድኃኒተ ዘእምኀቤሁ፣

ነገር ግን ከሱ የሚገኝ ሕይወትን ተስፋ አድርጉ፤

ወጸውዕዎ ይርድአነ ወይስምዓነ ቃለነ፣

ልመናችንን ሰምቶ ይረዳን ዘንድ ለምኑት፤

እመ ፈቀደ ያድኅነነ፣

ያድነን ዘንድ ከወደደ ያድነናል፤

፲፰፤ እስመ ኢተንሥአ በመዋዕሊነ፣

በዘመናችን ጣኦት የሚያመልክ አልተነሳምና፤

ወአልቦ ዮም፣

ዛሬም የለምና፤

ኢሕዝብ ወኢነገድ፣

ወገንም ሁኖ ሕዝብም ሁኖ፤

ወኢብሔር ወኢሀገር፣

ሀገርም ሁኖ፤ መንደርም ሁኖ፤

እምኔነ እለ ይሰግዱ ለአማልክት ግብረ እደ ሰብእ፣

የሰው እጅ ሥራ ለሚሆኑ ጣኦታት ከኛ ወገን የሚሰግድ የለምና፤

በከመ ኮነ በመዋዕለ ቀደምት፣

ባባቶቻችን ዘመን ጣኦት ያመልኩ እንደ ነበረ፤

፲፱፤ ወበእንቲአሁ ኮኑ ለኲናት ወለተበርብሮ አበዊነ፤

እሱን ስለተዉት ለጦር ለመበዝበዝ እንደሆኑ፤

ወወድቁ ዓቢየ ድቀተ እምቅድመ ፀሮሙ፣

በጠላቶቻቸው ፊት ድል እንደተነሱ፤

፳፤ ወንሕነሰ አልብነ ባዕድ አምላክ እንበሌሁ፣

እኛ ግን ከሱ በቀር የምናመልከው የለምና ያድነናል፤

ወቦቱ ንትአመን፣

በሱ እናምናለን፤

ከመ ኢይትዐወረነ አዝማዲነ፣

ወገኖቻችንን ቸል እንዳይል፤ አንድም እስመ ኢይትዔወር ቢል ከኛ አንዱንም አንዱን ቸል አይለንምና፣ እመ ቦቱ ንትአመን ሳለው፤



፳፩፡ እስመ ከመ ነሥአነ ከማሁ ገብረ ይሁዳ፣

በረድኤት እንዳቀረበን ጊዜ ይሁዳ አድርጓልና ማለት ጣዖት ኣላመለክንምና፤ አንድም ኢነሥአነ በረድኤት እንዳቀረበን ጊዜ ይሁዳ አድርጓልና፡ አንድም እስመ ከመ አመ ኮነነ ከማሁ ገብረ ኮሉ ይሁዳ፣ አባት እንደሆነን ጊዜ ይሁዳ አድር ጓልና፤ አንድም ኢኮነነ ይላል፤ አባት እንዳልሆነን ጊዜ ይሁዳ አድርጓልና፤

ወተበርበረ ኮሉ ቅድሳቲነ፣

ንዋየ ቅድሳቱ እንደተማረከ ጊዜ ኣላደረገምና፤

ወይትኃሠሦሙ በእንተ ርኵሶሙ እምነ አፉሆሙ፣

ካፋቸው በወጣ ኃጢአት እንደ ተመረመረቸው ጊዜ ኣላደረ ገምና፤

፳፪፤ ወተቀትሉ አኃዊነ፣

ወንድሞቻችን እንደ ሞቱ ጊዜ ኣላደረገምና፤

ወተፄወወ ብሔርነ፣

ሀገራችን እንደጠፋች ጊዜ ኣላደረገምና፤

ወማሰነ ርስትነ ዘይገብእ ውስተ ርስትነ፣

ወደርስታችን የሚመለስ ርስታችን እንደጠፋበት ጊዜ ኣላደረገምና፤ አንድም ወደርስታችን የሚመለስ ሰው ጠፋ፤

ወውስተ አሕዛብ ኀበ ተቀነይነ ህየ ንከውን ዕቁፋነ፣

በገዙን በአሕዛብ ዘንድ በመከራ እንደተሰነካከልንበት ጊዜ ኣላደረገምና ንቁፋን ቢል የተነቀፍን እንሆናለን፤

ወማዩራነ በቅድመ እለ ያጠርዩነ፣

በገዙን ሰዎች ፊት እንደተገዳደሩብን ጊዜ ኣላደረገምና ኀዩያነ ቢል ቸል የምንባል እንሆናለን፤ እዩያ ነቢል በካና ፈዛዛ አውታታ እንሆናለን፤

፳፫፤ እንበለ አኰቴት ይከውን ቅኔነ፣

መገዛታችን ያለ ምስጋና ይሆናልና፤

እስመ ትሕትናነ ርእየ እግዚአብሔር አምላክነ፣

ዛሬ ግን ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ትሕትናችንን አይቷልና፤

፳፬፡ ወይእዜኒ አኃዊነ ንግርዎሙ ለቢጽነ፤

አሁንም ወንድሞቻችን ለባልንጀሮቻችን ንገሯቸው፤ እነሱን በተፈታተኗቸው ጊዜ፤

እስመ ኪያነ ያጸምዑ፤

እኛን ይሰማሉና፤

www.ethiopianorthodox.org

ውነቤነ ተሰቅለ ነፍሰሙ፤

ልቡናቸው ከኛ ጋራ አንድ ሁኗልና፤

ወቤተ መቅደስኒ ወምሥዋዕኒ ብነ ያሰምክ፤

ቤተ መቅደስም ምሥዋዕም በኛ ይጠናልና፤

፳፭፤ ወበዝንቱ ኵሉ ናእኵቶ ለእግዚአብሔር፤

በዚህ ሁሉ ፈጣሪያችን እግዚአብሔርን እናመስግነው፤

ዘያሜክረነ በከመ አበዊነ፤

አባቶቻችንን ልቡናቸውን ሳያውቅ የተፈታተናቸው እንዳይደለ፤ ልቡናችንን ሳያውቅ የተፈታተነን አይደለም፤

፳፮፤ ተዘከሩ ኵሎ ዘገብረ ምስለ አብርሃም፤

ከአብርሃም ጋራ ያደረገውን አስቡ፤ ልጅህን ሠዋልኝ ያለውን አይሆንም እንዳይለው አውቆ እንደሆነ፤

ወመጠነ አመከሮ ለይስሐቅ፤

ይስሐቅን የተፈታተነው ሳያውቅ እንዳይደለ፤

ወበከመ ኮነ ለያዕቆብ በመስጴጦምያ ዘሶርያ እንዘ ይርኢ አባግዒሁ ለላባ እኁሃ ለእሙ፤
የናቱን ወንድም የላባን በጎች ሲጠብቅ የሶርያ አውራጃ በምትሆን በመስጴጦምያ ያዕቆብን የተፈታተነው ልቡናውን ሳያውቅ እንዳይደለ አስቡ፤

፳፯፤ እስመ አኮ አመ አምከሮሙ ለእልክቱ ፈተነ ልበሙ፤

እነሱን በተፈታተናቸው ጊዜ ልቡናቸውን ሳያውቅ የተፈታተናቸው አይደለምና፤ አንድም በመከራ በተፈታተ ናቸው ጊዜ ያለረብህ የፈተናቸው አይደለምና፤

ወለነኒ አኮ ዘገፍዓነ፤

እኛንም ሳያውቅ ያለጥቅም የተፈታተነን አይደለምና፤

አላ ከመ ይምሐሮሙ ለእለ ይቀርብዎ ይቀሥፎሙ እግዚአብሔር፤

የቀረቡትን ሰዎች ይቅር ይላቸው ዘንድ እግዚአብሔር በመከራ ይገርፋቸዋል እንጂ፤

፳፰፤ ወይቤላ ዖዝያን ኵሎ ዘተናገርኪ በሠናይ ልብ ነበብኪ፤

የተናገርሽውን ሁሉ በቀና ልብ ተናገርሽ፤

ወአልቦ ዘይትቃወሞ ለቃልኪ፤

ነገርሽን የሚቃወመው የለም፤

፳፱፤ እስመ ኢኮነ እምዮም ዘተሰምዐ ጥበብኪ፤

ጥበብሽ ከዛሬ ጀምሮ የተሰማ አይደለምና፤



አላ እምነ ቀዳሚ መዋዕልኪ አእመረ ኵሉ ሰብእ ጥበበኪ፤

ከቀደመ ዘመንሽ ጀምሮ ሰው ሁሉ ጥበብሽን አወቀ እንጂ፤

እስመ ቡሩክ ውእቱ ፍጥረተ ልብኪ፤

የልቡናሽ ዕውቀት ብዙ ነውና፤

፴፤ ወባሕቱ እስመ ፈድፋደ ጸምዑ ሕዝብ አገበሩ ንግበር ዘከመ ይቤሉነ፤

ነገር ግን ሕዝቡ እጅግ ተጠምተዋልና ያሉንን እናደርግ ዘንድ ግድ አሉን፤

ወአምጽኡ ላዕሌነ መሐላ ዘኢንክል ክሒደ፤

ማፍረስ የማይቻለንን መሐላ አመጡብን፤ አንድም ክሂደ ይላል፤ አሌ ማለት የማይቻለንን አመጡብን፤

፴፩፤ ወይእዜኒ ጸልዩ ለነ እስመ ብእሲት ፈራሂተ እግዚአብሔር አንቲ፤

አሁንም አንቺ እግዚአብሔርን የምትፈሪ የምታመልኪ ነሽና ለምኝልን፤

ወይፌኑ እግዚአብሔር ዝናመ፤

እግዚአብሔር ዝናምን ያዘንምልናል፤

ወይምላዕ ዓዘ ቃቲነ፤

ዓዘቅቱም ውሀውን ይመላል፤

ወኢንጸማዕ እንከ፤

ከዚያ በኋላ አንጠማም፤

፴፪፤ ወትቤሎሙ ዮዲት ስምዑኒ፤

ዮዲት ስሙኝ አለቻቸው፤

ወእገብር ግብረ ዘይትነገር ለትውልደ ትውልድ፤

ለልጅ ልጅ ዘመን የሚደረግ ሥራ እሠራላችኋለሁ፤

፴፫፤ ወአንትሙሰ ቁሙ ኀበ አንቀጽ በዛቲ ሌሊት፤

እናንት ግን በዚች ሌሊት ከበሩ ቁሙ፤

ወእወጽእ አነ ምስለ ቀኁልዔትየ፤

እኔ ከገረዴ ጋራ እወጣለሁ፤

ወበእልክቱ መዋዕል እለ ትብሉ ያገብእ ሀገረ ለፀርነ፤

ሀገራችንን ለጠላታችን እንሰጣለን ባላችኋቸው በነዚህ ባምስቱ ቀኖች፤

ይረድአነ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል በእዴየ፤

የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር በኔ እጅ ይረዳናል፤ አንድም በኔ ጸሎት ይረዳናል፤

፴፬፤ ወአንትሙሰ ኢትሕትቱኒ ዘእገብር፤

እናንተ ግን የማደርገውን አትመርምሩኝ፤

www.ethiopianorthodox.org

እስመ ኢይነግረክሙ እስከ የሐልቅ ዘእገብር፤

የማደርገው ነገር እስኪፈጸም አልነግራችሁምና፡

፲፫፡ ወይቤልዋ ዖዝያን ወመላእክቲሆሙ ሑሪ በሰላም፤

ዖዝያን አለቆቻቸው በሰላም በፍቅር ሂጂ አሏት፡

ወእግዚአብሔር ምስሌኪ፤

እግዚአብሔር በረድኤት ካንቺ ጋራ ይኑር፡

ወቅድሜኪ ይትቤቀል ፀረነ፤

ጠላቶቻችንን በፊትሽ ተበቅሎ ያጥፉልን፡

፲፬፡ ወገብኡ ወሖሩ ኀበ ቢጸሙ፤

ተመልሰው ወደ ባልንጀሮቻቸው ሂዱ።

ወአብአት ቍርባነ ውስተ ቤተ እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም ለዝሉፉ፤

ቍርባንን ፈጽማ በኢየሩሳሌም ወደቤተ እ ግ ዚ አ ብ ሔ ር አገባች፤ አ ግ ቡ ል ኝ ብላ ስለሰጠች ነው፡

ዕጣነ ዘይእቲ አሚር፤

የዚያች ቀን ዕጣን አቀረበች፡

ወጸርሐት በዓቢይ ቃል ውእተ አሚረ፤

ያን ጊዜ ቃሏን አስምታ ጮኸች፡

፪፡ ወትቤ ዮዲት እግዚኦ አምላከ አቡየ ስምዓኒ ዘመጠውኮ ኵናተ ለስምዖን ውስተ እዴሁ፤

ዮዲት እንዲህ አለች፤ ለስምዖን ለሌዊ ኃይል ሥልጣን በእጁ የሰጠኸው ያባቴ ፈጣሪ አቤቱ ስማኝ፡

ለተበቅሎ ፀር እለ ሰበሩ ማኅፀነ ወአርኰሱ ድንግለ፤

የዲናን ማኅፀን ያረከሱ ድንግሊቱን ያጐሰቈሉ ሴኬምና ኤሞርን ለመበቀል ለስምዖን ሰይፍ የሰጠኸው አቤቱ ልመናዬን ስማኝ፡

ወሰለቡ፤

የሰውን ብልት የሰለቡ፡ አንድም የሰውን ልብስ የሰለቡ፡

## ምዕራፍ ፲፮

### ጉባዔ

፩፡ ወዮዲትሰ ወድቀት በገጸ ውስተ ምድር፤

ዮዲት ግን በግምባሯ ፍግም ብላ ከምድር ወደቀች፡

ወወደየት ሐመደ ውስተ ርእሳ፤

በራሷ ላይ አመድ ነሰነሰች፡

ወአርአየት ሠቀ ዘትለብስ፡

የለበሰችውን ማቅ ለእግዚአብሔር አሳየች፡



ወገመኑ ማኅፀነ በትዕይንት እኮ ከመዝ፤

የዲናን ማኅፀን ያጐሰቈሉ በከተማ ብቻ አይደለም፡

ወበኵለሂ፤

በሁሉም ነው እንጂ እንዲህ እንዲህ የሚያደርጉ፤ ሰብአ ሰቂማን ለመበቀል ለስምዖን ለሌዊ ሥልጣን የሰጠህ አቤቱ፡ አንድም እለ ሰዐሩ ማኅፀነ፤ ማኅፀንን፤ ያረከሱ ወአርኰሱ፤ ድንግልናን ያረከሱ፡ ወሰለቡ፤ ብልትን የሰለቡ፡ አንድም ልብስን የገፈፉ፤ ወገመኑ በትዕይንት፤ በከተማ ያረከሱ፤ በትዕይርት ቢል በመገዳደር ያረከሱ፤ ወበኵለሂ እኮ ከመዝ፤ እንዲህም ማድረጋቸው በሀገሩ ሁሉ ነው እንጂ፤ በከተማ ብቻ አይደለም፡ ትች ነው፡ እንዲህ እንዲህ የሚያደርጉ ሰብአ ከነዓንን ለመበቀል ለኢያሱ ኃይል ሥልጣን የሰጠህ አቤቱ ስማኝ፡

፫፡ ወእሙንቱሰ ገብሩ፤

እነሱ ግን ፈቃዳቸውን አደረጉ፡

እስመ ወሀብኮሙ ኃይለ ለመላእክቲሆሙ ውስተ ቀትል፤

በሰልፍ ጊዜ ለአለቆቻቸው ለነናቡከደነፆር ኃይል ሰጥተሃቸዋልና፡

ወምስካብ ተነጽፈ በደመ እለ ተቀትሉ አግብርት፡

መኝታቸውም የሞቱ ሰዎች ደም ተነጥፎበታልና፡

ጽኑዓን ወኃያላን እመናብርቲሆሙ፤

ኃያላን ጽኑዓን የሆኑ ሰዎች ከዙፋናቸው ወድቀዋልና፡

፬፡ ወተሄወዋ አንስቲያሆሙ ወአዋልዲሆሙ፤

ልጆቻቸው ሚስቶቻቸው ተማርከዋልና፡

ወተካፈሉ ምሕርካሆሙ ለውሉድ እለ ፍቁራን በኀቤከ፤

በአንተ ዘንድ የተወደዱ የልጆችህን ምርኮ ተካፍለዋልና፡

እለ ቀንዑ ቅንዓተከ፤

ለአምላክነትህ የቀኑ፡

ወአስቈረሩ ርኩሰ ደሞሙ፤

የረከሰ ደማቸውን ተጸይፈዋልና፡

ወጸውዑከ ከመ ትርድኦሙ፤

ትረዳቸው ዘንድ ጠርተውሃል ለምነውሃልና፡

እግዚኦ አምላከ ዚአየ ስምዓኒ ሊተ ለመበለት፤

እንዲህ እንዲህ የምታደርግ አቤቱ የእኔ የድኃዪቱን ልመናዬን ስማኝ፡

www.ethiopianorthodox.org

፳፡ እስመ አንተ ገበርከ ዘቅድመ ዝንቱ፤

ከባቢሎን አስቀድሞ የግብፃውያንን ጥፋት አንተ አድርገሃልና፤

ወዘእልኩቱ፤

የነሰናክሬምንም ጥፋት፤

ወዘእምድኅሬሁ፤

ከሰናክሬም በኋላ የባቢሎንን፤

ወዘይእዜኒ፤

የሆሎፎርኒስን፤

ወዘይመጽእኒ፤

የጽርዓውያንን ጥፋት፤

አእመርከ፤

አውቀሃልና፤ አንድም ከባቢሎን አስቀድሞ የሚሆን የሰናክሬምን ጥፋት፤

ወዘእልኩቱ፤

የግብፃውያንን፤

ወዘእምድኅሬሁ፤

የሰናክሬምን፤

ወዘይእዜ፤

የሆሎፎርኒስን፤

ወዘይመጽእኒ፤

የጽርዓውያንን ጥፋት አውቀህ አድርገሃልና፤

ወኮነ በዘአእመርከ፤

አንተ እንዳወቅህ ሆነ፤

፳፩፡ ወርቱዕ ምክርከ፤

ምክርህም የቀና ነው፤

ወይቤሉከ ናሁ መጻእነ፤

እነሆ መጣህ አሉህ፤

እስመ ድልው ኵሉ ፍናዊከ፤

ሥራህ ሁሉ የተዘጋጀ ነውና፤

ወኵነኔከኒ በዘአእመርከ ኩነንከ፤

ፍርድህንም አንተ ባወቅህ ገንዘብ ፈረድህ፤

፳፪፡ እስመ ናሁ ፋርስ በዝኑ ምስለ ኃይሎሙ፤

የፋርስ ሰዎች ከሠራዊታቸው ጋራ በዝተዋልና፤

ወተለዐሉ ዲበ አፍራሲሆሙ፤

በፈረሶቻቸው ላይ ተቀምጠዋልና፤

ወመስተፅዕናን ተሐየሉ በመዝራዕቶሙ፤

በፈረስ የተቀመጡ ሰዎች በሥልጣናቸው ተበረታትተዋልና፤

አጋርያን ተአመኑ በድርየሙ፤

አርበኞችም በጥሩራቸው ታምነዋልና፤ አንድም በጽንየሙ ይላል፤ በኃይላቸው ታምነዋልና፤

በኲናቶሙ ወበቀስቶሙ ወበሞጸፎሙ፤

በጦራቸው፤ በቀስታቸው በድል ነጐዳቸው ታምነዋልና፤

ዘዮዲት ምዕ. ፱ 47

ኢያእመሩከ ከመ አንተ እግዚአብሔር ዘትቀጠቅጥ ፀባኢተ፤

አርበኞውን ሁሉ የምታጠፋ ፈጣሪ አንተ እንደሆንክ አላወቁህም፤

ወእግዚእ ስምከ፤

ስምህም ገዥ እንደሆንህ አላወቁም፤

፳፫፡ ወአንተ ነሣህከሙ ምስለ ኃይሎሙ በኃይልከ፤

አንተ በከሀሊነትህ ከሠራዊቶቻቸው ጋራ አጠፋሃቸው፤

ወአስጥሞሙ በመዓትከ ለጽንዖሙ፤

አርበኞቻቸውን በባሕረ መከራ አሠጥማቸው፤

እስመ መከሩ ያርኵሱ መቅደስከ፤

ቤተ መቅደስህን ያጐስቁሉ ዘንድ መክረዋልና፤

ወያገምኑ ደብተራ ምዕራፈ ስብሐተ ስምከ፤

የስምህ ምስጋና ማደሪያ ደብተራ ኦሪትን ያሳድፉ ዘንድ መክረዋልና፤

ወነሠቱ በኃጺን አቅርንተ ምሥዋዒከ፤

አቅርንተ ምሥዋዑንም በድጅኖ አፍርሰዋልና፤

፳፬፡ ወርኢ ትዕቢቶሙ ወፈኑ መዓትከ ውስተ ርእሶሙ፤

ትዕቢታቸውን እይተህ መዓቱን በራሳቸው ላይ አምጣ፤

ወሀብ ኃይለ በእዴየ ሊተ ለመበለት፤

ደካማ በምሆን በኔ እጅ ኃይልን ግለፅ፤

፳፭፡ በዘሐለይኩ አትትል ገብረ፤

ሠራዊቱን አጠፋ ዘንድ፤

ወመልእከ፤

ናቡከደነፆርን፤

ወቀልዔሁ፤

ሆሎፎርኒስን፤

በአስፍጦ ከናፍር፤

በማታለል አጠፋው ዘንድ ባሰብሁት ገንዘብ፤

ወደምስስ ቆሞሙ በእደ ብእሲት፤

ሠራዊታቸውን በእኔ እጅ አጥፋ፤

፳፮፡ እስመ ኢኮነ ለብዙኃን ጽንዕከ፤

ኃይልህ መደረጉ ለጽኑዓን ቢሆን ደግ አይደለምና፤

ወአኮ ለጽኑዓን ኃይልከ፤

ኃይልህም ለብርቱዎች ቢሆን ደግ አይደለምና፤ ለደካሞች ቢሆን ነው እንጂ፤ አንድም ኃይልህ መደረጉ ለጥቂቶች ነው እንጂ ለብዙዎች አይደለም፤ ለደካሞች ነው እንጂ ለብርቱዎች አይደለምና፤

አትሕቶሙ እግዚእ፤

አቤቱ አዋርዳቸው፤

www.ethiopianorthodox.org

እስመ ረዳኢሆሙ አንተ ለውኁዳን ወረዳኢሆሙ ለድኩማን፤

የጥቂቶችም፣ የደካሞችም ረዳታቸው አንተ ነህና፡

ወመድኅኖሙ አንተ ለኅጉላን፤

የጠፉትንም የምታድናቸው አንተ ነህና፡

ወማሕየዊሆሙ አንተ ለትቡዓን፤

ተስፋ ያጡትን የምታድና ቸው አንተ ነህና፡

፲፪፡ እወ እግዚእ አምላከ አቡየ፤

አቤቱ ያባቶቼ ፈጣሪ እውነት ነው፡

ወአምላከ ርስቶሙ ለእስራኤል፤

የእስራኤል የማደሪያቸው ፈጣሪ፡

እግዚአ ሰማያት ወምድር፤

ሰማይንም ምድርንም የፈ ጠርህ ጌታ አንተ ነህ፡

ፈጣሬ ማይ፤

ውሀውን የፈጠርህ አንተ ነህ፡ ውሀውን ይዘውባቸው ነበረና ፈጣሬ ማይ አለች፡ አንድም ፈጣሬ ሰማይ ይላል፡

ንጉሥ አንተ ለኵሉ ተግባርከ፤

ለፈጠርኸው ሁሉ ፍጥረት ንጉሥ አንተ ነህ፡

አንተ ስማዕ ጸሎትየ፤

ንጉሥ የምትሆን አንተ ልመና ዬን ስማኝ፡

፲፫፡ ወረስዮ ለቃልየ ከመ ያስህቶሙ ወያቍስሎሙ ወይቅትሎሙ ለዐረ ሕግከ፤

ልመናዬን የሕግህ ደመኞችን ያጠፋ ዘንድ እንዲያጠፋ አድርገው፡

ወቤተ መቅደስከ፤

ወዐረ ቤተ መቅደስከ ሲል ነው፡ የቤተ መቅደስን ጠላቶች፡

ወርእሳ ለጽዮን፤

ወዐረ ርእሳ ሲል ነው፡ የጽዮንን ጠላቶች፡

ወቤተ ንብረቶሙ ለደቂቅከ፤

ወዐረ ቤተ ንብረቶሙ ሲል ነው፡ ልጆችህ የሚኖሩበት የቤታቸውን ደመኞች ያጠፋ ዘንድ፡

እለ መከሩ ዕሡባተ፤

ጭንቅ ነገርን የመከሩ ጠላቶችህን ያጠፋ ዘንድ፡

፲፬፡ ወግበር ለኵሉ ሕዝብከ ከመ ያእምሩ ወይጠይቁ ከመ አንተ ውእቱ እግዚአብሔር እግዚአ ኵሉ፤

የሁሉ ጌታ ፈጣሪ አንተ እንደ ሆንህ ያውቁ ይረዱ ዘንድ ለወገኖችህ አድርግላቸው፡

ወአልቦ ባዕድ ዘያፀንዖሙ ለዘመደ እሥራኤል ዘእንበሌከ፤

ካንተ በቀር የእሥራኤልን ወገኖች የሚያፀናቸው የለም።



# ምዕራፍ ፲

፩፡ ወእምዝ ሶበ አኅለቀት ጸሪሐ ኀበ እግዚአብሔር አምላከ እሥራኤል፡

ከዚህ በኋላ ከእስራኤል ፈጣሪ ከእግዚአብሔር ልመናዋን በፈጸመች ጊዜ፡

፪፡ ወፈጺማ ዘንተ ኵሎ ነገረ ተንሥአት እምነበ ወድቀት፡

ይህን ሁሉ ነገር ፈጽማ ከወደቀችበት ተነሣች፡

ወጸውአታ ለወለታ፤

ልጇን ብላቴናዋን ጠራቻት፡

ወወረደት ውስተ ቤታ ኀበ ትነብር በመዋዕለ ሰንበታት፤

ቅዳም ቅዳም ወደምትቀመጥባት ቤታ ወረደች፡

ወአመ በዓላት፤

በበዓለ ሠዊት፣ በበዐለ መጸለት፡ በዐለ ፋሲካ ወደምትቀመጥበት ሄደች፡

፫፡ ወአሰሰለት ሠቀ ዘትለብስ፤

የለበሰችውን ማቅ አውጥታ፡

ወለብሰት ልብሰ መበለታ፡

የድኅነቷን ልብስ ለበሰች፡

ወተሐፅበት ሥጋሃ በማይ፡

ሰውነቷን በውሃ ታጠበች፡

ወተቀብዓት እፍረተ፤

ሽቱውን ተቀባች፡

ወተነፍቀት ስእርተ ርዕሳ፡

ጠጉሯን ከፍላ ከፍላ ተሠራች፡

ወተሠርገወት ባዝግናሃ፤

ዝርግፏን የወርቅ ማርዳዋን አጌጠች፡

ወእምዝ ለብሰት አልባሰ ትፍሥሕታ ዘትለብስ አመሕያው ምታ ምናሴ፡

ባሏ ምናሴ ደኅና ሳለ የምትለ ብሰውን ልብስ ለበሰች፡

፬፡ ወተሰእነት አሣዕኒሃ፤

ጫማዋን አደረገች፡

ወተሠርገወት፤

አጌጠች፡

ወአውቃፈ፤

አምባሯን፡

ወኅልቀታተ፤

ቀለበቷን፡

ወአእኑገ፤

ኑሮውን መንደልቶውን አደረ ገች፡

ወኵሎ ሠርጓ፤

ጌጧን ሁሉ አደረገች፡

ወተሠነየት ጥቀ እስከ ታስሕት ዓይኖሙ ለኵሉ ዕደው እለ ይሬእይዋ፡

የሚያይዋትን ሰዎች ሁሉ ዓይን እስክታስት ድረስ እጅግ አጌጠች፡

www.ethiopianorthodox.org

፭፡ ወወሀበታ ለወለታ ትዑር ግብነተ ወይን፤

አንቋሊቱን ትሸከም ዘንድ፡ አንድም ግንባተ ወይን ይላል፤ ፊቀኑን ትሸከም ዘንድ ለልጇ ሠጠቻት፡

ወግምዔ ቅብዕ፤

ዘይት ያለበትን ማሠሮ፡

ወመልዓት ዕፍነታ ጥሕነ፤

ስልቋን በአቁማዳ መልታ፡

ወበለስ፤

በለሱን፡

ወኅብስተ ስንዳሌ፤

የስንዴውን ዳቦ፡

ወአስነቀት ኵሎ ንዋያ፤

ገንዘቧን ሁሉ አስያዘች፡

ወአያረታ፤

አሸከመቻት፡ አንድም ሐሰወት የሚል አብነት ይገኛል፡ ተበተበች፤ አነገተች፡

፮፡ ወሖረት መንገለ ገጸ ቤጤልዋ፤

ወደቤጤልዋ ሄደች፡

ወረከበቶሙ ይቀውሙ ህየ ለዖዝያን ወለሊቃውንተ ሀገር ከብራም ወከርሚን፤

የሀገር አለቆች ከብራምን ከርሚንን ዖዝያንን ከዚያ ቆመው አገኘቻቸው፡

፯፡ ወሶበ ይሬእይዋ ከመ ኮነ ተወለጠ ገጻ፤

ባይዋት ጊዜ ባዕድ አስመሰሏት፡ አንድም ነኪር ገጸ ልዩ የሆነ ፊቷን ባዩ ጊዜ ባዕድ አስመሰሏት፡

ወትትዓፀፍ አልባሲሃ፤

መጐናጸፊያዋን ባዩ ጊዜ፡

ወብዙኀተ ደመ እምነ ስና ፈድፋደ ጥቀ፤

ከመልኳ ደም ግባት የተነሣ እጅግ አደነቁ፡

፰፡ ወይቤልዋ የሀብኪ አምላከ እስራኤል ሞገሰ ትግበሪ ዘሐለይኪ ለጽንዖሙ ለደቂቀ እስራኤል ወለኢየሩሳሌም፤

ልጆችሽንና ኢየሩሳሌምን ለማጽናት ያሰብሽውን ታደርጊ ዘንድ የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር ባልሟልነትን ይስጥሽ አሏት፡

፱፡ ወትቤሎሙ አኀዙ ሊተ ዘያርኅዉኒ አንቀፀ ሀገር፡

የሀገሩን በር የሚከፍትልኝ እዘዙልኝ አለቻቸው፡

ወእጸእ እግበር ዘንተ ቃለ ዘተናገርኩ ምስሌክሙ፤

ከናንተ ጋራ የተናገርሁትን ነገር አደርግ ዘንድ ልውጣ፡

ወአዘዝዎሙ ለመሐዛት ያርኅዉዋ ዘከመ ትቤ፤

እሷ እንደተናገረች ይከፍቱላት ዘንድ ጐልማሶችን አዘዟቸው፡



፲፣ ወገብሩ ከማሁ፤

እንዳዘዟቸው አደረጉ፡

ወወፅአት ዮዲት፤

ዮዲት ወጣች፡

ወቁልዔታ ምስሌሃ፤

ገረዷም ከሷ ጋራ ወጣች፡

ወይኔጽርዋ ሰብአ ሀገር እስከ ወረደት እምደብር ወእስከ ኀለፈት እምነ ዓውሎኒ፡

ካምባው እስክትወርድ ድረስ ከዓውሎኒም እስክታልፍ ድረስ በሀገር ያሉ ሰዎች ያይዋት ነበር፡

ወኢርእይዋ እንከ፤

ከዚያ ወዲያ አላዩዋትም፡

፲፩፡ ወሖረት እንተ ዓውሎኒ ርቱዓ፤

ወደዓውሎኒ አቅንታ ሄደች፡

ወረከብዋ መዓቅበ ፋርስ፤

የፋርስ ዘበኞች አገኟት፡

፲፪፡ ወአኀዝዋ ወሐተትዋ፡

ይዘው መረመሯት፡

ወይቤልዋ መኑ አንቲ፤

አንቺ ማነሽ አሏት፡

ወአይቴ ተሐውሪ፤

ወዴት ትሄጃለሽ፡

ወእምአይቴ መጻእኪ፤

ከወዴት መጣሽ አሏት፡

ወትቤሎሙ ወለቶሙ አነ ለዕብራውያን፤

የዕብራውያን ልጅ ነኝ አለቻቸው፡

ወተኀጣዕኩ እምኔሆሙ ሶበ ፈቀዱ ያግብኡ ለከሙ ሀገሮሙ፤

ሀገራቸውን ለናንተ ይሰጡ ዘንድ በወደዱ ጊዜ፡

፲፫፡ አነ አቅደምኩ መጺአ ኀቤሁ ለሆሎፎርኒስ መልአከ ኃይልክሙ፡

የሠራዊቶቻችሁ አለቃ ወደ ሚሆን ወደ ሆሎፎርኒስ እኔ አስቀድሜ መጣሁ፡

ከመ እንግር ቃለ ጽድቅ፡

እውነተኛ ነገር እነግረው ዘንድ፡

ወአርእዮ ፍኖተ እንተ ባቲ ተሐውሩ፡

የምትሄዱበትን ጎዳና አሳየው ዘንድ፡

ወታስተጋብኡ ኵሎ ደወሎሙ፡

አውራጃቸውን ሁሉ እጅ ታደርጉ ዘንድ፡

ወአልቦ ዘይቈስል እምነ ሰብእክሙ ወኢአሐቲ ነፍስ፤

ከሰውነታችሁ አንድ ሰው ስንኳ የሚቆስል የለም፡

፲፬፡ ወሶበ ሰምዑ እሙንቱ ዕደው ቃላ፡

እነዚያ ሰዎች ቃሏን በሰሙ ጊዜ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወርእየዋ ገጻ፣

ፊቷን ባዩዋት ጊዜ፣

ወመድምም ውእቱ ስነ ፊድፋደ በቅድሜሆሙ፣

ዕንዕ የሚሆን ደም ግቧቷን ባዩዋት ጊዜ፣

፲፭፡ ወይቤልዋ አሕየውኪ ነፍስኪ ዘአፍጠንኪ ወሪደ ኀበ እግዚእነ፣

ወደጌታሽ ፈጥነሽ የመጣሽ አንቺ ሰውነትሽን አዳንሽ አሏት፣

ወይእዜኒ ሑሪ ኀበ ደብተራሁ፣

አሁንም ወደድንኳኑ ሂጂ፣

ወንፌኑ ምስሌኪ እምኔነ እለ ያበጽሑኪ ኀቤሁ፣

ወደሱ የሚያደርሱሽ ካንች ጋራ ከኛ ሰዎች እንሰዳለን፣

፲፮፡ ወሶበ ቆምኪ ቅድሜሁ ኢይፍራህ ልብኪ፣

ከፊቱም በቆምሽ ጊዜ ልቡናሽ አይፍራብሽ፣

ዳዕሙ ዜንዊዮ ዘንተ ነገረኪ፣

ይህን ነገርሽን ደፍረሽ ንገሪው እንጂ፣

ወይሜኒ ላዕሌኪ፣

ለአንቺ በጐ ነገር ያደርግልሻል፣

፲፯፡ ውነረዩ እምኔሆሙ ምእተ ብእሴ፣

ከነዚያ መቶ ሰዎች መረጡ፣

ወነድእዋ ምስለ ወለታ፣

ከገረዷ ጋራ ይዘዋት ሄዱ፣

ወአብጽሕዋ ኀበ ሆሎፎርኒስ እስከ ያየድእዎ በእንቲአሃ፣

የሷን ነገር እስኪነግሩት ድረስ ከሆሎፎርኒስ ዘንድ አደረሷት፣

፲፰፡ ወአንከሩ ስና፣

ደም ግቧቷን አደነቁ፣

ወተደሙ እምደቂቀ እስራኤል በእንቲአሃ፣

ከእስራኤል ልጆች የተነሣ የሷን ነገር አደነቁ፣

ወተበሀሉ በበይናቲሆሙ፣

እርስ በርሳቸው እንዲህ ተባባሉ፣

መኑ ዘይሜንኖሙ ለእሉ ሕዝብ እንዘ በውስቴቶሙ ዘከመዝ አንስት፣

እንዲህ ያሉም መልከ መልካሞች ሴቶች ሳሏቸው ንቆ የሚተዋቸው ማነው ማለት ወንዱ ወንዱን ገድሎ ሴቶችን የማያገባ ማነው፣

እስመ ኢኮነ ሠናየ ያትርፉ እምኔሆሙ ፩ደ ብእሴ፣

ከነዚያ አንድ ሰው ሊያስቀሩ አይገባምና፣ አንድም ሳያጋቡት ቢቀር አገባብ አይደለምና መኑ ዘይሜንኖሙ ሳለው፣ አንድም እስመ ኢኮነ እምኔሆሙ ይትርፍ ፩ደ ብእሴ ይላል፣ ሳይገድሉት ሳያገቡት ቢቀር አግባብ አይደለምና መኑ ዘይሜንኖሙ ሳለው፣



ወእለሰ ይክሉ ኀዲገ ተጠቢቦሙ እምነ ኵሉ ምድር፣

መግደል ሲቻላቸው የተዋቸው ለብልሀታቸው ነው፣ እንጋባቸዋለን ብለው፣ አንድም ተመኑ ዘይሜንኖሙ ብለህ መልስ፣ እንዲህ ያሉ መልከ መልካም ሴቶች ሳሏቸው ንቆ የሚተዋቸው ማነው የማያገባቸው? አንድ ሳይቀር ሊያገቧቸው ይገባልና መግደል ሲቻላቸው የተዋቸውም እንጋባቸዋለን ብለው ለብልሀታቸው ነው፣

፲፱፡ ወወፅኡ እለ ይነብሩ ኀበ ሆሎፎርኒስ ወኵሉ ደቂቁ፣

ከሆሎፎርኒስ ዘንድ የተቀመጡ ልጆችም ሁሉ ወጥተው፣

ወአብእዋ ውስተ ደብተራሁ፣

ወደ ድንኳኑ አገቧት፣

፳፡ ወሆሎፎርኒስ ይነውም ውስተ ምስካቡ ፊላሶ፣

ሆሎፎርኒስም ድልድል ደልድሎ ጉዝጓዝ ጐዝጉዞ ተኝቶ ነበር ፍላስን ቢል እልፍኝ ድንኳን፣ አንድም አጻራሽ ድንኳን፣

ዘርጉፍ በልብሰ ሜላት ዘወርቅ፣

ወርቀ ዘቦ ባለበት በነጭ ሐር ያጌጠ፣

ወመረግድ፣

መረግድ የሚባል ዕንቍ፣

ወእንቍ ዘብዙኅ ሤጡ፣

ዋጋው ብዙ የሚሆን እንቍ በውስጡ አለበት፣

፳፩፡ ወነገርዎ በእንቲአሃ፣

የሷን ነገር ነገሩት፣

ወወፅአ ገብጋቦ፣

ገብጋቦ ወጣ የሰው ስም ነው፣ አንድም ፊላሶንን እልፍኝ ድንኳን ያሉ እንደሆነ ወደ አጻራሽ ድንኳን ወጣ፣ አንድም መጋረጃውን አስገለጠ፣

ወመሐትወ ወርቅ የሐትዉ ቅድሜሁ፣

በወርቅ መቅረዝ ላይ በፊቱ ፋናውን ያበሩ ነበረ፣

፳፪፡ ወሶበ መጽአት ዮዲት ኀቤሁ ወይቀውሙ ደቁ፣

ዮዲት ወደሱ በመጣች ጊዜ ልጆቹ በፊቱ ቁመው ነበረ፣

ወተደሙ ኵሎሙ እምስነ ላህየ ገጻ፣

ከፊቷ ደም ግባት የተነሳ ሁሉም ተደነቁ፣

ወወድቀት በገጻ ውስተ ምድር ወሰገደት ሎቱ፣

ግምባሯን ምድር አስነክታ ሰገደችለት፣

ወአንሥእዋ አግብርቲሁ፣

አሽከሮቹ አነሷት።

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ፲፩

፩፡ ወይቤላ ሆሎፎርኒስ ተአመኒ ብእሲቶ፤

ሆሎፎርኒስ አንቺ ሴት እመኝ አላት፡

ወኢይፍራህኪ ልብኪ፤

ልቡናሽ አይፍራብሽ፡

እስመ አንሰ ኢየሐስም ላእለ ሰብእ ዘያገብእ ርእሶ ከመ ይትቀነይ ለናቡከደነፆር ንጉሠ ኵሉ ዓለም፤

ለዓለሙ ሁሉ ንጉሥ ለናቡከደነፆር ይገዛ ዘንድ ራሱን ባዋረደ ሰው ላይ ምንም ምን ክፉ አላደርግምና፡

፪፡ ወይእዜኒ እሉ ሕዝብኪ እለ ይነብሩ ውስተ አድባር ሶበ አኮ ዘዓለዉኒ እምኢያንሣእኩ ኵናትየ ላዕሌሆሙ፤

አሁንም በደጋ የሚኖሩ እሊህ ወገኖችሽ የከዱኝ ባይሆን ጦሬን በነዚያ ላይ ባላነሣሁ ባቸውም ነበረ፡

አላ እሙንቱ ለሊሆሙ ገብርዎ ለዝንቱ፤

ይህንን እነዚያ ራሳቸው አመጡት እንጂ፡

፫፡ ወይእዜኒ ንግርኒ በበይነ ምንት ተኃጣእኪ እምኔሆሙ ወመጻእኪ ኀቤነ፤

አሁንም ንገሪኝ ከነዚያ ኮብለሽ ስለምን ወደኛ መጣሽ፡

ወባሕቱ ለሕይወትኪ መጻእኪ፤

ነገር ግን ሕይወት ሊደረግልሽ መጥተሻል፡

ተአመኒ ከመ በዛቲ ሌሊት ተሐይዊ ለዝሉፉ፤

በዚች ሌሊት ለዘለዓለሙ እንድትድኚ እመኚ፡

፬፡ ወአልቦ ዘየሐሥም ላዕሌኪ፤

ባንቺ ላይ ክፉ ነገር የሚያደርግ የለም፡

ዘእንበለ ሠናይ ዘንገብር ላዕሌኪ፤

ባንቺ ከምናደርገው ከበጐ ነገር በቀር፡

በከመ ንገብር ለአግብርተ እግዚእነ ንጉሥ ናቡከደነፆር፤

ለጌታችን ለናቡከደነፆር ባሮች እንደምናደርገው እናደርግ ልሻለን እንጂ፡

፭፡ ወትቤሎ ዮዲት ተወከፍ ቃለ አመትከ፤

ዮዲትም የኔን የባሪያህን ነገር ተቀበለኝ አለችው፡

ወትነግረከ አመትከ በቅድሜከ፤

እኔ ባሪያህ በፊትህ ልንገርህ፡

ወኢይነግሮ ሐሰተ ለእግዚእየ በዛቲ ሌሊት፤

በዚች ሌሊት ለአንተ ለጌታዬ ሐሰት አልነግርህም፡



፮፡ ወለእመ ተለውከ ቃለ አመትከ ፍጹመ ግብረ ይገብር እግዚአብሔር፤

የኔን የባሪያህን ቃል ብትሰማ እግዚአብሔር ጠላቶችህን ያጠፋልሃል፡

ወአልቦ ዘይስሕት እምዘ ሐለይከ እግዚእየ፤

ጌታዬ ካሰብኸው ሁሉ ምንም የሚቀር የለም፡

፯፡ ወሕያው ውእቱ ናቡከደነፆር በኵሉ ምድር፤

ናቡከደነፆር በዚህ ዓለም በሕያውነት ሳለ፡

ወሕያው ኃይሉ ዘፈነወከ ከመ ታስተራትዕ ኵሎ፤

ሁሉን ታስገዛለት ዘንድ አንተን የሰደደህ ሕያው ነው፡

ከመ አኮ ሰብእ ባሕቲቱ ዘይትቀነይ ሎቱ በዕብሬትከ፤

በዘመንህ የሚገዛለት ሰው ብቻ እንዳይደለ፡

አላ አራዊተ ገዳምኒ ወእንስሳ ወአዕዋፈ ሰማይኒ በእንተ ኃይልከ ይትቀነዩ፤

ባንተ ኃይል የምድረ በዳ አራዊት እንስሳም የሰማይ አዕዋፍም ይገዙለታል እንጂ፡

ወየሐይዉ ለናቡከደነፆር ወኵሉ ቤቱ፤

ለናቡከደነፆር ለወገኖቹም ሲገዙለት ይኖራሉ፡

፰፡ እስመ ሰማዕነ ግብረከ፤

ሥራህን ሰምተናልና ወጥበቤሃ ለነፍስከ፤ የልቡናህንም ጥበብ ሰምተናልና፡

ወተሰምዓ በኵሉ ምድር ከመ አንተ ባሕቲትከ ኄር በኵሉ መንግሥቱ፤

በሚገዛው ሀገር ሁሉ ቸር አንተ ብቻ እንደሆንህ በዓለሙ ሁሉ ተነገረ፡

ወጽኑዕ አንተ በኵሉ ግብርከ፤

በምትሠራው ሥራ ሁሉ አንተ ጽኑ ነህ፡

ወመድምም አንተ በኵሉ ፀብዕከ፤

በሰልፍህ ሁሉ አንተ ግሩም ነህ፡

፱፡ ወይእዜኒ ቃለ ዘይቤለክሙ አኪዮር ዘይቤ በውስተ ትዕይንትክሙ ሰማዕነ ዘይቤ፤

ዘይቤና ዘይቤ አንድ ወገን፤ አክዮር የነገራችሁን የሰማችሁትን ሰማን፡ አንድም አኪዮር የነገረው ሰው የነገራችሁን ነገር፡ አንድም አኪዮር ሲናገር ሰምቶ የነገረው ሰው የነገራችሁን ነገር ሰማን፡

ወሰብአ ቤጤልዋ አሕየውዎ፤

የቤጤልዋ ሰዎች ያዳኑት፡

ወዜነዎሙ ኵሎ ዘይቤለክሙ፤

የነገራችሁን ሁሉ የነገራቸው የቤጤልዋ ሰዎች ያዳኑት የአኪዮርን ነገር፡

www.ethiopianorthodox.org

፲፡ ወይእዜኒ እግዚኦ ኢታስትት ቃሎ፣

አቤቱ አትናቅ፣ አትዘንጋ፡

አላ ሢሞ ውስተ ልብከ፡

በልቡናህ አስበው፣ አስተውለው እንጂ፡

እስመ አማን ከማሁ ውእቱ፣

እኔ እንደተናገርሁት እውነት ነውና፡

እስመ ኢይክልዎሙ ለሕዝብ ተበቅሎቶሙ፣

ሕዝቡን ተበቅሎ ለማጥፋት አትችሉምና፡

ወኢትክል ኵናት ቀቲሎቶሙ፣

ጦርም ማጥፋት አይቻላትምና፡

እመ ኢአበሱ ለአምላኮሙ፣

ፈጣሪያቸውን ካልበደሉ፡

፲፩፡ ወይእዜኒ ከመ ኢይኩን እግዚእየ መስትተ፡

አሁንም ጌታዬ የጌታህን ቃል የናቅህ፣ ያቃለልህ እንዳትሆን፡ አንድም መስሕተ ይላል፡ መዘበቻ እንዳትሆን፡

ወዘኢይበቍዕ፣

ለጌታህ የማትረባ እንዳትሆን፡

በዘይበጽሖሙ ሞቶሙ ቅድመ ገጽከ፣

የእስራኤል ሞታቸው በፊትህ በሚደርስ ገንዘብ እስራኤል የሚሞቱበትን ነገር ልንገርህ አለችው፡ አንድም በዘኢይበጽሖሙ ሞቶሙ ይላል፡ የሰዎችህ ሞታቸው በማይደርስ ገንዘብ የማይሞቱበትን ልንገርህ፡

ወበዝ ኃጢአቶሙ እንተ ባቲ አምዕዕዎ ለአምላኮሙ በግብረ ጌጋዮሙ፣

በበደላቸው ሥራ ፈጣሪያቸውን ባሳዘኑት ሰዓት ኃጢአት ታገኛቸዋለች፡

፲፪፡ እስመ ሐልቀ እክሎሙ፣

እህላቸው አልቋልና፡

ወአዕዋረ ማዮሙ፣

ተሸክመው ያመጡት ውሀው አልቋልና፡

ወገብኡ ይብልዑ እንስሳሆሙ፣

ላሙን በሬውን ወደመብላት ተመለሱ፡

ወኵሎ ዘንተ ዘከልአሙ አምላኮሙ በውስተ አሪቶሙ ከመ ኢይብልዑ አልጸቁ ኪያሁ ይብልዑ፣

ፈጣሪያቸው እግዚአብሔር በኦሪት አትብሉ ያላቸውን ፈረሱን በቅሎውን ወደመብላት ተመልሰዋልና፡

፲፫፡ ወዘቀዳምያተ እክሎሙ፣

ከእህሉ አስቀድሞ የደረሰውን ለመብላት፡

ወአሥራተ ወይኖሙኒ፣

የወይኑንም አሥራት ወደመብላት ተመልሰዋልና፡

ወቅብዖሙኒ ዘዓቀቡ ዝኩ ወዘቀደሱ፣

ዝኩና ዘቀደሱ አንድ ወገን ለካህናት ለይተው ያኖሩትን፣ ዘይቱን ወደመብላት ተመልሰዋልና፡



ለካህናት እለ ይቀውሙ በኢየሩሳሌም ቅድመ ገጹ ለአምላክነ፣

በፈጣሪያችን ፊት በኢየሩሳሌም ለሚያገለግሉ ለካህናት የለዩትን፡

ሐለዩ ኪያሁ፣

ፈረሱን፣ በቅሎውን ሊበሉ በማሰባቸው ላይ አሥራቱን ሊበሉ አስበዋልና፡

ወኢይከውኖሙ ለገሢሥ በእደዊሆሙ፣

ስንኳን ሊበሉት በጃቸው ሊዳስሱት የማይገባቸውን፡

ወኢለአሐዱ እምውስተ ሕዝብ፣

ከሕዝቡም ላንዱ ሊበላው የማይገባውን ሊበሉ አስበዋልና፡

፲፬፡ ወለአኩ ውስተ ኢየሩሳሌም፣

በኢየሩሳሌም ያሉ ሰዎች አይበላ የተባለውን ይበላ ብለው ከላኩ፡

እስመ እለኒ ህየ ሀለዉ ከመዝ ይግበሩ፣

በዚያም ያሉ ሰዎች እንዲህ ካደረጉ የማይበላውን ብሉ ታሏቸው፡

ወእለኒ ነሥኡ ዘኅድገት እምኀበ ሊቃውንት ወመሳፍንት፣

አይበላ የተባለውን ፈረሱን በቅሎውን ይበላ የሚል ክታብ ካለቆች የተቀበሉ ሰዎች፡

፲፭፡ እምከመ ነገርዎሙ ወገብሩ ከመዝ፣

ከነገሩዋቸው እነዚያም አይበላ የተባለውን ከበሉ፡

ውእተ አሚረ ያገብአሙ ውስተ እዴከ፣

ያን ጊዜ በጅህ ይጥላቸዋል፡

፲፮፡ ወሶበ አእመርኩ ዘንተ ኵሎ አነ አመትከ ተኃጣእኩ እምኔሆሙ፣

እኔ ባሪያህ ይህን ሁሉ ባወቅሁ ጊዜ ከነዚያ ኮብልዬ መጣሁ፡

ወፈነወኒ እግዚአብሔር እግበር ምስሌከ ግብረ ዘአመሰ ምዕዎ ሰብእ ወኵሉ ምድር ይደነግፅ፣

ምድርም ሁሉ፣ ሰውም ሁሉ በሰማው ጊዜ የሚያስደነግጥ ሥራን ካንተ ጋራ እሠራ ዘንድ እግዚአብሔር ሰደደኝ፡

፲፯፡ እሰመ አነ አመትከ ፈራሂተ እግዚአብሔር አነ፣

እኔ ባሪያህ እግዚአብሔርን የማመልክ የምፈራ ነኝና ፡

ወእጸመዶ ለእግዚአብሔር አምላከ ሰማይ ወምድር መዓልተ ወሌሊተ፣

በመዓልትም በሌሊትም ሰማይና ምድርን የፈጠረ እግዚአብሔርን አገለግለዋለሁና፡

አዝዝ ወበል ኢትክልዕዋ፣

አትከልክሏት ብለህ እዘዝ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወይእዜኒ እነብር ኀቤከ እግዚኦ፤
አቤቱ አሁንም ከአንተ ዘንድ እቀመጣለሁ፤

ወባሕቱ በሌሊት እወጽእ አመትከ ገዳመ ከመ እጸሊ ኀበ እግዚአብሔር፤
ነገር ግን እኔ ባሪያህ ከእግዚ አብሔር እለምን ዘንድ ሌሊት ወደምድረ በዳ እሄዳለሁ፤

ወይነግረኒ ማዕዜ ዘገብሩ ኃጢአቶሙ፤
መቼም መች ያደረጉትን ኃጢ አታቸውን ይነግረኛል፤

፲፰፤ ወእመጽእ ወአየድዐከ፤
መጥቼ እነግርሃለሁ፤

ወትወጽእ ምስለ ኵሉ ኃይልከ ወአልቦ ዘይትቃወመከ፤
ከሠራዊቶችህ ጋራ ትወጣለህ የሚቃወምህ የለም፤

፲፱፤ ወእወስደከ እንተ ማዕከለ ይሁዳ እስከ ትበጽሕ ቅድመ ኢየሩሳሌም፤
በኢየሩሳሌም አንፃር እስክት ደርስ በይሁዳ መካከል እወስድሃለሁ፤

ወታነብር መንበረከ ማዕከላ፤
ዙፋንህን በመሀከሏ ትዘረ ጋለህ፤

ወታስተጋብኦሙ ወትነሥኦሙ ከመ አባግዕ ዘገደፎሙ ኖላዊሆሙ፤
ጠባቂ እንደሌላቸው በጎች ትይዛቸዋለህ እንጂ፤

ወከልብ ኢይልሕስ በልሳኑ በቅድሜከ፤
እነሆ ጥቂት መከራ የሚያ መጣብህ የለም፤

እስመ ሊተ ከመዝ ነገሩኒ ወአይድዑኒ፤
መላእክት፤ እንድም ሥላሴ ለኔ ነግረውኛልና፤

ወአእሚርየ ተፈነውኩ እንግርከ፤
ይህን አውቄ ልነግርህ መጣሁ፤

፳፤ ወአዳም ቃላ በቅድመ ሆሎፎ ርኒስ፤
ነገሯ ሁሉ ሆሎፎርኒስን በፊቱ ደስ አሰኘው፤

በቅድመ ኵሉ ሕዝብ፤
በሰው ሁሉ ፊት ደስ አሰኘው፤

ወአንከሩ ጥበቢሃ፤
ጥበቧን አደነቁ፤

፳፩፤ ወይቤሉ አልቦ ከመ ዛቲ ብእሲት እምአጽናፈ ምድር እስከ አጽናፈ ምድር፤
ጽንፍ እስከ ጽንፍ ድረስ እንደዚች ያለች ሴት የለም አሉ፤

በስነ ገጽ፤
በመልኳ ማማር ፡
ወበጥበበ ቃላ፤
ነገር በማወቋ፤



፳፪፤ ወይቤላ ሆሎፎኒስ ሠናየ ገብረ እግዚአብሔር ላዕሌኪ ዘፈነወኪ ቅድመ ሕዝብኪ ከመ ትኩኒ ውስተ ጽንዓ እዴነ፤
ሆሎፎርኒስ እንዲህ አላት፤ በኛ ሥልጣን ትድኝ ዘንድ ከወገኖችሽ አስቀድሞ ወደኛ የሰደደሽ እግዚአብሔር በጐ ነገር አደረገልሽ፤

ወለእለሰ ዐለውዎ ለእግዚእየሞት ወሕርትምና፤
ጌታዬን የከዱትን ሰዎች ግን ሞት ተዋርዶ ያገኛቸዋል፤

፳፫፤ ወይእዜኒ ሠናይት በራእይኪ አንቲ፤
አሁንም አንቺ መልከ መልካም ነሽ እነሆ ብትልም፤

ወቡርክት አንቲ በቃልኪ፤
ነገር በማወቅሽም ንእድ ክብርት ነሽ፡

ወእመ ገበርኪ በከመ ትቤሊ ይከውነኪ አምላክኪ አምላኪየ፤
እነሆ እንደተናገርሽ ብታደርጊ ፈጣሪሽ ፈጣሪዬ ይሆናል፤

ወአንቲ ትነብሪ ውስተ ቤቱ ለናቡከደነፆር፤
አንችም በናቡከደነፆር ቤት ትኖሪያለሽ፤

ወይትሌዓል ስምኪ በኵሉ ምድር፤
ስምሽ በዓለም ሁሉ ይከብራል።

## ምዕራፍ ፲፪

፩፤ ወአዘዘ ያብእዋ ኀበ ያነብሩ ንዋየ ብሩር፤
ብር ከሚያኖሩበት ከዕቃ ቤት ያገቧት ዘንድ አዘዘ፤

ወአዘዘ ይሴስይዋ እምነ ዘይገብሩ ሎቱ ሲሳዮ፤
እሱ ከሚበላው ያበሏት ዘንድ፤
ወያስትይዋ እምነ ወይኑ፤
እሱ ከሚጠጣው ያጠጧት ዘንድ አዘዘ፤

፪፤ ወትቤ ዮዲት ኢይበልዕ እምኔሁ ከመ ኢይኩነኒ ጌጋየ፤
ዮዲት እንዲህ አለች፤ እዳ እንዳይሆንብኝ ከዚህ አልበላም አለች፤

አላ እምነ ዘአምጻዕኩ እሴሰይ፤
ከአመጣሁት ከስንቄ እመገ ባለሁ እንጂ፤

፫፤ ወይቤላ ሆሎፎርኒስ፤
ሆሎፎርኒስ እንዲህ አላት፤

ወእመሰ ኀልቀ ዘአምጻእኪ ምስሌኪ እምአይቴ ናመጽእ ለኪ ዘንሁበኪ ዘከማሁ፤
ያመጣሽው ያለቀ እንደሆነ እንደሱ ያለ የምንሰጥሽ ከወዴት እናገኛለን፤

ወእምነ ሕዝብኪ አልቦ ዘሀሎ ምስሌነ፤
ከወገኖችሽም ከኛ ጋር የሚኖር የለም፤

www.ethiopianorthodox.org

፬፡ ወትቤሎ ዮዲት ሕያው ነፍስከ እግዚእየ፣

ዮዲት እንዲህ አለችው፤ ጌታዬ በረከትህን፤

ከመ ኢትዌድእ አመትከ ዘሀለወ ምስሌሃ እስከ አመ ይገብር እግዚ አብሔር ዘመከረ በእዴየ፣

እግዚአብሔር በኔ ቃል የመከረ ውን እስከ አደርግ ድረስ ከኔ ጋራ ያለውን እንዳልፈ ጽመው በረከትህን አለችው፤

፭፡ ወአብእዋ ደቂቀ ሆሎፎርኒስ ውስተ ደብተራ፣

የሆሎፎሮኒስ ልጆች ወደ ድንኳኑ አገቧት፤

ወቤተት ወኖመት እስከ መንፈቀ ሌሊት፣

እስከ መንፈቀ ሌሊት ተኝታ አደረች፤

፮፡ ወተንሥአት በሰዓት፣

በጊዜው ጊዜ ተነሣች፤

ወእምድኅረ ንቅሐተ ሌሊት ለአከት ኀቤሁ ለሆሎፎርኒስ፣

ሌሊት ከነቃች በኋላ ከሆሎፎ ርኒስ ዘንድ ላከች፤

እንዘ ትብል አዝዝ እግዚእየ ያብሕዋ ትፃእ አመትከ፣

እኔ ባሪያህ ለጸሎት እወጣ ዘንድ እንዳይከለክሉኝ እዘዝ፤

፯፡ ወአዘዞሙ ሆሎፎርኒስ ለእለ የዓቅብዋ ከመ ኢይክልእዋ፣

ሆሎፎርኒስ የሚጠብቋትን ሰዎች እንዳይከለክሏት አዘዛቸው፤

ወእምዝ ነበረት ሠሉሰ መዋዕለ ውስተ ትዕይንት፣

ከዚህ በኋላ ሦስት ቀን በሰፈሩ ተቀመጠች፤

ወትወጽእ በሌሊት ውስተ ቈላተ ቤጤልዋ፣

ሌሊት ወደ ቤጤልዋ ቆላ ትሄድ ነበር፤

ወትጠመቅ በትዕይንት ውስተ ነቅዓ ማይ፣

በከተማው ባለው ውሀ ትጠ መቅ ነበረ፤

፰፡ ወሰበ ተዓርግ ትጼሊ ኀበ እግዚአብሔር አምላከ እሥራኤል ያርትዕ ፍኖታ፣

ከውሀውም ተጠምቃ በወጣች ጊዜ ጎዳናዋን ያቀናላት ዘንድ ወደእሥራኤል ፈጣሪ ወደእግ ዚአብሔር ትጸልይ ነበር፤

በዘኢይትነሥኡ ደቂቀ ሕዝባ፣

የወገኖቿ ልጆች በማይማረኩ ገንዘብ፤

፱፡ ወእምዝ ትገብእ፣

ከተጠመቀች በኋላ ወደ ድንኳኗ ትመለስ ነበር፤



ወነበረት ንጽሕተ ውስተ ትዕይንት፣

በከተማው ከኃጢአት ንጽሕት ሁና ተቀመጠች፤

ወሠርከ ሠርከ ትበልዕ፣

ማታ ማታ ትበላ ነበረች፤

፲፡ ወእምዝ አመ ራብዕት ዕለት ገብረ ሆሎፎርኒስ ምሳሐ ለአግብር ቲሁ ለባሕቲቱ፣

ከዚህ በኋላ በአራተኛው ቀን ሆሎፎርኒስ ለቤተሰቦቹ ብቻ ምሳ አደረገ፤

ወኢፀውዐ ባዕደ ሰብአ ወኢመነሂ ውስተ ምሳሕ፣

ማንንም ማን ወደምሳው ባዕድ ሰው አልጠራም ነበረ፤

ጉባዔ

፲፩፡ ወይቤሎ ለባግዋ መጋቢሁ ሕጽው ዘኮሉ ንዋዩ ላዕሌሁ፣

በገንዘቡ ሁሉ ላይ የሾመው ባለሟሉ ባግዋን እንዲህ አለው፤

አስፍጣ ሊተ ለዛቲ ብእሲት ዕብራዊት እንተ ኀቤከ፤

ካንተ ዘንድ ያለች ያችን ዕብራዊት ሴት አባብልልኝ፤

ከመ ትምጻእ ኀቤነ ወትብላዕ ወትስተይ ምስሌነ፣

መጥታ ከኛ ጋራ ትበላ ትጠጣ ዘንድ አባብልልኝ፤

ሐር ኀቤሃ ተናገራ፣

ከሷ ዘንድ ሂደህ ንገራት፤

፲፪፡ እስመ ኃፍረት ለነ እንተ ከመ ዛቲ ብእሲት ረኪበነ እመ ኢተናገርናሃ፣

እንዲህ ያለች መልከ መልካም ሴት አግኝተን ሳንጫወት ብንሰዳት ለኛ ተዋርዷችን ነውና፤

ወእመ ኢረከብናሃ ለዛቲ ይስሕቁነ፣

ይህችንም ሳንገናኝ ብንሰዳት ይዘብቱብናልና አባብልልኝ አለው፤

፲፫፡ ወወፅአ ባግዋ እምኀቤሁ ለሆሎፎርኒስ ወቦአ ኀቤሃ፣

ባግዋ ሆሎፎርኒስ ካለበት ወጥቶ እሷ ካለችበት ገባ፤

ወይቤላ ኢትትሐከዪ ወለትየ ሠናይት መጺአ ኀበ እግዚእየ ትትአከቲ በኀቤሁ፣

ያማርስ የተወደድሽ ልጄ በሱ ዘንድ ትመሰገኝ ዘንድ ወደሱ መምጣትን ቸል አትበይ፤

ወትስተዪ ወይነ ምስሌሁ ወትትፈሥሒ፣

ወይኑን ጠጥተሽ ከሱ ጋራ ደስ ይልሽ ዘንድ፤

ወትኩኒዮ ዮም ከመ አሐቲ እምነ አዋልደ ደቂቀ አሶር እለ ይቀውማ ውስተ ቤቱ ለናቡከደነፆር፣

በናቡከደነፆር ፊት ከሚቆሙ ከኃያላኑ ልጆች እንደ አንዲቱ ትሆኚ ዘንድ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፬፡ ወትቤሎ ዮዲት ምንት አነ፣

ዮዲት እንዲህ አለች፤ እኔ ምንድር ነኝ፤

ወሚ ዘመድየ ከመ እትዋሥአ ለእግዚእየ፣

ጌታዬን አይሆንም ብዬ እከራ ከረው ዘንድ ወገኔስ ማነው?

ኵሎ ዘአደመከ በቅድመ አዕይንቲከ አገብር ፍጡነ፣

በፊትህ ደስ የሚያሰኝህን ሁሉ ፈጥኜ አደርጋለሁ፤

ወሊተ ይከውነኒ ትፍሥሕተ እስከ አመ እመውት፣

ለኔም እስክሞት ድረስ ተድላ ደስታ ይሆነኛል፤

፲፭፡ ወተንሥአት ወተሠነየት፣

ተነሥታ አጌጠች፤

ወለብሰት አልባሲሃ፣

ልብሷን ለበሰች፤

ወተሠርገወት ኵሎ ሠርጉ አንስት፣

የሴቶችን ሁሉ ጌጥ አጌጠች፤

ወሖረት ምስሌሃ ወለታ፣

ገረዷ አብራት ሄደች፤

ወነጸፈት ላቲ ውስተ ምድር ቅድሜሁ ለሆሎፎርኒስ ምስካቢሃ ዘነሥአት እምነበ ባግዋ፣

ከባግዋ ዘንድ የተቀበለችውን ምንጣፏን ከሆሎፎርኒስ ዘንድ አነጠፈችላት፤

ዘነጸፈ ላቲ በውስተ ማኅደራ ዘዲቤሁ ትረፍቅ ሶበ ትመስሕ፣

በምትበላበት ጊዜ በቤቷ የምት ቀምጥበትን ምንጣፍ አነጠፈ ችላት፤

፲፮፡ ወቦአት ዮዲት ወሰከበት፣

ዮዲት ገብታ አልጋውን ተጠ ግታ ተቀመጠች፤

ወተሀውከ ልቡ ለሆሎፎርኒስ ላዕሌሃ፣

የሆሎፎርኒስ ልቡናው በሷ ላይ ተነሳሳበት፤

ወፈተወት ነፍሱ ፈድፋደ ይስክብ ምስሌሃ፣

ከሷ ጋራ ፈቃዱን ይፈጽም ዘንድ ልቡናው እጅግ ወደዳት፤

ወይጸንሕ እምአመ ርእያ እስከ ጊዜ ያስፍጣ፣

ከአያት ጀምሮ እስኪያታልላት ድረስ ደጅ ጸናት፤

፲፯፡ ወይቤላ ሆሎፎርኒስ ስተዪ ምስሌነ ወተፈሥሒ፤

ሆሎፎርኒስ ከኛ ጋራ ብዪ ጠጪ ደስ ይበልሽ አላት፤

፲፰፡ ወትቤሎ ዮዲት እሰቲ እግዚእየ፤

ዮዲት ጌታዬ እጠጣለሁ አለችው፤

እስመ አብየት ዮም ሕይወትየ ላዕሌየ፣

በኔ ላይ ያለች ሰውነቴ ዛሬ ከብራለችና፤



እምነ ኵሉ መዋዕልየ ዘአመ ተወለድኩ፣

ከተወለድሁበት ዘመን ጀምሮ ይልቅ፤

፲፱፡ ወነሥአት ወሰትየት ወበልዐት በቅድሜሁ ዘአስተዳለወት ላቲ ዓመታ፣

ገረዷ ያዘጋጀችላትን በላች ጠጣች፡

፳፡ ወተፈሥሐ ሆሎፎርኒስ በእንቲአሃ፣

ሆሎፎርኒስ ስለሷ ደስ አለው፡

ወሰትየ ወይነ ብዙኃ፣

ብዙ ወይን ጠጣ፡

ወፈድፋደ ዘኢሰትየ ከማሁ ወኢበአሐቲ ዕለት እምአመ ኮነ ወእም አመ ተወልደ፣

ከተወለደና ከተፈጠረ ጀምሮ ባንዲት ቀንስ እንኳ እንደዚህ ጠጥቶ የማያውቀውን አብዝቶ ጠጣ።

## ምዕራፍ ፲፫

፩፡ ወሶበ መስየ አስተፋጠኑ አግብርቲሁ ወአግሐሡ፣

በመሸ ጊዜ ባሮች ሰውን አፋጠኑ ሰውን ተመለሱ አሉ፡

ወባግዋ ዐጸወ ደብተራሁ ላዕሌሆሙ እንተ አፍአ፣

ባግዋ በውጭ ድንኳኑን ቆለፈ ባቸው፡

ወሰደዶሙ ለእለ ይቀውሙ ቅድመ እግዚኡ፣

በጌታውም ፊት የሚቆሙ ትንም፤ ሰዎች ተመለሱ ብሎ አሰናብቶ ሰደዳቸው፤

ወአተዉ ውስተ ማኅደሪሆሙ፣

ወደቤታቸው ገቡ፤

እስመ ድኩማን ኵሎሙ እስመ ፈድፋደ ሰትዩ፡

መጠጥ ስላበዙ ሰክረዋልና፤

፪፡ ወተርፈት ዮዲት ባሕቲታ፣

ዮዲት ብቻዋን ቀረች፡

ወሆሎፎርኒስኒ ውስተ ደብተራሁ፣

ሆሎፎርኒስም ከድንኳኑ ብቻ ውን ነበረ፤

ውእቱሰ ይሰክብ ውስተ ምስካቡ፣

እሱ ግን ካልጋው ተኝቶ ነበር፡

እስመ ፈድፋደ ሰትየ፣

መጠጡን አብዝቷልና፤

ወስኩር ውእቱ፣

ሰክሮ ነበርና፣

፫፡ ወትቤላ ዮዲት ለአመታ፣

ዮዲት ባሪያዋን እንዲህ አለቻት፤

ትፃእ አፍአ ወትቁም ኀበ ማኅደራ፣

ከውጭ ወጥታ ከማደሪያዋ ትቆም ዘንድ፤

ወትፅቀባ ጊዜ ትወጽእ ከመ ዘልፍ፣

በምትወጣበት ጊዜ እንደ ወትሮው ትጠብቃት ዘንድ፤

www.ethiopianorthodox.org

እስመ እወጽእ ኀበ እጼሊ ትቤላ፤

ወደምጸልይበት ቦታ እወጣለሁ ብላታለችና፡

ወለባጎዋኒ ከማሁ ትቤሎ፤

ባግወንም ከዚህ ምን እቁሞሃል? አለችው፡

፬፡ ወወጽኡ ኵሎሙ እምኀቤሁ፤

ሁሉም እሷ ካለችበት ወጡ፡

ወአልቦ ዘተርፈ ውስተ ጽርሑ ኢንዑስ ወኢዓቢይ፤

ታናሽም ሁኖ ታላቅም ሁኖ ከዚያ ከድንኳኑ የቀረ የለም፡

ወተንሥአት ዮዲት ወቆመት ኀበ ምስካቡ፤

ዮዲት ተነሥታ ከድንኳኑ ቆመች፡

ወትቤ በልባ እግዚኦ አምላከ ኵሉ ኃይል፤

በልቡናዋ እንዲህ አለች፡ አቤቱ የመላእክት ፈጣሪ፡

ርኢ ወግበር በእዴየ በዛቲ ሰአት ከመ ትትለአል ኢየሩሳሌም፤

በዚህች ሰዓት ኢየሩሳሌም ከፍ ከፍ ትል ዘንድ መከራችንን አይተህ በኔ እጅ ይቅርታህን አድርግ፡

፭፡ እስመ በጽሐ ጊዜሁ በዘታንሥእ ርስተከ፤

እስራኤልን ከኃጣር የምታነሣበት ጊዜው ደርሷልና፡

ወግበር ሊተ ሕሊናየ በዘይሜሮ ፀር እለ ተንሥኡ ላዕሌነ፤

በኛ ላይ የተነሣ ጠላት በሚጠፋ ገንዘብ የልቡናየን አሳብ አድርግልኝ፡

፮· ወሖረት ውስተ ምስካቡ መንገለ ትርአሲሁ ለሆሎፎርኒስ፤

በሆሎፎርኒስ በራስጌው በኩል ወደመኝታው ሄደች፡

ወመልሐት መተርእስቶ፤

ተንተርሶት ያለ መክድ ሰይፉን መዘዘች፡

፯፡ ወቆመት መልዕልቴሁ፤

በጠላትነት ተነሣችበት፡

ወአኀዘት በስዕርተ ርዕሱ፤

ቁንዳላውን ይዛ፡

ወትቤ እግዚእየ አምላከ፡ እስራኤል አጽንዓኒ ዮም፤

የእስራኤል ፈጣሪ ዛሬ አጽናኝ አለች፡

፰፡ ወዘበጠት ካዕበ ውስተ ክሳዱ በኃይላ፤

በኃይሏ ሁለት ጊዜ አንገቱን መታችው ሴት ደካማ ናትና ሳይቆረጥ ቀረ ደገመችው ተቆረጠ፡

ወመተረት ርእሶ እምኔሁ፤

ቾብቾቦውን ከሱ ቆረጠች፡



፱፡ ወአውደቀት በድኖ እምነ ምስካቡ ውስተ ምድር፤

ይህ ጣዖታዊ ብላ በድኑን ከዙፋኑ ገልብጣ ከመሬት ጣለችው፡

ወነበረት ንስቲተ፤

ጥቂት ተቀመጠች፡ አንድም፡ አርፋ ቆየች፡

ወወጽአት ወወሀበታ ለወለታ ርእሶ ለሆሎፎርኒስ፤

ወጥታ የሆሎፎርኒስን ቾብቾቦ ለገረዷ ሠጠቻት፡

፲፡ ወወደየቶ ውስተ ዕፍኒታ ዘእክል፤

በስንቋ አቁማዳ አደረገችው፡

ወወፅአ ክልኤሆን ኅቡረ በከመ ያለምዳ ለጸሎት፤

ሁለቱም ለጸሎት እንዳስለመዱ አንድ ሁነው ወጡ፡

ወዐደዋ እምተዓይን ዓደዋ እንተ ውስተ ቈላት፤

ከከተማው ወጥተው ቆላቆላውን ሄዱ፡

ወዓርጋ እንተ ዓቀበ ቤጤልዋ፤

ቆላውን ጨርሰው ተራራውን ወጡ፡

ወበጽሓ ኀበ አንቀጸ ሀገር፤

ካምባው በር ደረሱ፡

፲፩፡ ወትቤሎሙ ዮዲት አምርኁቅ ለእለ የዓቅቡ አንቀጸ አኅርዉ አንቀጸ፡

ዮዲት በር የሚጠብቁትን ዘበኞች ከሩቅ በሩን ክፈቱልኝ አለቻቸው፡

እስመ እግዚአብሔር ምስሌነ ከመ ይግበር ዓዲ ኃይለ ወጽንዓ ለእሥራኤል እምነ በሮሙ ከመ ገብረ ዮም፤

ለኔ ዛሬ እንዳደረገ ከጠላቶቻቸው ይልቅ ዳግመኛ ለእሥራኤል ኃይልን ጽንዕን ያደርግላቸው ዘንድ እግዚአብሔር በረድኤት ከኛ ጋራ አለና፡

፲፪፡ ወእምዝ ሶበ ሰምዑ ቃላ ሰብአ ሀገር አፍጠኑ ወሪደ ኀበ አንቀጸ ሀገር፤

ከዚህ በኋላ ካምባው ላይ ያሉ ሰዎች ቃሏን በሰሙ ጊዜ ፈጥነው ወደበሩ ወረዱ፡

ወጸውዑ ሊቃውንተ ሀገር፤

የሀገሩን አለቆች ጠሩ፡

፲፫፤ ወሮጹ ኵሎሙ ንኡሳሙ ወዓቢዮሙ ፤

ታላቆችም ትንሾችም ፈጥነው ሄዱ፡

እስመ አንከሩ እፎ ገብአት፡

እንዴት ተመለሰች ብለው መመለሷን አድንቀዋልና፡

ወአርኃዉ አንቀጸ ወተቀበልዋ፤

በሩን ከፍተው ተቀበሏት፡

www.ethiopianorthodox.org

ወአንደዱ እሳተ ወአብርኍ፤

እሳቱንም አነደዱ መብራቱንም አበሩ፡

ወዖድዋ፡

ከበቧት፡

፲፬፡ ወትቤሎሙ በዐቢይ ቃል ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር፤

ቃሏን አሰምታ እግዚአብሔርን አመስግኑት አለች፡

እስመ ኢያርኀቀ ሣህሎ ወምሕረቶ እምነ እስራኤል፤

ይቅርታውን ቸርነቱን ከእስራኤል አላራቀምና፡

አላ ሠረዮሙ ለፀሩ በዛቲ ሌሊት፤

በዚች ሌሊት ጠላቶቹን በኔ እጅ አጠፋቸው እንጅ፡

፲፭፡ አውፅአት ርእሶ እምነ ዕፍነታ ወአርአዮቶሙ፤

ቸብቸቦውን ካቁማዳው አውጥታ አሳየቻቸው፡

ወትቤሎሙ ናሁ ርእሱ ለሆሎፎርኒስ መልአከ ኀይሎሙ፡ ለአሶር፤

የኀያላኑ ሠራዊት አለቃ የሆሎፎርኒስ ቸብቸቦው ይህ ነው አለቻቸው፡

ወናሁ መተርእሶቱ እንተ በዲቤሃ ይሰክብ፡ ሶበ ይሰቲ፤

በጠጣ ጊዜ ተንተርሷት የሚተኛ መከድ ሰይፉ ይህች ናት፡

ወቀተሎ እግዚአብሔር በእደ ብእሲት፤

እግዚአብሔር በእኔ እጅ ገደለው፡

፲፮፡ ወሕያው እግዚአብሔር ዘአቀበኒ በፍኖትየ እንተ ሖርኩ ከመ አስሕቶ በገጽየ ከመ ይሙት፡

ይሞት ዘንድ በመልኬ አስተው ዘንድ በሄድሁበት ጎዳና የጠበቀኝ እግዚአብሔር ሕያው ነው፡

ወኢገብረ ላዕሌየ አበሳ ወርኵሰ ወኀሣረ፤

ምንተ ሕሡመ ወምንተ ሕሩመ ሲል ነው፤

ምንም ምን ክፉ ነገር አላደረገብኝም፡

፲፯፡ ወደንገፁ ኵሉ ሕዝብ ፈድፋደ፡

ሕዝቡ እጅግ ደነገጡ ፡

ወደነኑ ወሰገዱ ለእግዚአብሔር፤

አንገታቸውን ዝቅ አድርገው ለእግዚአብሔር ሰገዱ፡

ወይቤሉ ኅቡረ፡

አንድ ሁነው እንዲህ አሉ፡

ቡሩክ አንተ አምላክነ ዮም በዛቲ ዕለት ዘአሕሠርኮሙ ለፀረ ሕዝብከ፤

ዛሬ በዚህች ቀን የወገኖችህን ጠላቶች ያጐሰቆልሐቸው ፈጣሪያችን አንተ ክቡር ምስጉን ነህ፡



፲፰፡ ወይቤላ ዖዝያን፤

ዖዝያን እንዲህ አላት፡

ቡርክት ለእግዚአብሔር ልዑል አንቲ ወለትየ እምነ ኵሎን አንስት እለ ውስተ ምድር፤

ልጄ በዚህ ዓለም ከሚኖሩ ሴቶች ይልቅ አንቺ የእግዚአብሔር ክብርት ፍጥረቱ ነሽ፡

ወቡሩክ እግዚአብሔር ፈጣሬ ሰማያት ወምድር፤

ሰማይንና ምድርን የፈጠረ እግዚአብሔር ክቡር ምስጉን ነው፡

ዘረድአኪ ትምትሪ ርእሶ ለመልአከ ፀርነ፡

የጠላቶቻችን አለቃ የሆሎፎርኒስን አንገቱን ትቆርጪ ዘንድ የረዳሽ እግዚአብሔር ክቡር ምስጉን ነው፡

፲፱፡ እስመ ኢይደመስስ አኰቴትኪ እምልበ እጓለ እመሕያው እንዘ ይዜክሩ ኀይለ እግዚአብሔር ለዓለም፤

የእግዚአብሔርን ተአምራቱን ለዘለዓለም ሲያስቡ ምስጋናሽ ከሰው ልቡና አይጠፋምና፡

፳፡ ወይሬስዮ ለኪ እግዚአብሔር ስመኪ ዘለዓለም፤

እግዚአብሔር ስምሽን ለዘላለም ሲጠራ እንዲኖር አደረገው፡

ወይነጽርኪ በሠናይቱ፤

በዓይነ ምሕረት ይመልከትሽ፡

እስመ ኢመሐክኪ ነፍስኪ በእንተ ሕማመ ሕዝብኪ፤

ስለወገኖችሽ መከራ ለሰውነትሽ አላዘንሽምና፡

አላ አንቲ ወፃእኪ በእንተ ሞት፤

ልሙት ብለሽ ሄድሽ እንጅ፡

ወርቱዐ ሖርኪ ቅድመ አምላክነ፡

በፈጣሪያችን ፊት አቅንተሽ ሄድሽ፡

ወይቤሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን፤

ሕዝቡ ሁሉ እውነት ነው እውነት ነው አሉ።

## ምዕራፍ ፲፬

፩፡ ወትቤሎሙ ዮዲት ስምዑኒ አኃውየ፤

ዮዲት ወንድሞቼ ስሙኝ አለቻቸው፡

ንሥኡ ዘንተ ርእሶ ወስቅሉ ውስተ ተድባበ አረፍትክሙ፤

ቸብቸቦውን ወስዳችሁ ከቅጽሩ ላይ ስቀሉት፡

፪፡ ወእምዝ ሶበ ጎሐ ጽባሕ፡

በነጋ ጊዜ፡

ወወጽአት ፀሐይ ውስተ ምድር፡

ፀሐይ በዚህ ዓለም በወጣች ጊዜ፡

www.ethiopianorthodox.org

ንሥኡ ኵልክሙ ንዋየ ሐቅልክሙ።

ሁላችሁም ጋሻ ጦራችሁን ያዙ፡

ወይፃኡ ኵሎሙ ዕደው ኃያላን አፍአ እምነ ሀገር።

ኃያላኑ ሁሉ ካምባው ወደ ውጭ ይውጡ፡

ወሚሙ ለክሙ መልአከ።

ለናንተ አለቃ ሹሙ፡

ወሶበ ወረድክሙ ውስተ ምድር መንገለ መዓቅቢሆሙ ለደቂቀ አሶር።

የኃያላኑ ልጆች ዘበኞች ወዳሉበት ወደመሬት በወረዳችሁ ጊዜ፡

፫፡ ንሥኡ ኵልክሙ ንዋየ ሐቅልክሙ ወቡሩ።

ሁላችሁም ጋሻ ጦራችሁን አንሥታችሁ ያዙ፡

ወእምከመ ርእዩክሙ የሐውሩ መዐቅቢሆሙ ኀበ ተዓይኒሆሙ።

ከአዩዋችሁም በኋላ ዘበኞቹ ወደሰፈራቸው ይሄዳሉ፡

ከመ ያንሥኡ መላእክተ ሠራዊቶሙ ለአሶር ወኃይሎሙ።

የኃያላኑ የሠራዊቶች አለቆችና ሠራዊቱን ያስነሱ ዘንድ ይሄዳሉ፡

ወእምዝ ይረውጹ ኀበ ደብተራሁ ለሆሎፎርኒስ ወኢይረክብዎ።

ከዚህ በኋላ ወደ ሆሎፎርኒስ ድንኳን ይሄዳሉ አያገኙትም፡

ወእምዝ ይፈርሁ ወይደነግፁ ወይጐይዩ እምቅድመ ገጽክሙ።

ከዚህ በኋላ ፈርተው ከፊታችሁ ይሸሻሉ፡

፬፡ ወአንትሙሰ ዴግንዎሙ፡

እናንተ ግን ተከተሏቸው፡

ወኵሉ እለ ይነብሩ ውስተ ኵሉ ደወለ እሥራኤል።

በእሥራኤል አውራጃ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ይከተሏቸው፡

ወነጽርዎሙ ውስተ ኵሉ ፍኖቶሙ።

የሚሄዱበትን ጎዳናቸውን ተመልከቷቸው፤ አንድም አጥርታችሁ ልቀሟቸው፤

፭፡ ወእምቅድመ ትግበሩ ዘንተ ጸውዑ ሊተ አክዮርሃ አሞናዊ ፡

ይህንን ከማድረጋችሁ አስቀድሞ የአሞንን አለቃ አክዮርን ጥሩልኝ፤

ከመ ይርአይ ወያእምር ከመ ዘሀለወ ለቤተ እሥራኤል ወፈነዎ ኪያሁኒ ኀቤነ ይሙት ምስሌነ፡

ከኛ ጋራ ይሞት ዘንድ እሱን ወደኛ የሰደደው የእሥራኤልን ወገኖች የወነጀላቸው እንደ ሆነ አይቶ ያውቅ ዘንድ፤

፮፡ ወጸውእዎ ለአኪዮር እምነ ቤተ ዖዝያን።

አክዮርን ከዖዝያን ቤት ጠሩት፡



ወሶበ መጽአ ወርእየ ርእሶ ለሆሎፎርኒስ ውስተ እደ ብእሲት በማኅበረ ሕዝብ።

መጥቶ የሆሎፎርኒስን ራስ በእስራኤል መካከል በዮዲት እጅ ባየው ጊዜ፡

ወድቀ በገጹ ወደንገጸት ነፍሱ።

በግምባሩ ፍግም ብሎ ወደቀ ልቡናውም ደነገጠች፡

፯፡ ወሶበ አንሥእዎ ወድቀ ውስተ እገሪሃ ለዮዲት ወሰገደ በገጹ።

ባነሱት ጊዜ ከዮዲት እግር ወደቀ፡ በግምባሩ ወድቆ ሰገደ፡

ወይቤ ቡርክት አንቲ እምነ ኵሉ ዓበይተ ይሁዳ።

በይሁዳ ካሉ። ከነገሥታቱ ከመሳፍንቱ አንቺ ክብርት ነሽ፡

ወእምኵሉ ሕዝብ በዓለም ሰሚያሙ ስመኪ ይደነግፁ።

ከሕዝቡም ወገን በዚህ ዓለም ስምሽን ሰምተው ይደነግጣሉ፡

፰፡ ወይእዜኒ ዜንውነ ኵሎ ዘገበርኪ በእላንቱ መዋዕል።

አሁንም በነዚህ ወራት ያደረግሽውን ሁሉ ንገሪን አላት፡

ወዜነወቶሙ ዮዲት በማዕከለ ሕዝብ ኵሎ ዘገብረት እምአመ ወጽአት እስከ አመ ገብአት።

ከወጣች ጀምሮ እስክትመለስ ድረስ ያደረገችውን ሁሉ ዮዲት ነገረቻቸው፡

፱፡ ወሶበ አህለቀት ነገራ።

ነገሯን ተናግራ ከፈጸመች በኋላ፡

ወወውዑ ኵሉ ሕዝብ በዓቢይ ቃል።

ሕዝቡ ሁሉ እንዳንድ ቃል ተናገረ ሁነው ደነፉ፡

ወጸርሑ በቃለ ትፍሥሕት በበሀገሮሙ።

በየቋንቋቸው በደስታ ቃል ጮሁ፡

፲፡ ወሶበ ርእየ አኪዮር ኵሎ ዘገብረ እግዚአብሔር ለእስራኤል አምነ ፈድፋደ በእግዚአብሔር።

አክዮር በእስራኤል ያደረገውን ተአምራት ባየ ጊዜ ፈጽሞ በእግዚአብሔር አመነ፡

ወተገዝረ።

ተገዘረ፡

ወተወሰከ ውስተ ቤተ እስራኤል እስከ ዮም።

እስከ ዛሬ ድረስ ከእሥራኤል ወገኖች ተጨመረ፡

፲፩፡ ወሶበ ጎሐ ወጸብሐ ሰቀሉ ርእሶ ለሆሎፎርኒስ ውስተ አረፍት።

ፈጽሞ በነጋ ጊዜ የሆሎፎርኒስን ቸብቸቦ ከቅጽሩ ላይ ሰቀሉ፡

ወነሥኡ ኵሎሙ ዕደዊሆሙ ንዋየ ሐቅሎሙ።

ወንዶች ሁሉ ጋሻ ጦራቸውን አነሱ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወወጽኡ ወአገትዎሙ እንተ መንገለ ዐቀበ ደብር፤

ወጥተው በተራራው አቀበት በኩል ከበቧቸው፤

፲፪፤ ወደቂቀ አሶር ሶበ ርእይዎሙ ለአኩ ኀበ መሳፍንቲሆሙ፤

የኃያላኑ ልጆችም ባዩዋቸው ጊዜ ወደመሳፍንቱ ላኩ፤

፲፫፤ ወወጽኡ መላእክቲሆሙ ወሥዩማኒሆሙ፤ ወመሳፍንቲሆሙ ኀበ ደብተራ ሆሎፎርኒስ፤

አለቆች የተሾሙት መሳፍንቱ ወደ ሆሎፎርኒስ ድንኳን ሄዱ፤

ወይቤልዎ ለመጋቢሁ አንቅሆ ለእግዚእነ፤

ሹሙን ጌታችንን ቀስቅስልን አሉት፤

እስመ ተሀበሉ አግብርት ወወረዱ ላዕሌነ ይትቃተሉነ፤

ባሮች ተደፋፍረው ይወጉን ዘንድ መጥተዋልና፤ አንድም ተታብው ይላል ወንጳወንድ ሁነውብናልና፤

፲፬፤ ወቦአ ባግዋ ወጕድጕደ ኀበ አፀድ ዘቅድመ ደብተራ፤

ከደጅ ሁኖ እጅ ጸፍቶ ባግዋ ወደድንኳኑ ገባ፤

እስመ መሰለ፡ ይሰክብ ምስለ ዮዲት፤

ከዮዲት ጋር የሚጫወት መስሎታልና፤

፲፭፤ ወሶበ አልቦ ዘየውሥእ ለቀየ፤

ቃል የሚመልስለት ባጣ ጊዜ ፈታ፤ ገለጠ፤

ወቦአ ውስተ ጽርሕ፤

ወደድንኳኑ ገባ፤

ወረከበ በድኖ ግዱፈ ውስተ ምድር ወርእሱ ኢሀለወ ላዕሌሁ፤

ቸብቸቦው ተቆርጦ በድኑ ከመሬት ወድቆ አገኘው፤

፲፮፤ ወጸርሐ በዐቢይ ቃል እንዘ ይበኪ ወይግዕር፤

እያለቀሰ እየጮኸ ቃሉን አሰምቶ ተናገረ፤

ወአውየወ በሕቁ፤

ፈጽሞ ጮኸ ፤

ወሰጠጠ አልባሲሁ፤

ልብሱን ቀደደ፤ ራቁቱን ሆነ፤

፲፯፤ ወቦአ ውስተ ደብተራ ኀበ ተኀድር ዮዲት፤

ዮዲት ወደምታድርበት ድንኳን ገባ፤

ወኢረከባ፤

አላገኛትም፤

ወሮፀ ኀበ ሕዝቡ፤

ወደወገኖቹ ፈጥኖ ሄደ፤

ወጸርሐ ሎሙ ወይቤሎሙ፤

ጮሆ እንዲህ አላቸው፤



፲፰፤ ዐለዉነ ዐለዉነ አግብርት፤

እኒህ ባሮች ከዱን ከዱን አላቸው፤

አሐቲ ብእሲት ዕብራዊት ገብረት ኃሣረ ላዕለ ቤተ ናቡከደነፆር ንጉሥ፤

አንዲት ዕብራዊት ሴት በንጉሡ በናቡከነፆር ቤት ላይ ተዋርዶ አደረገች፤

ወናሁ ሆሎፎርኒስ ውዱቅ ውስተ ምድር በድኑ፤

እነሆ የሆሎፎርኒስ በድኑ ከመሬት ወድቋል፤

ወኢሀለወ ርእሱ ላዕሌሁ፤

ቸብቸቦው የለም፤

፲፱፤ ወሶበ ሰምዑ ዘንተ ነገረ መላእክተ ኃይሎሙ ለአሶር ሰጠጡ አልባሲሆሙ፤

የኃያላኑ ሠራዊት አለቆች ይህን በሰሙ ጊዜ ልብሳቸውን ቀደዱ፤ ራቁታቸውን ሆኑ፤

ወደንገፀት ነፍሶሙ ፈድፋደ፤

ልቡናቸው ፈጽማ ደነገጠች፤

ወጸርሑ ወአውየዉ በዐቢይ ቃል ጥቀ፤ በማዕከለ ትዕይንት፤

በሠፈሩ መካከል ቃላቸውን አሰምተው ጮሁ፤

# ምዕራፍ ፲፭

## ገባዔ፤

፩፤ ወሶበ ሰምዑ እለ ውስተ ተዓይን ሀለዉ ደንገጹ እሙንቱኒ በበይነ ዘኮነ፤

በከተማ ያሉ ሰዎች ይህን በሰሙ ጊዜ ስለ ተደረገው ነገር እነዚህም ደነገጡ፤

፪፤ ወአኃዞሙ ፍርሃት ወረዓድ፤

ፍርሃት ረዓድ ያዛቸው፤

ወአልቦ እንከ ሰብእ ዘቆመ ምስለ ቢጹ፤

ከባልንጀራው ጋራ አብሮ አንድ ሰው የቆመ የለም፤

አላ ደንገጸሙ ጕዩ ኵሎሙ ኅቡረ ውስተ ኵሉ ፍናው፤

ሁሉም ደንግጠው በየጎዳናቸው ተበተኑ እንጅ ፤

ወውስተ ሐቅል፤

ወደምድረ በዳው ሸሹ፤

ወውስተ አድባር፤

ወደ ተራራው ሸሹ፤

፫፤ ወእለ ውስተ ተዓይን፤

በከተማ ያሉ፤

ወእለ ውስተ አድባር ዘአውደ ቤጤልዋ እሙንቱኒ መምዑ ወጐዩ፤

በቤጤልዋ ዙሪያ በተራሮች ያሉ ሁሉ እነዚህም ተሸበሩ፤ ሸሹ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወውእተ ጊዜ ተንሥኡ ደቂቀ እሥራኤል ኵሎሙ መስተቃትላን ዕደው ወዴገንዎሙ፤

ያን ጊዜ የእስራኤል ልጆች አርበኞች ሁሉ ተነሥተው ተከተሏቸው፡

፬፤ ወለአከ ዖዝያን ውስተ ቤሎ ወበስቴሞስ ወቤቢ፡ ወኮቤ፡ ወቆላ፡ ውስተ ኵሉ ደወለ እስራኤል፤

እኒህ ሁሉ የእሥራኤል ሀገሮች ናቸው ዖዝያን ወደነዚህ ሁሉ ላከ፡

ይዜንዉ በእንተ ዘኮነ፤

የሆነውን ነገር ይናገሩ ዘንድ ላከ፡

ወከመ ይርድኡ ኵሎሙ ወይዴግኑ ፀሮሙ፤

ሁሉን ይረዱ ዘንድ ጠላቶ ቻቸውን ይከተሉ ዘንድ፡

ወይቅትልዎሙ፤

ያጠፏቸው ዘንድ፡

፭፡ ወሶበ ሰምዑ ደቂቀ እስራኤል ዴገኑ ኵሎሙ ኅቡረ፤

የእስራኤል ልጆች ይህን በሰሙ ጊዜ ሁሉም አንድ ሁነው ተከተሉ፡

ወቀተልዎሙ እስከ ኮቤ፤

እስከ ኮቤ ድረስ አጠፏቸው፡

ወከማሁ እለ እምኢየሩሳሌም መጽኡ፤

አሁን እንደተናገርነው ከኢየሩ ሳሌም መጡ፡

ወእምኵሉ ደወሎሙ፤

ከአውራጃቸው ሁሉ መጡ፡

እስመ ዜነውዎሙ ዘከመ ኮነ በትዕይንተ ፀሮሙ፤

በጠላቶቻቸው ከተማ የሆነውን ነግረዋቸዋልና፡

ወእለኒ እምነ ገሊላ ወእምነ ገለዓድ ዴገንዎሙ፤

በገሊላና በገለዓድ ያሉም ተከተሏቸው፡

ወቀተልዎሙ ዓቢየ ቀትለ፤

ጽኑ ሰልፍ አድርገው አጠ ፏአቸው፡

እስከ አደዉ እምደማስቆ ወእም ደወላ፤

ከደማስቆና ካውራጃዋ እስኪ አልፉ ድረስ፡

፮፡ እለሰ ይነብሩ ውስተ ቤጤልዋ ወረዱ ውስተ ትዕይንቶሙ ለአሶር፤

በቤጤልዋ የሚኖሩ ሰዎች ግን ወደ ኃያላኑ ሠፈር ወረዱ፡

ወተሐብለይዎሙ፤

በዘበዟቸው፡

ወብዕሉ ፈድፋደ፤

እጅግ ከበሩ፡

፯፡ ወእምዝ ገብዑ ደቂቀ እሥራ ኤል እምነበ ቀተሉ፤

ከዚህ በኋላ እሥራኤል ከተዋ ገብት ተመለሱ፡



ወአስተጋብኡ ኵሎ ዘተርፈ አዕፃዳተ፤

የቀረውን ድንኳኑን ሰበሰቡ፡

ወአህጉሪሆሙኒ ዘውስተ አድባር፤

በተራራው በኮረብታው ያለ ውን ሀገር ሁሉ እጅ አደረጉ፡

ወዘውስተ ምድር፤

በምድር ያለውን መንደሩን እጅ አደረጉ፡

እስመ እምብዙኅ መዋዕል ነሥእዎሙ ዓቢየ ደወሎሙ፤

ከብዙ ዘመን ጀምሮ ሀገራቸውን ወስደውባቸው ነበረና፡

፰፡ ወመጽአ ኢዮአቄም ካህን ዐቢይ ወአዕረጎሙ ለደቂቀ እሥራ ኤል እለ ይነብሩ ኢየሩሳሌም፤

ደጉ ካህን ኢዮአቄም መጥቶ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ የእሥራ ኤልን ልጆች ይዟቸው ወጣ፡

ወመጽኡ ከመ ይርአዩ ሠናይተ እንተ ገብረ እግዚአብሔር ለእስራ ኤል፤

እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደ ረገውን ተድላ ደስታ ያዩ ዘንድ መጡ፡

ወከመ ይርአይዋ ለዮዲት፤

ዮዲትን ያዩአት ዘንድ፡

ወከመ ይግበሩ ምስሌሃ ሰላመ፤

ከሷም ጋራ ፍቅር አንድነትን ያደርጉ ዘንድ፡

፱፡ ወሶበ ቦኡ ኀቤሃ ኵሎሙ ኅቡረ ባረክዋ፤

ወደሷ በገቡ ጊዜ ሁሉም አንድ ሁነው አመሰገኗት መረቋት፡

ወይቤልዋ አንቲ ይእቲ ላዕለ ኢየሩሳሌም፤

በኢየሩሳሌም እመቤት አንች ነሽ አሏት፡

ወአንቲ ይእቲ ዕበዮሙ ለደቂቀ እሥራኤል፤

የእስራኤል ልጆች ክብራቸው አንች ነሽ፡

ወአንቲ ይእቲ ትምክህቶሙ ለሕዝብነ፤

የወገኖቻችን መመኪያ አንቺ ነሽ፡

፲፡ እስመ ተገብረ ዝንቱ ኵሉ በእዴኪ፡

ይኸ ሁሉ በአንቺ እጅ ተደርጓ ልና፡

ወገበርኪ ዘንተ ሠናይተ በውስተ እስራኤል፤

ይህን ተድላ ደስታ ለእሥራኤል አደረግሽ፡

ወሠምረ ቦሙ እግዚአብሔር፤

ኪያሆሙ ሲል ነው፡ እግዚአ ብሔር እሳቸውን ወደዳቸው፡

ኩኒ ቡርክተ በኀበ እግዚአብሔር ዘኵሎ ይመልክ ለዓለመ ዓለም፤

ለዘለዓለም ሁሉን በሚገዛ በእግዚአብሔር ዘንድ ንእድ ክብርት ሁኚ፡

www.ethiopianorthodox.org

፯፡ ወእግዚአብሔር ዘኵሎ ይመልክ ቀተሎሙ በእደ ብእሲት፡

ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር በዮዲት እጅ አጠፋቸው፡

፰፡ እስመ ኢወድቀ ጽንአሙ በእደ ወሬዛ፡

አርበኞቻቸው በጎልማሳ እጅ አልጠፉምና፡

ወአኮ ደቂቀ ጤቤኖን ዘቀተልዎሙ፣

የኃያላኑ ልጆች የገደሏቸው አይደለም፡

ወአኮ እለ ያርብሕ ዐበይት ዘሞዕ ዎሙ፡

አርበኞች ድል የነሷቸው አይደለም፡

ዘእንበለ ዮዲት ወለተ ሜራሪ፡

በደካማይቱ በኔ እጅ ነው እንጂ፡

በስነ ገጻ አድከሞቶ፣

በመልኳ ደም ግባት አለዘ በችው፣ አነኑለለችው፡

፱፡ ውነደገት አልባሰ መበለታ ላዕሌሆሙ ለእለ የሐምሙ በውስተ እስራኤል፡

በአዘኑ በእሥራኤል ፊት የድኅነቷን ልብስ ትታ ሰርመዴዋን አደረገች፡

፲፡ ወተቀብዐት ገጻ ዕፍረተ፣

ሽቱውን ተቀባች፡

ወተጸፍረት ርእሳ፡

ራሷን ተሠራች፡

ወተከፍለት፡

ከፍላ ከፍላ ተሠራች፡

ወለብሰት አልባሰ አግያት ለአስሕቶቱ፣

እሱን ለማሳት የቁንጅናቷን ልብስ ለበሰች፡ አንድም የጌጥ ልብስ ነጭ ሐር ለበሰች አጌ ያለውን ይዞ፡

ወተስእነት አሣዕኒሃ፣

ጫማውን አደረገች፡

፲፩፡ ወበስና ተሐይዳ አዕይንቲሁ፣

በመልኳ ደም ግባት ዓይኑ ተቀማ፡

ወላሕያ ፄወዋ ለነፍሱ፣

መልኳ ልቡናውን ማረከች፡

ሐለፈ ሰይፍ እንተ ክሳዱ፡

ሰይፍ በአንገቱ ላይ ተመላለሰ፡

፲፪፡ ወደንገፁ ፋርስ እምተሀብሎታ፣

ከኃይሏ ጽናት የተነሣ የፋርስ ሰዎች ደነገጡ፡ አንድም እምትባአ ይላል፡ አንድም እምተኃብሎታ ይላል፡

ወፈርሑ ሜዶን እምነ ትብዓ፣

እምተኃይሎታ ሲል ነው፡ በኃይሏ ጽናት የተነሣ ፈሩ፡

፲፫፡ ወውእተ ጊዜ ወውዑ ሕሙማንየ፣

ያን ጊዜ ያዘኑ እስራኤል ደነፉ፡



ወፈርሑ ድውያንየ፣

መከራ የተቀበሉ እሥራኤል የደስታ ፍርሃት ፈሩ፡

ወደንገፁ፣

የደስታ ድንጋጤ ደነገጡ፡

ወዐልዓሉ ቃሎሙ፣

ቃላቸውን ከፍ ከፍ አደረጉ፡

፲፬፡ ወዴገንሙ ደቂቀ አዋልድየ ወወግዕዎሙ፣

የልጆቼ ልጆች ተከትለው ወጓቸው፡

ወወራዙቶሙኒ ተደራበይዎሙ፣

ጎልማሶቻችን ተወራወሯቸው፡ ተመካከቷቸው፡

ወጠፍኡ እምፀባዒተ እግዚአብሔር፣

ከእግዚአብሔር አርበኞች ከእሥራኤል የተነሳ ጠፉ፡

፲፭፡ አነብብ ስብሐተ ለእግዚአብሔር፣

በውስጥ በአፍአ ምስጋናውን እናገራለሁ፡

አነብብ ስብሐተ ሐዲስ፡ ለእግዚአብሔር ፣

ለእግዚአብሔር አዲስ ምስጋና አቀርባለሁ፡

፲፮፡ እግዚአብሔርሰ ዐቢይ ውእቱ፡

እግዚአብሔር ግን ገናና ነው፡

ወክቡር ፈድፋደ፣

እጅግ ክቡር ነው፡

ወመድምም ኃይሉ፣

ኃይሉም ድንቅ ነው፡

፲፯፡ ለከ ይገንዩ ኵሉ ተግባርከ፣

ፍጥረቶችህ ሁሉ ላንተ ይገዙልሃል፡

እስመ ትቤ ወኮኑ፣

አንተ አዝዘህ ተፈጥረዋልና፡

ወፈኖከ መንፈሰከ፡

መንፈሰ ረድኤትህን ሰደድህ፡

ወተሐንፁ፣

በረድኤት ጸኑ፡ አንድም መንፈስ ቅዱስን ሰድደህ በልጅነት ጸኑ፡

ወአልቦ ዘኢይትኤዘዝ በቃልከ፡

በቃልህ የማይታዘዝ የለም፡ አንድም በልጅህ የማይታዘዝ የለም፡ አንድም ለወንጌል የማይታዘዝ የለም፡ የዮዲት ሐዲሷ ይህ ነው፡

፲፰፡ እስመ አድባርኒ መሠረቶሙ ይትከወሱ፡

ምስለ ማያት፡ ነገሥታቱ ከሠራዊቱ ጋራ ሥር መሠረታቸው ይጠፋሉ፡

ወይትከወሱ ሰማያትኒ፣

ልዑላኑም ይጠፋሉ፡

ወኰኵሕኒ ከመ መዓረ ግራ ይትመሰው እምቅድመ ገጽከ፣

አርበኞውም ሰም አደሮማር ቀልጦ እንዲጠፋ ይጠፋል፡

www.ethiopianorthodox.org

ወዓዲ ተሠሃሎሙ ለእለ ይፈርሁከ፤

ዳግመኛ የሚፈሩህን ይቅር በላቸው።

፲፱፡ እስመ ኢየአክል ኵሉ መሥዋዕት ለመዓዛ ሠናይ፤

እንደ አምላክነትህስ መሥዋዕቱን ሁሉ ወድደህ ልትቀበለው አይበቃም።

ወይውህድ ኵሉ ስብሕ እምነ ቍርባንከ፤

ስቡ ሁሉ ቁርባን ሁኖ ሊጤስ አይበቃም።

ዘሰ ይፈርሆ ለእግዚአብሔር ዓቢይ ውእቱ በኵሉ ጊዜ፤

እግዚአብሔርን የሚያመልከው ሰው ግን በየጊዜው ሁሉ ገናና ነው።

፳፡ አሌ ሎሙ ለአሕዛብ እለ ይቀውሙ ዲ በዘመድየ፤

በወገኖቼ ላይ በጠላትነት ለሚነሡ ለጽርዓውያን ወዮላቸው፤ አንድም ለሐሣውያነ መሲሕ ወዮላቸው።

እግዚአብሔር ዘኵሎ ይመልክ ይትቤቀሎሙ በዕለተ ደይን፤

ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር በቍርጥ ፍርድ ቀን ተበቅሎ ያጠፋቸዋል።

፳፩፡ ወይፌኑ እሳተ ወእፄ ውስተ ሥጋሆሙ፤

እጼሁ ዘኢይነውም እሳቱ ዘኢይጠፍዕ ያለውን ያመጣባቸዋል።

ወይበክዩ በሕማም ዘለዓለም፤

በመከራ ተይዘው ለዘለዓለሙ ያለቅሳሉ፤ አንድም የጌታን መከራ እያሰቡ ያለቅሳሉ።

፳፪፡ ወሶበ በጽሑ ኢየሩሳሌም ሰገዱ ለእግዚአብሔር፤

ኢየሩሳሌም በደረሱ ጊዜ ለእግዚአብሔር ሰገዱ።

ወሶበ አንጽሑ ርእሶሙ ሕዝብ አብኡ ቊርባኖሙ፤

ሕዝቡ ሰውነታቸውን አንጽተው መብዓውን አቀረቡ።

ወዘበፈቃዶሙ ሀብቶሙ፤

በፈቃዳቸው ያመጡትን አቀረቡ።

፳፫፡ ወአንበረት ዮዲት ኵሎ ንዋዮ ለሆሎፎርኒስ ዘወሀብዋ ሕዝብ፤

ሕዝቡ የሠጧትን የሆሎፎርኒስን ገንዘብ አኖረች።

፳፬፡ ተፈሥሑ ሕዝብ በኢየሩሳሌም በቅድመ መቅደስ ሠለስተ አውራኀ፤

ሕዝቡ በኢየሩሳሌም በቤተ መቅደስ አንፃር ሦስት ወር ተድላ ደስታ አደረጉ።

ወዮዲትኒ ነበረት ምስሌሆሙ፤

ዮዲትም ከነዚያ ጋራ ነበረች።

፳፭፡ ወእምድኅረ እማንቱ መዋዕል አተዉ ኵሉ ውስተ ርስቱ፤

ከሦስት ወር በኋላ ሁሉም ወደ ርስቱ ገባ።



ወዮዲትኒ አተወት ቤጤልዋ፤

ዮዲትም ወደቤጤልዋ ገባች።

ወነበረት ውስተ ተግባራ፤

በብሕትውና ጸንታ ኖረች።

ወኮነት ክብርተ በመዋዕሊሃ በኵሉ ምድር፤

ባለ በዘመኗ በዓለሙ ሁሉ ክብራ ኖረች።

፳፮፡ ወብዙኃን እለ ይፈቅድዋ፤

እናግባሽ ያሏት ብዙ ናቸው።

ወአልቦ ብእሲ ዘአእመራ በኵሉ መዋዕለ ሕይወታ፤

ባለ በዘመኗ ሁሉ ያገባት የለም።

እምአመ ሞተ ምናሴ ምታ፤

ባሏ ምናሴ ከሞተ ጀምሮ፤

ወተቀብረ ኀበ ሕዝቡ፤

ከወገኖቹ ከተጨመረ ጀምሮ ያገባት የለም።

፳፯፡ ወዐብየት ፈድፋደ፤

እጅግ ከበረች።

፳፰፡ ወረስዓት በቤተ ምናሴ ምታ፤

በባሏ በምናሴ ቤት አረጀች።

፻ወ፭ቱ ዓመታቲሃ፤

ዘመኗም መቶ አምስት ነው።

ወአግዓዘታ ለእንታክቲ ወለታ፤

ገረዷንም ነፃ አወጣቻት።

ወሞተት በቤጤልዋ፤

በቤጤልዋ ሞተች።

ወተቀብረት ውስተ በዓተ ምናሴ ምታ፤

በባሏ በምናሴ ቦታ ተቀበረች።

፴፡ ወለሀውዋ ቤተ እስራኤል ሰቡዓ መዋዕለ፤

የእስራኤል ወገኖች ሰባት ቀን አለቀሱላት፤ የሰባት ቀን ፍታት አምሳል።

ወከፈለት ንዋያ እምቅድመ ትሙት ለኵሉ ቅሩበ ምናሴ ምታ፤

ከመሞቷ አስቀድማ ገንዘቧን ከፍላ የባሏን ገንዘብ ለባሏ ዘመዶች ሰጠች።

ወለቅሩበ አዝማዲሃ፤

የሷን ገንዘብ ለሷ ዘመዶች ሰጠች።

፴፩፡ ወአልቦ እንከ ዘገረሞሙ ለደቂቀ እሥራኤል በመዋዕለ ዮዲት፤

በዮዲት ዘመን የእስራኤልን ልጆች ያስፈራቸው የለም፤ አንድም ዘረገሞሙ ይላል፡

ወዓዲ እምድኅረ ሞተት ብዙኃ መዋዕለ፤

እሷም ከሞተች በኋላ ብዙ ዘመን ያስፈራቸው የለም።

ተፈጸመ ዘዮዲት በረከተ ጸሎታ የሃሉ ምስሌነ ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ለዓለመ ዓለም አሜን።

የዮዲት ገባዔ ፲፮ ነው።

www.ethiopianorthodox.org